
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር 7ኛ ዓመት ቁጥር 1 የካቲት/መጋቢት

## የአባ ጰንጠሌዎን ገዳም– አክሱም አጠገብ

(ታሪኩን ወደፊት እናወጣለን)



# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ከመገሰጽ ይልቅ...

አንዳንድ ወጣት ክርስቲያኖች ከቤተክርስቲያን በመራቅ /በንዝህላልነት/ ሕይወታቸውን ሲያሳልፉ፡ሌሎቹ ደግሞ ወደ ባእድ እምነት እግራቸውን ሲያዞሩ እንመለከታለን። ለዚህም በመላምትነት በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ወጣቶቹ ቤተክርስቲያንን አውቀው እንዳይቀርቧት እንቅፋት የሚሆንባቸው የቋንቋ ችግር ነው። እንደእኔ ከሆነ ይህ ጉዳይ እንኳንስ አሁን በብዙው የቅዳሴ ክፍልና የመጻሕፍት ንባብ አማርኛ እንዲያገለግል በሆነበት ዘመን ቀርቶ ድሮም ቢሆን የቋንቋ ችግር ከሚወዷት ቤተክርስቲያን የሚያስኮበልል አይደለም። የሆነው ሆኖ «በጥበብ ኑሩ» እንደተባለ የሚቆሙበትን ሳያውቁ ወደ ተሳሳተ ቦታ የሚሄዱትን ወጣቶች መታደግ ከቤተክርስቲያን በተለይ ከሰባክያነ ወንጌል ብዙ ይጠበቃል። ሰባክያን የወጣቶቹን ድርጊት እንደችልተኝነት ወይም ለዘብተኝነት ቆጥሮ ከመገሰጽ ይልቅ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ወጣቶቹን በሚገባቸው ቋንቋና አቀራረብ ቢያስጠኑአቸው መልካም ነው እላለሁ።

ወልደ መድኅን
ከባሌ /ሮቤ/

## ድርሻችንን ዕንወቅ

በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ለሁሉ ነገር ሥርዓት አላት። ታዲያ አሁን አሁን በተለይ «በሥርዓተ ቅዳሴ» ላይ የሚታየው ሥርዓት መስመር እየለቀቀ መጥቷል። በቅዳሴያችን ሥርዓት መሠረት የካህን፣ የዲያቆን፣ የሕዝብ ተብሎ ተለይቶ ሳለ ካለማወቅ ይሁን ከግድየለሽነት የተነሣ ብዙዎች በተለይ እኅቶቻችን የካህኑን ከካህኑ ጋር የዲያቆኑን ከዲያቆኑ ጋር ሲሉት ይሰማል። ይህ ጉዳይ በአጭሩ ካልተቀጨ እነዚህ ሰዎች ቆይተው «ማዕሠረ ኃጢአት እግዚአብሔር ይፍታ» ማለታቸው አይቀርምና ድርሻችንን ዕንወቅ፣ያላወቁትንም እናሳውቅ።

ሰይፈ ገብርኤል ዓለማየሁ
ከኮተቤ ቅ/ሚካኤል

## በማስተዋል ይሁን

ከባሕር ማዶዎቹ እጃችንን ዘርግተን ከተቀበልናቸው ባዕድ ባሕሎች አንዱ በበዓላት ጊዜ ልዩ ልዩ ካርዶችን መለዋወጥ ነው። በመሆኑም የበዓላት ሰሞን ፈላጊዎች ካርዶችን ለመግዛት የመትጋታቸውን ያህል አቅራቢዎቹ ነጋዴዎችም ገዥዎችን ለማስደሰት ይተጋሉ። ከሚተጉባቸው መንገዶች አንዱ ልዩ ልዩ «ሃይማኖታዊ መልእክት ያላቸውን» ካርዶች ፎቶግራፍ በማንሣት እነሱን በማባዛት ነው። እነዚህ ሰዎች ካርዶቹን ሲያባዙ ግን መልእክታቸው ምንድነው? ብለው አይመረምሩም ወይም ደግሞ አያስመረምሩም። በዚህ የተነሣ ምእመናን ከካርዱ የተሳሳተ መልእክት ወስደው ሲሳሳቱ ይታያሉ። በዚህ ላይ እኔ ያየሁትን ልንገራችሁ። እኔ ባለሁበት ከተማ ባሳለፍነው የብርሃን ልደቱ በዓል ሰሞን አንድ ካርድ ለሽያጭ ቀርቦ ነበር። በካርዱ ላይ ያለው ሥዕል እንደሚከተለው ነው። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ተሸክሞ ከሥሩ እንኳን ለብርሃን ልደቱ አደረሰዎት ይላል። ወይ ለትንሣኤው ወይ ለልደቱ ያልሆነ ካርድ ይሏል ይህ ነው። ስለዚህ ምእመናን ከቤተክርስቲያናችን ዶግማ፣ቀኖናና የሥዕል ጥበብ ውጭ የሆኑ ሥዕላትም ለገበያ ይቀርባሉና ስንገዛ በማስተዋል ይሁን።

ዘላለም መንግሥቱ
ጊደሌ ሆኅተ ብርሃን ሰንበት ት/ቤት

## ስሙ ቅዱስ ሆኖ ሳለ

ግሩም የሆነ የእግዚአብሔር ስሙ፡ሕሙማኑን የሚፈውስ፡ለምጻሙን የሚያነጻ፣እውሩን የሚያበራ፣የጐበጠውን የሚያቃና፣የርኩሳን መናፍስት ማባረሪያ የሰማዕታት የተጋድሏቸው ሞገስ፣ ለታመኑበት የሕይወታቸው መታወቂያ ማኅተም ሆኖ ሳለ በየትምህርት ቤቱ በየስልክ ቤቱ በየመፀዳጃ ቤቱ ግድግዳ ላይ «ኢየሱስ ጌታ ነው» «መዳን በኢየሱስ ብቻ ነው» ሌላም ሌላም እያሉ ይጽፋሉ። ታዲያ ቅዱስ የሆነው ስሙ ክቡር ሆኖ ሳለ መከበርና መፈራት ሲገባው በየግድግዳው ላይ መጻፍ ምን ይፈይድ ይሆን?

ስሙን መዘባበቻ ከማድረግ በቀር። ስሙን ብናቀል እኛው እንቀላለን፤ ለመቅሰፍትም ይዳርገናልና በየግድግዳው ከመጻፍ እጃችን ቢቆጠብ መልካም ነው።

ሲሳይ ታከለ
ድሬዳዋ

## የመናፍቃኑ በሽታ እንዳይጋባብን

ብዙ ጀማሪ ክርስቲያን ወጣቶች ስሜታውያን ናቸው። ለሁሉ ነገር ፈጣን ናቸው። ግን አይዘልቁበትም። ይህን ያልኩበት ምክንያት ለግል ጉዳይ ከአዲስ አበባ ወጣ ብዬ የታዘብኩት ነገር አንገቴን ስላስደፋኝ ነው። በአካባቢው ወደምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ልማር ከጉባኤው ተቀላቀልኩኝ። ነገር ግን ስብከቱን ስሰማ ውስጤ ረመጥ የፈሰሰበት ያህል ተቃጠለ። ሰባኪው የተማረ አልነበረም። ይህ በቤተክርስቲያን ትምህርት ያልተገራው ሰባኪ ሲጨርስ እንደቤተክርስቲያን ልጅነቴ ስህተቱን አሳየው ዘንድ በፍቅር አነጋገርኩት። እርሱም ገና ጀማሪ ክርስቲያን እንደሆነ ሳይደብቅ ገለጸልኝ። እኔም ለተንኮል ሳይሆን ፊልጶስ ገና ሲጠራ ሰባኪ ሆኖ ክርስቶስን በአዋቂ አነጋገር የዮሴፍ ልጅ እንዳለው /ዮሐ 1÷46/ ዓይነት መረዳትን ተረዳሁለት። ልጁም ምክሬን ሳይንቅ ስህተቱን ተቀብሎ በፍቅር ተለያየን። ይሄስ ልጅ ከስህተቱ ተመለሰ። ስንት የማይመለሱ አሉ መሰላችሁ። ስህተትን ማመን ኃጢአት ይመስላቸዋል። ከእኛም ወገን ቢሆን ገና እንደመጣን ደርሶ ሰባኪ የምንሆን ወጣቶች አለን። ዓላማው በጐ ሆኖ ሳለ ስህተታችንን ሲነግሩን እንደ አራስ ነብር እንሆናለን። እባካችሁ ሳይጠኑ አስተምራለሁ የማለት የመናፍቃኑ በሽታ እንዳይጋባብን እንጠንቀቅ።

አትናቴዎስ
ከገነተ ኢየሱስ

ከአሠርቱ ትእዛዛት መካከል የሰዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚመለከቱትን ሁሉ በመተሳሰፍ የሚበድል ሰው የፍቅርን ሕግ ይጥሳል። ባልንጀራውን የማይወድ ከሆነ ይህ ሰው ትእዛዛትን እንዳይጥስ፣ሕግም እንዳያፈርስ የሚከለክለው ገደብ የለም።

/ትምህርተ ሃይማኖት/



የቤተክህነት ሠራተኞች ሁለት ዓይነት ናቸው። ሥልጣነ ክህነት ያላቸውና የሌላቸው። በመሆኑም ቤተክህነት የራሷ ሠራተኞች እስካሏት ድረስ በራሷ ደንብና መመሪያ መሠረት ታስተዳድራለች። ደሞዛቸውን በሚመለከትም ያው እንደቤተክርስቲያኗ አቅም እንደየደረጃው ይገኛሉ።

/ቃለ መጠይቅ/

«አንግባ» አለ አንዱ ጥቂት ቆም ብሎና ተከታትለው ገቡ። ግቢው ጸጥ ብሏል። ወደቤት ዘለቁ። አሁን ሰው የለም። አዳራሹን አልፈው ገቡ። ሰው ተሰብስቧል። ግን ጸጥታ ነግሦአል። እንዱን ጠጋ ብለው የምንድን ነው?

ኪነ ጥበብ

*ምንም እንኳን ለኢትዮጵያውያን ከሰፊው ርስታቸው ተቆርጦ ኩሽና የማታህለ ቦታ ቢሰጣቸው ክርክር አልተቋረጠም ነበር። ይልቁንም በዚያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት የመንግሥታቸውን ድጋፍ እያገኙ ስለሚሠሩ ክርክራቸውና አቤቱታቸውን የበለጠ እያጠናከሩ መጡ።*

*/እናስተዋውቃችሁ/*

*ጥንትም ሆነ ዛሬ የሰው ልጅ ሰላም እየነሡት ከናረት ታላላቅ በሽታዎች መካከል ዘረኝነት አንዱ ነው። ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች ትኩረት ከሰጧቸው ወንጀሎች መካከል የዘር ማጥፋት ወንጀል አንዱ መሆኑ ይህንኑ ያመለክታል።*

ምንተ ንግበር


ዋና አዘጋጅ- ግርማ ወ/ሩፋኤል
ም/ዋና አዘጋጅ- መርሻ አለኸኝ

ስልክ 114870
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ



# ሐመር

7ኛ ዓመት ቁጥር 1
የካቲት/መጋቢት 1991 ዓ.ም


## ይዘት


**የማኅበሩ መልእክት**
አንገው ቢለያይም አንድ ነው ሸንበቆው....2

**ደብዳቤዎች**.....................................4

- መቅደሴን ፍሩ..................................6

**ትምህርተ ሃይማኖት**
- እናት እናትህ ....................................8
- ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ................9

**ቃለ መጠይቅ** ..................................11

**የጥያቄዎቻችሁ መልሶች**......................15

**ኪነ ጥበብ**
- በኢሊባቦር ጫካዎች ውስጥ..................17

**እናስተዋውቃችሁ**
- አባ ጀሮም.........................................20
- ዴር -ኤል-ሡልጣን...........................22

**ዓምደ ወራዙት**
- የኦርቶዶክሳዊ ወጣቶች የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት «ከመፈቃቀድ»ና «ከመጠናናት» አንጻር ........24

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**
- ሥራ ፈትነት .....................................27
- ዘረኝነት አሸሸ...................................29
- ሞቴን ከመጠበቅ ሌላ..........................30

**ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ**
- ንዋያተ ቅድሳት እና አያያዛቸው ....31



*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።*

# እንንው ቢለያይም አንድ ነው እንበቆ

«በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤ አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፣ወንድም ሴትም የለም፣ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» /ገላ.3÷27-29/

ይህንን ቃል ያስተላለፈው ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ነው። ወደ ክርስትና ከመጡ በኋላ «የእግዚአብሔር ምርጦች -አይሁድ» ወይም «ከቁልፈታቸው ያልተገዘሩ፣ጣዖት አምላኪ አሕዛብ፣ባሪያ ወይም ባርነት ያልደረሰባት ጨዋ»፤« በጉል በቱ-በዕውቀቱ የሚመካ ወንድ» ወይም «ከቤት መውጣት - ካደባባይ መዋል የማይገባት ሴት» ወዘተ የሚል ምድራዊ ክፍፍል አለመኖሩን ያስተማረበት ኃይለ ቃል ነው።

ክርስትና ፍቅር ነው። ፍቅር ደግሞ ከሌላው ጋር መስማማትና በአንድነት መኖር ነው። ሰይጣን ግን ይህንን አይወድም። የሚያስደስተው መለያየት፣በሌላው ላይ መነሣት፣ለወንድም ለእኅት እንቅፋት ማኖር ነውና። የግብር ልጆቹም የሚያደርጉት ይህንኑ ነው።

ሰይጣን በየዘመኑ አንዱን ከአንዱ ለመለየት የሚጠቀምባቸውን ሰዎች ለማስነሣት ይጥራል። ከሐዋርያት መካከል ይሁዳን፣ከካህናት መካከል አርዮስን፣ከጳጳሳት መካከል ንስጥሮስን፣መቅዶንዮስንና ልዮንን አስነሥቷል። ሁሉም ግን አልፈዋል- ጠፍተዋል። ይሁን እንጂ ጥንተ ጠላታችን ለማለያየት መጣሩን አላቆመም፤ ሊያቆምም አይችልም። የማሰናከያ ዘዴዎችን ይለዋውጣል። ከጊዜው የዕድገት ደረጃ፣ከሰው ልጅ የልብ መሻት ጋር የተገናኘ ነው።

መለያየት የፍቅር መጉደል፣«የኔ ይበልጣል» የማለት፣የመንፈሳዊነት መጉደል ውጤት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። መድኃኒቱም ፍቅር፣ራስን ዝቅ ማድረግ /በትኅትና/ ፣ከእኔ ወንድሜ ይበልጣል ማለት ነው። ይህንን የሚያደርግ ሲጠፋ «እልህ-ሃይማኖት እየሆነ» አገር ይጠፋል። ይህንን ሁሉ ለማለት የገፋፋን አንዳንድ ሰዎች በጊዜያችን ይዘዋቸው የተነሷቸው «ስብከቶች» ናቸው።

የነዚህ ሰዎች ስብከቶች ቤተክርስቲያን «የተወሰኑ ዘሮች፣ነገዶች፣ቋንቋዎችና ግለሰቦች «የግል-ሀብት» እንደሆነች ሌሎቹ ግን የእንጀራ ልጆች መሆናቸውን፣ሊከተሉት የሚገባው እምነትም «ሌላ» /ፈረንጆቹ ያመጡት/ መሆኑን የሚደሰኩሩ ናቸው። ከዚህ በፊት በዚሁ መጽሔታችን የማኅበሩ መልእክት ላይ እንዳሰፈርነው «ስንዴ ለመገበሪያነት የሚውለው ከቆላ ወይም ከደጋ ስለመጣ ሳይሆን ስንዴ ስለሆነ ብቻ ነው»

በሃይማኖት ውስጥ ትልቁ ቁም ነገር የአንድ ሰው ዘሩ፣ቋንቋውና ነገዱ አይደለም። በሃይማኖቱና በምግባሩ የተመሰከረለት መሆኑ እንጂ። ስለዚህም ነው «ከየት መጣህ? ቋንቋህ ምንድን ነው?» ብሎ መጠየቅ ነውር የሚሆነው። የሃይማኖተኛ ሰው ጥያቄ አይደለምና። እንዲህ ባይሆንማ ተሰዓቱ ቅዱሳን በሀገራችን ሥፍራ ባላገኙ ነበር። መመዘኛው ሃይማኖት ባይሆንማ ለ1600ዓመታት ከግብፅ አባቶችን ለማስመጣት ባልተጋን ነበር። መሠረቱ «ወልድ - ዋሕድ» የሚለው ትምህርተ-ሃይ ማኖት ባትሆንማ በኪደተ እግራቸው፣በጸሎታቸው አገራችንን የባረኩ አባቶችን ባላገኘን ነበር።

የእግዚአብሔር ሰው ሁሉም ሀገሩ፣ሁሉም ወገኑ፣ሁሉም ቋንቋው ነው። ለአብነትም የአባታችንን የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስን ታሪክ መመልከት እንችላለን። በሔዱበት ሁሉ በአገሩ ሕዝብ ቋንቋ አስተምረዋል። ሕዝቡም ወዷቸው አፍቅሯቸው ኖሯል። የመጡበት አገር የትም ይሁን የት ትምህርታቸውን የተቀበለ ሁሉም ልጃቸው ነበረ።

ቅዱስ አባታችን ተ/ሃይማኖትም በመላዋ ኢትዮጵያ ከመከበራቸው፣ከመዘከራቸው በተጨማሪ በምድረ ግብፅም ቤተመቅደሳቸው ሊኖር የቻለው ዋናው መመዘኛው ሃይማኖት በመሆኑ ነው። አባ ኤዎስጣቴዎስ

በአርመን ቤተክርስቲያን ያስተ ማሩትና የሚከበሩት በእምነት አንድ ስለሆንን ብቻ ነው:: የገ/መንፈስ ቅዱስ፣የተ/ሃይማኖት፣የተሰዓቱ ቅዱሳን ልጆችም ሌላ ውን ሰው ወገናቸው ፣ ወዳጃቸው፣ ዘመዳቸው የሚያደርጉት ስለ ሃይማኖቱ ብለው ነው:: ሃይማኖት አንድ የሚያደርግ ትልቅ መሣሪያ ነው:: ኢትዮጵያውያን የተለያየ ዘር፣ጎሣና ቋንቋ ቢሆኑም በአንድነት እግዚአብሔርን ለማመስገን የቻሉትም ለዚሁ ነው:: ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ እንደ አንድ ልብ መካሪ፣እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ለመሆን የተቻለውም ለዚህ ነው:: ይህ የማያስደስታቸው ወገኖች ግን ቤተክርስቲያኒቱን የተወሰኑ ብሔረሰቦች «የግል ገንዘብ» አስመስለው በማሣየት ችግር ለመፍጠር ይሞክራሉ:: ይህ ነገር ሐሰት መሆኑን ልቡናቸው ያውቀዋል:: የነርሱ ጭንቀት ግን «ነገሩ ትክክል ነው ወይም አይደለም» ሳይሆን «ሰዎችን ማሣሣት ችሏል ወይም አልቻለም?» ነው:: የሚከብደው ነገር መገንባት እንጂ ማፍረስ አይደለምና «ስብከታቸው» የአንዳንድ የዋሐንን ልቡና ለማሸፈት አያንስም::

የተንኮል ጥንስሳቸው ሥራ የሚሠራው ከሕፃናቱ ጀምሮ ነው:: በለጋ አእምሯቸው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርቲያን የነርሱ አለመሆኗን ይነግሯቸዋል:: የነርሱ እምነት «ሌላ» መሆኑን ያስርጿቸዋል:: ጊዜ ሲያልፍ በነዚህ ሕፃናት ልቡና የተቀረፀውን ይህንን የተሣሣተ ትምህርት ለመቅረፍ ያዳግታል:: ስለዚህም በጊዜው አፋጣኝ ርምጃ መውሰድ ይገባል::

እነዚህ ሰዎች በየፌርማታው በበራሪ ወረቀቶች፣በነዝናዛ ጭቅጭቆች መንጠቅ ያቃታቸውን ምእመን በማንነቱ፣በዘሩ፣በቋንቋው መጥተውበታል:: «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያንተን ዘርና ቋንቋ አትፈልግም» ብለውታል:: ይህ የነርሱ ስብከት ከእውነት የራቀ መሆኑን ለማሣየት ግን አፋጣኝ መልስ ያስፈልጋል:: አለመሆኑን መግለጥ ያሻል::

ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት:: ሐዋርያት ደግሞ ያስተማሩት በአንድ ቋንቋ ብቻ አይደለም:: እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ባወቀ እርሱ በገለጠላቸው ከ70 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች የወንጌልን ምሥ ጢር ለዓለም ሁሉ አስተምረዋል:: ጨለማውን በወንጌል ብርሃን አብርተዋል:: የነርሱን አሠረ ፍኖት ተከትለው የተነሡ ሌሎች አባቶቻችንም ያደረጉት ይህንኑ ነው:: በተለያዩ ቋንቋዎች «ወልድ-ዋሕድ» የሚለውን ትምህርት ለማዳረስ ተግተዋል::

በሀገራችንም ትምህርት ከጫፍ እስከ ጫፍ ተሰጥቷል:: ይህ የተደረገው ዘርና ጎሣ፣ቋንቋና ነገድ ተለይቶለት አይደለም:: በተለያዩ ችግሮች የትምህርቱ መሠራጨት ቢደክምም ቅሪቱ ግን ዛሬም አለ:: ለዚህም በተለያዩ ብሔረሰቦች የሚከበሩ የመስቀል በዓሎችን መመልከት ይቻላል:: የሚያስተ ምር፣የሚያጠምቅ በጠፋባቸው አካባቢዎች ሳይቀር ነገረ መስቀሉ ሙሉ በሙሉ አልጠፋም:: ንቅሣታቸው፣በዓላቶቻቸው፣አለባበሳቸው ይህንኑ ያጐላሉ:: እነዚህ ሰዎች በቅርቡ የወንጌል ትምህርት ስላላገኙ የክርስትና አሻራ አርማቸው ተዳፍኗል እንጂ አልጠፋም:: የሚቀሰቀሰው፣የሚያቀጣጥለው ይፈልጋል:: ስለዚህም የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሰባክያንን መላኩን ቤተክርስቲያን አጠናክራ ልትቀጥል ይገባታል::

በተለያዩ ቋንቋዎች ማስተማር ሐዋርያዊ ውርስ ነው:: ይህንን ሐዋርያዊ ውርስ በተግባር ማዋል ደግሞ የሐዋርያትን ሥርዓት የመከተላቸው መገለጫ ነው:: ይህ የማይዋጥላቸው ሐዋርያዊ ትምህርት የማይገባቸው ሰዎች ናቸው:: ሐዋርያውም «እምነት ከመስማት ነው፣መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» /ሮሜ.10÷17/ እንዳለ ሰዎች ያምኑ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰሙ፣ቃሉንም ይሰሙ ዘንድ በየቋንቋቸው ሊነገራቸው ይገባል:: ይህም ይሆን ዘንድ ቋንቋቸውን የሚያውቅ ሰባኪ ይፈልጋል::

ሰባው ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግሪክ የመተርጎማቸው፣አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንና ተሰዓቱ ቅዱሳን እንዲሁም አቡነ ሰላማ ዶግማዊ /መተርጉመ- መጻሕፍት/ የተለያዩ መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ የመተርጎማቸው ግቡ አንድ ነው:: ሰዎች ነገረ-እግዚአብሔርን እንዲማሩ ማድረግ:: ይህ ታላቅ መንፈሳዊ ተግባር መረሳት የለበትም:: መጻሕፍትን ወደተለያዩ የሀገራችን ቋንቋዎች መተርጎም ይጠበቅብናል:: ሁሉም በየእናት ቋንቋው የተዋሕዶን ትምህርት ይረዳ ዘንድ ጥረት መደረግ አለበት:: እጃቸውን ዘርግተው የቤተክርስቲያንን ትምህርት የሚጠብቁ በአፍሪካ፣በካሪቢያ፣በአውሮፓና በአሜሪካ የሚገኙ ጥቁር ወገኖቻችን ዘንድ ለመድረስ ከመጣራችን ጎንለጎን በአገር ውስጥ ያሉ ብዙ ወገኖቻችንንም ማስታወስ ያስፈልገናል::

መፍትሔውን ሁሉ የምንጠብቀው ግን ከአባቶች ብቻ መሆን የለበትም:: ሰ/ት/ቤቶችና ሰበካ ጉባኤዎች፣ምእመናን በጠቅላላው ብዙ ነገር ማድረግ ይጠበቅብናል:: ሰንበት ት/ቤቶች የጀመሩትን መልካም አገልግሎት መቀጠል አለባቸው:: ማዕከላዊ በሆነ መልኩ መዝሙሮችንና ትምህርቶችን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጎማቸውን መቀጠል አለባቸው:: የተተረጎሙ መዝሙሮችና ትምህርቶች ደግሞ በካሴትና በመጽሐፍ መልክ እየተዘጋጁ የሚሠራጩበት መንገድ እንዲታይ ከሚመለከታቸው የቤተክርስቲያን ክፍሎች ጋር መነጋገር ይጠ ይቃል::

ከዚህም በተጨማሪ አጥቢያ ሰበካ ጉባኤዎች ምእመናን በሚገባቸው ቋንቋ ትምህርት ያገኙ ዘንድ ነገሮችን ማመቻ ቸት አለባቸው:: ሌሎች ምእመናንንም ቤተክርስቲያን የኛ አለመሆኗን ለሚናገሩ ሰዎች መልስ ለመስጠ ት መትጋት አለ ብን:: በክርስቶስ ደም የተመሠረተች ቤተክርስቲያን የአንድ ዘር፣ቋንቋና ብሔረሰብ የግል ገንዘብ ሳትሆን የሁሉም /ዓለም አቀፋዊት/ መሆኗን መመስከር ይጠበቅብናል:: ሁላችን በክርስቶስ አንድ ነንና::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ደብዳቤዎች

## የዘወትር ጸሎቴ ነው

በሒሩት ገብረ ኪዳን የሚጻፈውና «ንዋያተ ቅድሳትና አያያዛቸው» በሚል ርዕስ በተከታታይ እየቀረበ ያለው ጽሑፍ የእያንዳንዱን ንዋያተ ቅድሳት ትርጉምና አገልግሎት እንድናውቅ ያደረገ በመሆኑ ጸሐፊዋም ሆነች እናንተ ትመሰገናላችሁ:: ጉኤ ዛለሁበት አጥቢያ ያሉ አባቶች እጅግ በጣም እየመረቋችሁ ነውና ይህም ይድረሳችሁ:: እዚህ እንዳለነው አንባ ብያን ሁሉ መጽሔቷ የምትደርሳቸው ሁሉ እንደሚመርቋችሁ እርግጠኛ ነኝና በዚሁ መልካም ሥራችሁ ቀጥሉ:: ቤተክርስቲያንን ለማሳወቅ የምታደርጉትን ሩጫ ቅዱሳን በጸሎታቸው እንዲያፋጥኑላችሁ የዘወትር ጸሎቴ ነው::

*እሸቱ ተክሌ*
*አዋሳ መምህራን ት/ኮሌጅ*

## ደግማችሁ ብታወጧቸው

ክርስቲያን ብዙ ሙገሳ አይሻምና በቀጥታ ወደመልእክቴ ልግባ:: መቼም ሐመር በተለይ ሰባክያነ ወንጌል በርከት ብለው በሌሉባቸው ቦታዎች ሰባኬ ወንጌል ናት:: ይኸውም እድሉ ገጥሚቸው ያገኟት በማንበብ ያላገኟት ደግሞ ባነበቧት ለመሰበክ ትሆናቸዋለች ማለቴ ነው:: እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ከሐመር 1ኛ ዓመት ቁጥር 1 ጀምሮ እስከ ሦስተኛ ዓመት የመጨረሻ ኅትመት ድረስ በብዛት በሰንበት ትምህርት ቤቶችም ሆነ በምእመናን እጅ አይገኙም:: እናንተ ጋር ግን ሊኖር ይችል ይሆናል:: ያ ደግሞ አሁን በተለይ በክፍላተ ሀገራት ካለው የሰባክያን እጥረት አንጻር ጥቅም አይኖረውም:: ስለዚህ ከላይ በጠቀስኩላችሁ ኅትመቶች በተለይ በትምህርተ ሃይ ማኖት ዓምድ የወጡትን ጽሑፎች አሁን በም ታሳትሟቸው መጽሔቶች በተከታታይ ብታ ወጧቸው መልካም ነው እላለሁ:: በተረፈ ሰላመ እግዚአብሔር አይለያችሁ::

*ሰሎሞን ተፈራ*
*ዝዋይ ሐመረ ኖኅ ቅ/ጊ/ገ/ሰንበት ት/ቤት*

ከአዘጋጁ

እንደአንተ ዓይነት መልእክት ከበርካታ አንባብያን ይደርሰናል:: ነገር ግን ይህ ጥያቄያችሁ የእኛም ሐሳብ ቢሆንም እስከ አሁን እንደጥያቄያችሁና እንደ ሐሳባችን ልንሠራ አልቻልንም:: ምክንያቱም ያለፈውን ደግመን እንጽፋለን ስንል አሁን ማለት ያለብንን ሳንል ልንቀር በመሆኑ ነው:: ምንም እንኳን አሁን ከምናወጣቸው ጽሑፎች ጋር በማጣቀሻነት እየተጠቀምንባቸው ቢሆንም እግዚአብሔር በፈቀደ ወደፊት ልናወጣቸው እንሞክራለን::

## ኅዳር የት ገባ?

የተከበራችሁ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች፤ባለፉት ተከታታይ እትሞቻችሁ ሐመር በሁለት ወር አንድ ጊዜ ትወጣ ነበር:: አሁን ግን ከመስከረም/ጥቅምት ለጥቆ የወጣው ታኅሳስ/ጥር ነው:: ኅዳርንስ የት ባላችሁት? በታይፕ ስህተት ወይስ እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ አደረሣችሁ ለማለት? ሁለተኛው ከሆነ መልካም እንኳን አብሮ አደረሰን:: የመጀመሪያው ከሆነ ግን ከሱ ጋር የፊደል መደራረብ፣የፊደሎች ግድፈት ስላለ በተቻላችሁ መጠን ለማስተካከል ሞክሩ::

*ዲ.አለባቸው ኪሮስ*
*ኢ.አ.ዩ /4 ኪሎ/*

ከአዘጋጁ:

እውነት ብለሃል:: የአሁኑ እትማችን ታኅሳስ/ጥር መባሉ በታይፕ ስህተት ሳይሆን አስበን ያደረግነው ነው:: ለምን ብትለን መጽሔታችን ስርጭቷ እስከ ባሕር ማዶ መሆኑን መቼም ሳትገነዘብ አትቀርም:: በመሆኑም ከዚህ ታትማ ባሕር ማዶ በተለይ ቀጥታ ግንኙነት ከሌለባቸው አገሮች እስከምትደርስ አንድ ወር ይወስዳል:: አንድ ወር ዘግይቶ የደረሣቸው ደንበኞቻችን ደግሞ መጽሔቱ በጣም የቆየ እየመሰላቸው ቅር ይሰኙብናል:: ምንም እንኳን የእግዚ አብሔር ቃል «ያለፈ ነው ባይባልም» በውጭ የሚኖሩ ምእመናን የሚሰማቸውን ስሜት እዚህም ወደ ጠረፍ የሚኖሩ ምእመናን ይጋሯቸዋልና ይህንን አደረግን:: የሚቀጥለው መጽሔታችን የካቲት/መጋቢት ይሆናል ማለት ነው::

## የእሣት አደጋ ማጥፊያም ሁኑ

ውድ ሐመሮች በሰላምና በመንፈሳዊ ትጋት እንድትኖሩ ዘወትር እጸልያለሁ:: መጽሔታችሁን በሚገባ አነባለሁ:: ወደ መልእክቴ ስገባም በጣና ሐይቅ ከሚገኙት ገዳማት ውስጥ አንዱ የአቡነ በትረ ማርያም ቤተክርስቲያን ነው:: ይሁንና ይህ ቤተክርስቲያን ከተገደመ ጀምሮ እድሳት ሳይደረግለት ቆይቶ በ1980 ዎቹ አጋማሽ ላይ ቤተመቅደሱ ብቻ እስከ መቅረት ደርሶ ነበር:: ነገር ግን በ1989 ዓ.ም በክርስቲያኖች ትጋት ታድሶ የነበረውን ክብር ይዞ ሳየው እጅግ ተደሰትኩኝ:: እናም ሐመሮች ይህ ቤተክርስቲያን ሊፈርስ ነው፤ያኛው ተቃጠለ ማለቱ ብቻ ሳይሆን ይህም ታደሰ፣ ያም ተሠራ ብላችሁ ክፉውን ዜና ሰምቶ ለሚቃጠለው ልባችን የእሣት አደጋ ማጥፊያ ብርጌድ ሁኑለት::

*ተፈሪ መኮንን*
*ከባሌ /ደሎ መና/*

## ማውጫ ብታዘጋጁ

ውድ የመጽሔታችን አዘጋጆች እንደ ምን አላችሁ? አዲሱ ጽ/ቤትስ ተስማማችሁ? ሐመሮች በመጽሔታችሁ የተለያዩ የቤተክርስቲያን ትምህርቶችን አስነብባችሁናል:: መጽሔቷ ባሏት ዓምዶች የወጡትን ልዩ ልዩ ጽሑፎች ምእመናን በተለይ ሰባክያነ ወንጌል እንደመረጃ ተጠቅመው ያገለግሉባቸውና ይገለገሉባቸው ዘንድ አጠቃላይ ማውጫ በአንዱ መጽሔት ላይ ብታወጡ ጥሩ ይመስለኛል:: ይህ ማውጫ ለሰባክያነ ወንጌል ከሚሰጠው ጥቅም ባሻገር ቀድሞ የመለሳችኋቸው ጥያቄዎች በድጋሚ ወደ እናንተ እንዳይላኩ ያደርጋል:: ስለዚህ ይህንን ጉዳይ አስባችሁበት ብትንቀሳቀሱ መልካም ነው እላለሁ:: በተረፈ እግዚአብሔር አምላካችን ይጠበቃችሁ::

*ሀብቴ /ከኮተቤ/ እና ተሾመ ታደሰ /ደሴ/*

## ስለ እሳቸውም ብትጽፉ

መጽሔታችሁን በተቻለ መጠን እከታተላለሁ:: በሕይወት ዘመናቸው መልካም ተግባር ፈጽመው ያለፉ ታላላቅ አባቶችን እየዘከሩ የሕይወት ታሪካቸውን ከተግባራቸው አዛምዶ ማቅረቡ እነሱን ከመዘከራችን በላይ ለአሁኑ ትውልድ መልካም ልምድ ሊሆን እንደሚችል አልጠራጠርም:: ስለዚህ በእናስተዋውቃችሁ ዓምድ ሥር የምታቀርቡትን የቅዱሳን የሕይወት ታሪክ ግፋበት:: እዚህ ላይ ላሳስባችሁ የምፈልገው ነገር ቢኖር በቅርቡ በመኪና አደጋ ሕይወታቸው ያለፈው የብፁዕ አቡነ ጐርጐርዮስ ስም ሲነሳ ሁሉም በኀዘን ያስታውሳቸዋል:: ነገር ግን ዝርዝር ታሪካቸውና ምግባራቸውን የሚገልጽልኝ አላገኘሁምና በሚቀጥለው እትማችሁ ስለ እሳቸው ብትጽፉ? አመሰግናለሁ::

*ጉልላት ግዛው*
*ከገርጂ*

ከአዘጋጁ

ስለሰጠኸን ገንቢ አስተያየት እናመሰግናለን:: ስለታላቁ የቤተክርስቲያን አባት ስለ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በስምዐ ጽድቅ 4ኛ ዓመት ቁጥር 6 ላይ አውጥተናል:: ካገኘህ ከዚያ አንብብ ካላገኘህ ደግሞ ወደ ቢሮአችን ብቅ በል::

## ራሳችንን ብንፈልግ

በ6ኛ ዓመት ቁጥር 6 እትማችሁ «ዓምደ ወራዙት» በሚለው ዓምድ ያወጣችሁት ጽሑፍ እጅግ ከፍተኛ ትምህርትን የሚሠጥ ነው:: ፈረንጆችን «የማምለክ» ሁኔታ ከወጣቱ ትውልድ ሕሊና መጥፋት አለበት:: በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ በአምላኩ የሚመካ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ችግሩ የሚቃለለው ብሎም የሚጠፋው በፈረንጆቹ ሳይሆን በአምላክ ጥበብ መሆኑን መገንዘብና ለዚህም አጥብቆ መጸለይ ይገባዋል:: ከጸሎቱም ጋር ኋላ ቀርነቱን አስወግዶ እሱ ወደ እነሱ ሳይሆን እነሱ ወደ እሱ እንዲያዩ መሥራት ይጠበቅበታል:: ለማንኛውም እናንተ በጅምራችሁ ቀጥሉበት::

*ብርሃኑ ውብነህ*
*አ/አ*
*ወልደ ኢየሱስ /አዋሳ/*
*የደማስቆ መንገደኞች*
*ይርጋለም*

## ደካማ ጐንም አለባችሁ

ሐመሮች ብዙ ጊዜ ከእናንተ የምናነበው ጠንካራ ጐናችሁን ነው። ይሁን እንጂ ደካማ ጐንም አለባችሁ። ለምሳሌ ሰውን ማበላለጥ ማለትም ለዶክተሮች፣ ለመምህራን፣ ሊያም የአዲስ አበባን ሰው ማስተናገድ የዘወትር ልምዳችሁ ነው። እንደዚሁም በሐመር ላይ የፊደል ግድፈትና የቃላት ስሕተት አለ። ለምሳሌ በ6ኛ ዓመት ቁጥር 6 እትም ላይ ጐልያድ ዳዊትን የገደለው በምንድነው? የሚል የተሳሳተ ታሪክ አቅርባችኋል። ስለዚህ ለወደፊቱ ጥንቃቄ አድርጉ። በተረፈ እግዚአብሔር ፍጻሜውን ያሳምርላችሁ።

*ሊቀ ዲያቆን ኪዳኑ ተካ*
*አ.አ*

ከአዘጋጁ

ውድ ወንድማችን በፊደልና በቃላት ግድፈት በኩል የሰጠኸውን አስተያየት ተቀብለናል። «ሰው ታበላልጣላችሁ» ላልከው ግን በማንኛውም ሁኔታ ሰው እንደማናበላልጥ ልንገልጽልህ እንወዳለን። በማዕረግ የጠቀስካቸውንና በአዲስ አበባ አሉ ያልካቸውንም ያቀረብናቸው አዲስ አበባ ስለሚኖሩ ወይም ዶክተርና መምህር ስለሆኑ አይደለም። በወቅቱ በሚተላለፈው መልእክት ላይ ትምህርት ይሰጣሉ በሚል ነው። ይህ ደግሞ መሆን ያለበትና ወደፊት የሚቀጥል ነው። ለምእመናን ትምህርት የሚሰጥበት ሁኔታ ካለ አቅማችን በፈቀደ መጠን የትም ድረስ በመሄድ ማንኛውንም ምእመን እናነጋግራለን-እናቀርባለን። አዲስ አበባ ላይ ያተኮርነው በወቅም ማነስና ብዙዎችም ባለሙያዎች ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የሚገኙት በዚሁ በመሆኑ ነው። በተሳትፎህ አትለየን።

## መድረኳን አስተዋውቁን

ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያናችን በክርስቶስ ደም ከተመሠረተች ወዲህ በመሰናክሎች መካከል እየተጓዘች አሁን ካለንበት ደረጃ ደርሳለች፤ ወደፊትም ትኖራለች። ታዲያ በተለይም ሐመር 6ኛ ዓመት ቁጥር 6 እትማችሁ ላይ በኢየሩሳሌም ስላለችው ቤተክርስቲያናችን ያቀረባችሁት ጽሑፍ የሃይማኖታችንን መሠረትና ታሪኳን እንዲሁም አመጣጧን ለመረዳት ያስችላል። ስለዚህ አሁንም በዝግጅቶቻችሁ ውስጥ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት በዓለም ዙሪያ በመዳሰስ በተለያዩ አገሮች ያላትን ታሪክ፣እንቅስቃሴ እንዲሁም ገዳማትንና አድባራትን ሰፋ ባለ ሁኔታ በማቅረብ ቤተክርስቲያናችን በዓለም መድረክ ያላትን የታሪክ እውቅና በማሳወቁ እንድትገፉ አደራ እላለሁ። በተረፈ ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲኖርበት ነውና እግዚአብሔር ይርዳችሁ።

*ተስፋዬ ወልዴ*
*ጂማ እርሻ ኮሌጅ*

## አስተማሪው እግዚአብሔር እንጂ...

በሐመር 6ኛ ዓመት ቁጥር 6 እትማችሁ ላይ «የአዘጋጅ ለውጥ» መደረጉን ተመልክቼ ትንሽ ተደናግጬ ነበር። ነገር ግን መጽሔቷን በሙሉ ሳያት እንደተለመደው ሆና አገኘኋት። በመሆኑም ከድንጋጤ ተረጋግቼ ይህን ሐሳብ ልሰነዝር ወደድኩ። መቼም ሰው የለመደው ነገር ሲቀርበት ትንሽ ለየት ያለ ስሜት እንደሚያድርበት እሙን ነው። ቢሆንም ይህንን ስሜት አስወግዶ መረጋጋት የራሱ ፈንታ ስለሆነ ማንን ወይም ምንን ነው ማየት ያለብኝ? ብሎ ራሱን ጠይቆ ከተረዳ በኋላ ዋናውን ቁምነገር ያገኘዋል።

እኛም አንባቢዎች ልናተኩርበት የሚገባን አንድ ነገር ቢኖር ምን ተጽፏል? ምን ዓይነት መልእክት አለ? የሚለውን ነው። ምክንያቱም ሁሉ በሁሉ ሆኖ የሚያስተምር፣በለገው እያደረ የሚመክር ይልቁንም ከሁሉ በላይ የምንከተለው እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ስላልሆነ ልናስተውል ይገባናል።

እናንተም አዲሶቹ አዘጋጆች እስከ ዛሬ ድረስ የማይጠገቡና የማይሰለቹ ዝግጅቶችን በመጽሔቱ እንዳገኘን ሁሉ ከአምላክ ጋር ሆናችሁ የበለጠ እንድትሠሩ ታላቅ ኃላፊነት ይጠበቅባችኋል። ወገባችሁንም በደንብ ታጥቃችሁ ተነሡ። ኃይልን ጥበብን ማስተዋልን የሚሰጥ አምላክ ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን።

*ሚሊዮን ደባባ*
*ንግድ ሥራ ኮሌጅ*

## የሚበጀኝን አግኝቻለሁ

ከመጽሔታችሁ ደንበኞች አንዱ ነኝ። እስከ አሁን መጽሔታችሁን በመከታተል ብቆይም አስተያየት በመስጠትም ሆነ በሌላ መንገድ ያደረግሁት ተሳትፎ አልነበረም። በቅርቡ በታተመው 6ኛ ዓመት ቁጥር 6 ላይ የማኅበሩ መልእክት ሥር ስለ ሰበካ ጉባኤ መጠናከር የተላለፈው መልእክት በአሁኑ ወቅት በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ ያለውን ችግር ለመፍታት ጠቃሚ አስተዋጽዖ አለው። ረክቼበታለሁም። በተለይ እኔ ባለሁበት አካባቢ በዓለ ጥምቀት በሚከበርበት ቦታ በርካታ ምእመናን እንዲያገኙት በመሆኑ ተደስቼበታለሁ። በመቀጠልም ከብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ስለ ቤተክርስቲያናችን ማንነት ወጣቶች ማድረግ ስለሚገባን ሁሉ ካስተላለፉት መልእክት የሚበጀኝን አግኝቻለሁና በዚሁ ቀጥሉ። የአባቶቻችን አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ብርታቱን ይስጣችሁ።

*ውብሸት ጌታቸው*
*ዲላ*

## አባቶችንና ምእመናንን

ባለፉት ሁለት ተከታታይ እትሞቻችሁ ከብፁዕ አቡነ ኤልያስና ከብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ጋር ያደረጋችሁት ቃለ ምልልስ ጠቃሚ ሆኖ አግኝተነዋል። ከሰፊ ትምህርታቸው፣ከረጅም ልምዳቸውና ከአገልግሎት ፍሬያቸው እንድንቋደስ ስላደረጋችሁን ተደስተናል። እንደልጅነታችን ብፁዓን አባቶቻችንን ማወቃችን ተገቢ በመሆኑ የከፈታችሁት ዓምድ መቀጠል አለበት። አባቶችንና ምእመናንን የበለጠ ለማቀራረብ የምታደርጉትን ጥረትም ከልብ እናደንቃለን።

ምእመናንን ከአባቶች ለመለየት የሚሯሯጡትን አንዳንድ ግለሰቦች አፋቸውን የምናዘጋበት መሣሪያችን ሆይልና የቃለ መጠይቅ ዓምዱ ሌሎች አባቶችንም እንደሚያቀርብልን ተስፋ እናደርጋለን።

*የትንበርክ ታሪኩ /ባሌ/*
*ብዙአየሁ ታምሩ /ደ/ጎንደር/*
*ደምስ ግርማ /አ.አ/*

## ድንግል ታስባቸው

ፊያሜታ ጋዜጣ እውነትነት የሌለው ወንጌል ይዞ የሚወጣው ለምንድነው? የጋዜጣው ዓላማስ ምንድነው? ተልእኮውስ? ይህንንም ልል የቻልኩት እንደአጋጣሚ ጋዜጣውን ከሰው ላይ ወስጄ በማነብበት ጊዜ የጌታችንና የእመቤታችንን ክብር የሚያቃልል ጽሑፍ ታትሞ በማግኘቴ ነው። ይህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምእመናንን ለማደናገር ሆን ተብሎ የተደረገ ሴራ በመሆኑ አልወደድኩትም። አባቶችሁ ከእንዲህ ዓይነቱ ድርጊት እንዲቆጠቡ ምክሩልኝ። እነሱንም ድንግል ታስባቸው።

*ምትኩ አብርድ*
*አሰበ ተፈሪ*

## መጽሔታችሁ ያደክማል

የሐመር መጽሔት ቋሚ አንባቢ ነኝና ባልጽፍም ዓምዶቿን ሁሉ ዐውቀዋለሁ። የቱ ከየቱ እንደሚቀድም እንኳን አሳማውም። የመጽሔቷን ይዘት ስቃኘውም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ለሚያነበው ሰው አድካሚ እየሆነ መጥቷል። «ከደብዳቤዎች፣ከአንባብያን...» ዓምዶች በስተቀርም የሚቀርቡት ጽሑፎች በጣም ረጃጅም፣ የማያቋርጡ ከመሆናቸውም በላይ በየገጹ የሚቀርበው ቀርጽ ዓይንን ያደክማል። ድሮ ድሮ በየገጹ የምታቀርቧቸው ግጥሞችም ቢሆኑ አሁን በጣም አንሰዋል። መልእክታቸውም ጠንካራ አይደለም። ስለዚህ በተወሰኑ ገጾች ርቀት ዕረፍት ማድረጊያ የሚሆኑ አጫጭር ነገሮችን የምታስገቡበት ዓምድ ቢኖራችሁ መልካም ነው።

ያለፈው እትማችሁ የሽፋን ገጽ ታም እንደሚያምር አልደብቃችሁም ያንን የመሰለ ቤተክርስቲያን ፎቶ አሳንሳችሁ ገጣጥሞ ለማንበብ የሚያስቸግር ሰላምታ በትልልቁ ማውጣታችሁ አሳዝኖኛል። እስኪ የድሮዎችን ሐመሮች ተመልከቷቸው። አደራ መሻሻል አለበትና አስቡበት። "ከፍትፍቱ ፊቱ" ይባል የለም? አበቃሁ።

*መታሰቢያ መስፍን*
*አ/አ*

## እንወያይበት

ባለፈው እትም ስለልመና መስፋፋትና ስለ ችግሩ አሳሳቢነት ያወጣችሁት ጽሑፍ የልቤን ስሜት ተጋርቷል። ልመና በጣም ከመስፋፋቱ የተነሣ ሕዝባችን በአብዛኛው ለማኝ እስከመሰል ድረስ መንገዱ ሁሉ በለማኞች ተሞልቷል። እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች መለመን በራሱ የሚያጸድቅ ሳይመስላቸው አይቀርም። ጤናና ጉልበት እያለ መለመን ኃጢአት መሆኑ እንዲሁም ለእንደዚህ ያለው የሚሰጠውም ከጥፋቱ ጋር የሚተባበር መሆኑን መግለጻችሁ አስደስቶኛል። በተለይ የፈረንጆች /የውጭ አገር ሰዎችን/ ልብስ ላይ እየተንጠለጠሉ የሚለምኑትን ሕጻናትና ወጣቶች ስመለከት ውስጤ ይቃጠላል። እባካችሁ አንድ ጊዜ አንስተናል ብላችሁ ሳትተውት ችግሩ እኔን ከሚገባው በላይ አሳስቦኛልና ትኩረት ሰጥተን ብንወያይበት መልካም ነው። በተረፈ ለወደፊቱም እንደዚህ ዓይነት ማኅበራዊ ችግሮችን ማንሣት እንዳትተው።

*ፍቅርት አየለ*
*አ/አ*

# መቅደሴን ፍሩ

ዘሌዋ.26÷2

*ቀሲስ ስንታየሁ አባተ*

ቤተመቅደስ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት፣ እርሱን የሚያምኑ ምእመናን ሥርዓተ አምልኮአቸውን የሚፈጽሙበት ፣የእግዚአብሔር ምሕረት፣ በረከት ለልጆቹ የሚታደልበት ቤት ነው::

ሰዎች ቤተመቅደስ ሠርተው ሥርዓት ባለው መንገድ ፈጣሪያቸውን እንዲያመሰግኑ ያዘዘ ያስተማረ ራሱ እግዚአብሔር ነው:: ሰማይዙፋኑ ፣ ምድር መረገጫው ስትሆን በዓለም ሁሉ የመላ እግዚአብሔር ለርሱ የሚገዙ ለት ልጆቹን ሊጠብቃቸው፣ ሊባርካቸው ስለወደደ «በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ» ብሎ አዘዘ /ዘጸ.25÷8/

እግዚአብሔር በወደደውና ባዘዘው መሠረት በየዘመኑ የነበሩ ቅዱሳን ለእግዚአብሔር ለስሙ ማደሪያ የሚሆን ደብተራ ኦሪት፣ መቅደሰ ኦሪት እና ቤተክርስቲያንን ሠርተው ሥርዓተ አምልኮአቸውን ሲፈጽሙ ኖረዋል:: ልዑል እግዚአብሔርም ማደርያ ይሆነው ዘንድ ባሠራው መቅደስ ክብሩን እየገለጠ ቤቱን ከመቀደሱም በላይ በንጽሕና ፣በትኅትና ሆነው በማደሪያው ያገለግሉና ይገለገሉ ለነበሩት በረከትና ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል:: ለአብነትም ያህል መገናኛ ድንኳኑን እግዚአብሔር እንዴት እንደቀደሰው ሊቀነቢያት ሙሴ «ማደርያውም በተተከለ ቀን ደመናው የምስክሩን ድንኳን ሸፈነው፤ ከማታም ጀምሮ እስከ ጥዋት ድረስ በማደሪያው ላይ እንደ እሳት ይመስል ነበር:: እንዲሁ ሁል ጊዜ ነበር፤ በቀን ደመና በሌሊትም የእሳት አምሳል ይሸፍነው ነበር» ብሎ ገልጧል:: /ዘኁ.9÷15–17/

እግዚአብሔር በበረከት፣ በምሕረትና በቸርነት ተገልጦ የሕዝቡን በደል ይቅር ወደሚልበት ወደቤተመቅደስ ሕዝቡ ሲመጡም ሊኖራቸው የሚገባውን አቀራረብ «መቅደሴን ፍሩ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ» በማለት አስጠንቅቋል::

በሐዲስ ኪዳን ለምንገኝ ምእመናንም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ አምላክነት ያመንን ቃሉን የምንማርበት፣ጸሎት የምንጸልይበት፣ሀብተ ወልድ ስመ ክርስትና የምናገኝበት፣ ሥጋውን በልተን ደሙን ጠጥተን ከርሱ ጋር የምንዋሐድበትን ቤተክርስቲያን በንዝሐተ ደሙ /በደሙ መረጨት/ ቀድሶ ሰጥቶናል:: በመዋዕለ ስብከቱም በአሪቱ ለንጉሥ ሰሎሞን «....ጸሎትህን ሰምቻለሁ፣ ይህንንም ሥፍራ ለራሴ ለመሥዋዕት ቤት መርጫለሁ፤ ...አሁንም በዚህ ሥፍራ ለሚጸለይ ጸሎት ዓይኖቼ ይገለጣሉ፣ ጆሮዎቼም ያዳምጣሉ:: አሁንም ስሜ ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለሁ:: ዓይኖቼና ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ» ብሎ ማደርያው ይሆን ዘንድ የቀደሰውን ቤት የማይገባ ሥራ ሲሠሩበት ባየ ሰዓት ተቆጣ:: «ወደ መቅደስም ገብቶ በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ያወጣ ጀመር:: የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጭዎችንም ወንበሮች ገለበጠ:: ዕቃም ተሸክሞ ማንም በመቅደስ ሊያልፍ አልፈቀደም:: አስተማራቸውም«ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ የተጻፈ አይደለምን? እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት» አላቸው፤ /ማር.11÷15–18/

ከጌታችን ተግሳፅ የምንማረው ነገር አለ:: አስቀድሞ «መቅደሴን ፍሩ» ብሎ ያዘዘንን ወደጎን ትተን መቅደሱን የወሬ፣የሐሜት፣ የትዕቢት፣የገበያ ቦታ ያደረግነው እንደሆነሙ ዕደ–መአቱን ያነሣል፣ በረከቱን ይነሣል:: እንዳያዩ ዓይኖቹን እንዳይሰማ ጆሮዎቹን ይመልሳል:: ስለዚህ እግዚአብሔር ማደርያው ወደአደረገው መቅደስ ስንሄድ እግዚአብሔር በፍቅር፣ በምሕረት እንዲቀበለን ወደመቅደሱ /ቤተክርስቲያን/ መሄዳችን ለምን እንደሆነ ማወቅ ይገባል::

አንድ ምእመን ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄደው ነገረ–ሃይማኖቱን ሊማር፣ ወደፈጣሪው ሊጸልይ፣ስለኃጢአቱ ንስሐ ሊገባ፣ቅዱስ ቁርባን ሊቀበል፣በክብረ በዓላት ደግሞ ማኅሌት ሊቆም፣...ነው:: ይህን ለመሰለውና ፈቃደ እግዚአብሔር ለሆነው ሁሉ ከሥጋ ፈቃዳት /ገላ.5÷19–22/ ተከልክለን በቤተክርስቲያን ብንገኝ እግዚአብሔር ለሰ ዎች የገባውን ቃል ኪዳን ሁሉ ይፈጽም ልናል:: /ዘሌዋ. 26÷11–13/ ጌታችን «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ፤» ብሎ ያስተ ማረውም ስሙን አክብረው ስለ እግዚአብሔር ብለው መመስገኛው በሆነች በቤተክርስቲያን በፍቅር ለመልካም ሥራ /ዓላማ/ የሚሰበሰቡትን የሚመለከት ነው:: /ማቴ.18÷20/

ምንም እንኳን የቤተመቅደስ ክብር ከላይ ለመግለጥ የሞከርነውን ቢመስልም ፍሩ እንዳልተባለ የሚዳፈሩ፣ አክብሩ የተባለውን ሊያዋርዱ የሚሹ ፣በቅድስና ቅረቡ የተባለውን ትተው በንስሐ ባልታደሰ ሕይወት ሊያረክሱ የሚፈልጉ አንዳንድ የውስጥ አላዋቀዎች ፣የውጪ መናፍቃን አሉ:: በመሆኑም ሰውና መላእክት በአንድነት በሚያመስግኑበት በቤተክርስቲያን ውስጥ ከመቅደስ እስከ ቅኔ ማኅሌት፣ ከካህኑ እስከም እመኑ የግል ወሬ የሚያወሩ፣ ባልንጀራቸውን የሚያሙ፣ ባላዋቂው የሚስቁ የሚያሽሟጥጡ፣ የታወቀ ምክንያት /በሽታ፣እርጅና/ ሳይኖርባቸው በቅዳሴና በጸሎት ሰዓት የሚቀመጡ፣የሚተኙ በየአድባራቱ መበራከት ጀምረዋል:: ከመቅደሱ ውጪ በቅጽር ግቢውም ውስጥ የሚደረጉ አንዳንድ ስህተቶች አሉ:: ለምሳሌ አንዳንድ ጓደኛሞች ለመማር ያይደለ ለመገናኘት ይቃጠሩባታል:: የባሰባቸውም አጸዷን ከለላ አድርገው ይዳሩባታል፣ድግስ ደግሰው ከደጇ ሰላሟ ውጭ ይበሉባታል ይጠጡባታል፣እዚያው በልተው በቅጥሯ ዙርያ ይጸዳዱባታል:: ሌላም አለ::

በቤተክርስቲያን የተጣላን ማስታረቅ ተገቢ ነው:: ነገር ግን ባልናሚስት የሚያፋቱባት፣ፍርድን ለወገኔ፣ ለሀገሬ ለወንዜ ልጅ በማለት የሚያዛንፉባት ከመኖራቸውም በላይ በሽምግልናው ወቅት ከመጠን በላይ በሆነ ክርክርና ጭቅጭቅ በግቢው ውስጥ የሚጸልዩትን የሚረብሹም ቀላል አይደሉም:: እግዚአብሔር ግን ያዘዘን እርሱ ያከበረውን፣ የቀደሰውን እንድናከብር «መቅደሴን ፍሩ እኔ እግዚአብሔር ነኝ::» በማለት ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ የመቅደሱ ክብር ከልቡናቸው ተሠውሮባቸው እግዚአብሔር ሥሩ ብሎ ያሠራውን፣ ያከበረውን፣ መቅደስ የሚሰድቡ መናፍቃን ሞልተዋል:: ክህደታቸውን ለማስፋት ቤተመቅደስ እንደማያስፈልግና ሰውነታቸው የእግዚአብሔር መቅደስ እንደሆነ በማስተማር ሕዝቡን ያሰናክላሉ:: በእርግጥ በቀና ሃይማኖት፣ በመ ልካም ምግባር ያለ ምእመን ሰውነት የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቢሆንም ሥርዓተ አምልኮአችንን የምንፈጽም በትን መቅደስ ጌታችን ባርኮ ቀድሶ ሰጥቶናል::

በመጀመሪያ ጌታችን መምጣቱ በአሪቱ የነበረውን ሊሽር ሳይሆን ሊያድስ፣ ፍጹም ሊያደርገው መሆኑን «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ፤ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም» ማቴ.5÷17 ብሎ አስተማረን:: በትምህርቱም መሠረት የገበያ ቦታ ሆኖ የነበረውን ቤተመቅደስ አጽድቶ፣ለቤቱ የማይገቡ ትን አውጥቶ «ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች» በማለት ክብሩን ገለጠ:: ቀድሞ በደመና ዓምድ ይገለጥበት የነበረው

በሐዲስ ኪዳን ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ እየተሰዋበት ይኖራል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰድቡት፣ ሲመቱት፣ አልተናገረም። ባርኮ ቀድሶ ማደርያው ያደረጋት ቤተመቅደስ በተደፈረች ጊዜ ግን ጅራፍ ገምዶ የደፈሩትን ከመቅደሱ አስወጣቸው። ዛሬም በድፍረት፣ በመናቅ፣ ወዘተ... ቤተመቅደስን የሚመለከቱ በንስሐ ካልተመለሱ የእግዚአብሔር የቁጣ ጅራፍ ይዘረጋባቸዋል። /ዮሐ.2÷13–18/ እነዚህ መናፍቃ «እግዚአብሔርንም ለመሳደብ፣ስሙንና ማደርያውንም /ቤተ መቅደስ እመቤታችንን፣ ቅዱሳንን ሰማይን/ በሰማይም የሚያድሩቱን /መላእክትን/ ሊሳደብ አፉን ከፈተ» ተብሎ ለተገለፀው ቋ መንገድ ጠራጊዎች ናቸው። /ራዕ13÷6/

ዛሬ እንደምናየው ሁሉ በአሪቱም «መቅደሴን ፍሩ» ያለውን ቃ እግዚአብሔር ተላልፈው በመቅደሱ መሥራት የማይገባቸውን በመሥራታ ቸው የተቀሰፉ ነበሩ፡ ናዳብና አብዩድ የተባሉት የአሮን ልጆች ለዕጣኑ ማጠኛ የሚያገለግለውን እሳት ከመንደር አምጥተው በጥና በመጨመራቸው እሳት ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ በላቸው። /ዘሌዋ.10÷1–11/ ዛሬም ለማዕጠንት የሚሆነውን ፍም ማፋም እያቃቸው ጧፍ አቀጣጥለው የሚያጥኑ አሉ። በመሆኑም ዕጣኑ በትክክል ጢሶ የተፈለገውን አገልግሎት አይፈጽምም።

የቆሬ ልጆች እሥራኤላውያን መሆናቸውን ብቻ ተመልክተው እኛም ክህነት ይገባናል፤እንደ አሮን ጥናውን ይዘን የዕጣን መስዋዕት /ማዕጠንት/ ማቅረብ አለብን ብለው ሙሴን በመገዳደራቸው የቆሙባት መሬት አፏን ከፍታ ከነሕይወታቸው ዋጠቻቸው። /ዘኁል 16÷1–35/ ይህም ትዕቢት ያመጣው መዘዝ ነው። ባለንበትም ዘመን ክህነትን በገንዘብ፣በወላጆቻቸው ስመጥርነት የካህናት ልጆች ብቻ በመሆናቸው ሳይማሩ ገንዘብ ሊያደርጉ የሚሹ አንዳንዶች አሉ።«ክህነት ለሴቶች ይገባል»ብለው በአሜሪካና በአውሮፓ የሚያውኩ በደቂቀ ቆሬ መንገድ የተጓዙ ናቸው። በሀገራችንም በቤተ ክርስቲያናችን ከድርሻቸው አልፈው በትዕቢት አለያም ባለማወቅ በተለይ በቅዳሴ ሰዓት ከካህናት ጋር /ዝግ ባለ ድምፅ/«አሐዱ»የሚሉ ከዲያቆናት ጋር «ተንሥኡ»ብለው የሚያውጁ ብቅ ማለት ጀምረዋል።

እነኚህ ብቻ አይደሉም። የካህኑ የዔሊ ልጆች አባታቸው በመሸምገሉ ወደመገ ናኛው ድንኳን ሕዝቡ የሚያመጣውን መስዋዕት እንደፈለጉ ለግል ጥቅማቸው ከማዋላቸውም በላይ በመገናኛ ድንኳኑ ከሚያገለግሉ ሴቶች ጋር ያውም በድንኳን ደጅ /በር/ በሥጋ ፈቃድ ወደቁ። በዚህም እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሁለቱ የዔሊ ልጆች እንዲሞቱ፣ታቦተ ጽዮን እንድትማረክ ዔሊ እንዲሞት አደረገ። /1ሳሙ.2÷12–34 ፣3÷12–14/ ዛሬስ? ባላቸው የተለየ ቀረቤታ ቤተመቅደሱንና የቤተመቅደሱን ንዋያተ ቅድሳት እንደግል ጥቅማቸው የሚጠቀሙ፣ በቤተክርስቲያን ቅጽረ ግቢ ሊጸልዩ፣ ከኃጢአታቸው ማሠርያ ተፈትተው የከበደባቸውን የኃጢአት ሸክም ሊያራግፉ የሚመጡ ምእመናንን በዝሙት የሚያሰነካክሉ... ከጧፍ ኩስታሪ እስከ ጽላት የሚሠርቁ ፈሪሃ እግዚአብሔር ከልባቸው የራቀ እየታዩ መጥተዋል።

ቤተመቅደስን መድፈር፣ማቋል ያከበረውን እግዚአብሔርን መዳፈር ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ትሑታንን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፣ የታበዩትን የሚያዋርድ ለእያንዳንዱ ዋጋውን እንደ ሥራው የሚከፍል፣ሁሉ /ትሑታን፣ ትዕቢተኞች/ በእጁ የተያዙ ናቸው። ስለ ዚህ እግዚአብሔር ባዘዘን መሠረት በፍቅር፣ በትኅትና ሆነን መቅደሱን በውስጥም በውጪም እናክብር።

ቅዱስ ዳዊት «አቤቱ እስከረጅም ዘመን ድረስ ለቤትህ ቅድስና ይገባል » በማለት እንደተናገረን ወደቤተ መቅደስ /ቤተክርስቲያን/ ስንሄድ ቅድስናን ገንዘብ እናድርግ። /መዝ.92÷5/ ምክንያቱም ቤተመቅደሱ ቅዱስ፣ በውስጡም የሚገለጠው የእግዚአብሔር ሥራ ድንቅ ነውና። /መዝ. 64÷5/ ወደዚህ የእግዚአብሔር ኃይልና ክብር ወደሚታይበት ወደ ቤተመቅደስ /መዝ.62÷2/ ስንገባ ንጉሥ ሰሎሞን «ወደ እግዚአብሔር ቤት በገባህ ጊዜ እግርህን ጠብቅ» እንዳለን በቤተክርስቲያን ውስጥ ከመሯሯጥ፣በእግረ ልቡናችን የሥጋን ፈቃድ ወደማሰብ ከመሄድ እንታቀብ።

እንዲሁም ቅዱሳን አበው «ማንም በቤተክርስቲያን ውስጥ ፈጽሞ አይናገር /በቤተክርስቲያን ውስጥ መነገር የሌለበትንና ረብ የሌለውን የሥጋን ሃሳብ/ ቤተእግዚአብሔር የነገር ቦታ አይደለችምና ከፍርሃት ጋር የጸሎት ቦታ ነው እንጂ በቤተክርስቲያን የሚናገር /ዋዛ ፈዛዛን፣ ሐሜትና ስድብን/ ሰው ይውጣ። በዚያን ጊዜ ሥጋውንና ደሙን አይቀበል » ብለው ሥርዓት የሠሩት በእምነት የወለዱን ልጆቻቸው መቅዳሴን ፍሩ ያለውን ትእዛዝ ተላልፈን በነፍስ በሥጋ እንዳንጎዳ ነው። /ፍት.ነገ.12÷ 476/

ቅድስናና ግርማ /መፈራት/ ወደመላበት ወደ ቤተክርስቲያን ለመቀደስም ሆነ ለማስቀደስ፣ ማኅሌት ለመቆም፣ ኪዳን ለማድረስ፣ለመማርም ሆነ ለማስተማር ስንሄድ በሩ ክፍት ስለሆነ ዘው ብለን መግባት፣በመንበሩም ፊት ስንቆም በትዕቢት መሆን የለበትም። ለአንድ አፍታ ወደ ልቡናችን ተመልሰን «ወደ ቅዱስ መቅደስህ መግባቴ የድፍረት አይሁ ንብኝ በቸርነትህ ነው እንጂ። ቤትህን በሚጠብቁ የወገኖችህን ምሥጋናና ልመና በሚያሣርጉ መላእክ ትህ እጅ በኃጢአቴ ከመቀሰፍ ሰውረኝ።» ልንል ያስፈልጋል።

ከዚህ በተጨማሪም በካህኑ በዔሊ ላይ የተፈጸመውን ልብ ማለት ተገቢ ነው። ዔሊ ልጆቹ በቤተመቅደሱና በሕዝበ እሥራኤል ላይ የሠሩትን ሥራ ያደረጉትን ግፍ ሠምቷል፤ አይቷል። ሰምቶ ግን የሚጠበቀውን ያህል ልጆቹን አልገሠጸም፤ ልጆቹን ፈርቷልና። ከእግዚአብሔር ፍቅር የልጆቹ ፍቅር በለጠበት። በዚህም የተነሣ «የዔሊ ቤት ኃጢአት በመሥዋዕትና በቁርባን ለዘላለም እንዳይሠረይለት ለዔሊ ቤት ምያለሁ» /1ሳሙ.3÷14/። ባለንበትም ዘመን መናፍቃ የበግ ለምድ ለብሰው ወደ ቤተክርስቲያን ሰርገው ከገቡ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በድፍረት የነቀፌታ ድምፅ ሲያሰሙ፣የክህደት መርዛቸውን ሲረጩ፡ ምእመናንን ከቤተክርስቲያን ሲያስኮበልሉ እያየን ሥጋዊ ጥቅም እንዳቀርብን፣ዝምድና እንዳይናጋብን መከራ እንዳያገኘን ፈርተን እያየን እንዳላየን የምንሆን ከሆነ፣በቤቱ እንድናገለግል ሥልጣን ከሰጠን ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን በመፍራታችን የዔሊ ዕጣ ፈንታ አይቀርልንም።

ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችን ባዘጋጀልን ሰማያዊት መቅደሱ ከቅዱሳን ጋር ለዘላለም እያመሰገንነው እንድንኖር ዛሬ በምድር የተሰጠችንን ቤተመቅደስ ስናከብር፣ ወደርሷም ስንገባ «እመቦ ነኪር እምትእዛዙ ለኢየሱስ ይትከላዕ...ነጽሩ ነፍስክሙ፣ ወአንጽሑ ነፍስተክሙ፤ ጌታ ካዘዘው ትእዛዝ የወጣ ቢኖር ይከልክል። ...ሰውነታችሁን መርምሩ መርምራችሁ፡ ከኃጢአት ንጹሕ አድርጉ» የተባለውን ቋ ልብ እንበል። /ቅዳሴ እግዚእ/ ያከበሩትን የሚያከብር እግዚአብሔር መቅደሱን ለማክበር ያበቃ ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን። አሜን።

♦ ♦ ♦ •

## አዳም ከነዘሩ

ቅዱሟ ተዋሕዶ ቃለ አብ ከሥጋ
መርገምን አጥፍቶ አለበሰን ጸጋ
ተፈሥሒ ያለው ገብርኤል በብሥራቱ
ትወልጃለሽ መድኅን ነበረ መልእክቱ
ቤዛ እንድትሆኚው ለአዳም ዘር በሙሉ
አፀናሽ ፈጣሪ ጠበቀሽ በቃሉ
ብትወልጂ መድኃኒት በዘጠኝ ወራት
አዳም ከነዘሩ ወጣ ከእስር ቤት።

ሙሉ ወርቅ ስለሺ
ደብረ ብርሃን ቴሌ

# እነኋት እናትህ... እነሆ ልጅሽ

ዮሐ 19÷26–27

ከባስልዮስ ዘቂሣርያ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ የተናገራቸውን ቃላት የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ሰባቱ አጽርሐ መስቀል በማለት ይጠሩ ዋቸዋል:: እነዚህም

1. *አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው*
2. *ዛሬ ከኔ ጋር በገነት ትሆናለህ*
3. *እነኋት እናትህ*
4. *አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ*
5. *ተጠማሁ*
6. *አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ*
7. *ተፈጸመ*

በጌታችን እግረ መስቀል ጌታችንን እጅግ የሚወዱ ሁለት ሰዎች ቆመው ነበር:: አምላክን በማኅፀንዋ የተሸከመች፣ከሄሮድስ ፊት ሸሽታ ለልጇ ስትል የተንከራተተች፣ የተሰደደች፣ ዛሬም በልጅዋ መከራ እጅግ አዝና የቆመች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ጌታን እጅግ በመውደዱ ዕድሜውን በዕንባ የፈጸመው ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ፣ ዮሐንስ ቁጽረ ገጽ ብዙዎች ከአይሁድ የሚደርስባቸውን መከራ ፈርተው ሲሸሹ እስከ መጨ ረሻው ጸንቶ መከራውን ታግሶ የተገኘ ብቸኛው ሐዋርያ::

እሳተ መለኮትን በማኅፀንዋ ለተሸከመች እናቱ ነገረ መለኮትን አምልቶ አስፍቶ የጻፈውን ሐዋርያ ልጇ ይሆን ዘንድ ሰጣት:: ነገረ መለኮትን አምልቶ አስፍቶ ለጻፈው ሐዋርያም እሳተ መለኮትን የተሸከመች ድንግል እናቱ ትሆነው ዘንድ ተሰጠችው::

የእግዚአብሔር ጥበቡ ምን ይረቅ፣ ምንስ ይደንቅ:: ነገረ መለኮት የገባቸው ሰዎች ነገረ ማርያም መልቶ ጐልቶ ይረዳቸዋል:: ይገለጥላቸዋል:: ይሰጣቸዋልም:: እነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣እነ ቅዱስ ቄርሎስ፣እነ አባ ኤፍሬም ሶርያዊ፣እነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣እነ ቅዱስ ያሬድ ነገረ መለኮት ተገልጦላቸው አምልተው አስፍተው አጉልተው የጻፉትን ያህል ነገረ ማርያም ተጨም ሮላቸው ፈትፍተው ተንትነው አስረድተዋል::

በዚህ ዓለም በሥጋ ሲገለጥ መጀመሪያ ያየው እርሷን ነበር– እናቱን:: ተፈጸመ ብሎ ሥራውን ሲፈጽምም ያየው እርሷን ነው እናቱን:: የእግዚአብሔር ጥበቡ ምን ይደንቅ::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ሳለ ለሁለት ሰዎች ስጦታ ሰጥቷል:: ለፈያታዊ ዘየማን ገነትን /ለሰው ልጆች ምሕረትን/ ለቅዱስ ዮሐንስ እመቤታችንን /ለእመቤታችን ቅዱስ ዮሐንስን/:: ፈያታዊ ዘየማን ገነትን ያገኘው ጠይቆ ነው:: «ጌታ ሆይ በመንግሥትህ አስበኝ» ብሎ:: እመቤታችን ግን አልጠየቀችም፣ነገር ግን ልጅዋ ወዳጅዋ ምን እንደሚያስፈልጋት ዐወቀ:: የቃናው ተአምር የሚያጠራጥራችሁ ወገኖች ሆይ ይህንን ድንቅ ምሥጢር እዩ:: እንኳንስ «የወይን ጠጅ አልቆባቸዋል» ብላ ለምና ቀርቶ ሳትለምን እንዲደረግላት ልጇ መስክሯልና:: ደግሞም የእናቱን ልመና በሰሙም በወርቁም ሲመልስላት ተመልከቱ፣ በጊዜው የሚያልቀውን ወይን ሰጥቶላታል:: «ጊዜዬ አልደረ ሰም» ብሎ የተናገረለት ጊዜው ሲደርስ ደግሞ አማናዊውን ወይን በቀራንዮ አደባባይ ሰጥቶላታል:: ኑ ይህንን ድንቅ እዩ፣ስለተገለጠልን ምሥጢርም ምሥጋና አቅርቡ::

«ለምኑ ይሰጣችኋል፣ ፈልጉ ታገኛላችሁ» ማቴ 6÷7 የሚለው ለዓለም ሁሉ የተሰጠ ነው:: እንዴት ይኼ ይደንቀናል? ፈያታዊ ዘየማን 5500 ዓመት የተዘጋች ገነትን ለምኖ ሲያገኝ እመቤታችን ያልሞላውን ወይን ጠጅ ይሞላ ዘንድ ለምና ታጣለች? ፈያታዊ ዘየማን ለራሱ ለምኖ ሲያገኝ እመቤታችን ለተቸገሩ ለተጨነቁ ለምና ታጣለች?

እመቤታችን በእግረ መስቀሉ ነበረች:: አንዳች ግን አልተናገረችም:: ዓለም በመዳኑ ተደስታለች፣በልጅዋ ስቃይ ግን አዝናለች ፤ ልጅዋ ሉቃስ በወንጌሉ «ማርያም ግን ይህንን ሁሉ ነገር በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር» ሉቃ 2÷20–51 በማለት እንደተናገረላት በዝምታ ችላ ቆመች እንጂ የልቅሶ ድምጽ አላሰማችም:: «በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል» እንዳላት ሉቃ 2÷35 አረጋዊው ስምዖን፣ ከማንም በላይ አዝናለች ግን ዝም አለች:: አርምሞ ትዕግሥት ጠባይዋ ነውና::

ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ ጌታችንን እጅግ ይወደው ነበር:: ጌታችንም የዮሐንስን ልብ ተቀብሎ ለእመቤታችን ሰጣት:: ጌታን ብንወደው ኖሮ የእመቤታችን በሆንን ነበር:: እስከመጨረሻው የጸና እርሱ ይድናል:: ማቴ 24÷13:: ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ እስከመጨረሻው ጸና:: የመዳኑ ምልክት የሆነችውን ድንግልንም አገኘ::

ድኅነትን ፈልገው ይቅበዘበዙ ለነበሩት እሥራኤላውያን «ጌታ ራሱ ምልክትን ይሰጣችኋል፤እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች. ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች» /ኢሳ 7÷14/ በማለት ትንቢትን የተናገርክ ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ ሆይ በረከትህ ይደርብን:: እስከመጨረሻው ለሚጸኑ የድኅነታቸው ምልክት እመቤታችን መሆንዋን አይተናልና:: የሰው ልጆች እናት አልባ ሆነው ይኖሩ ነበር:: ሔዋንን እናታችን ማለትንም ትተው ነበር:: ሔዋን ማለት የሕያዋን ሁሉ እናት ማለት ነው:: ነገር ግን እንደስሟ አልሆነችልንም፤የሙታን እናት ሆነች:: የሰው ልጅ ሁሉ ሞት ባንቺ መጣ እያለ ይወቅሳትም ነበር:: አሁን ግን የሰው ልጅ እናትን አገኘ፣ የሕያዋን እናት፣ የሕያዋን ነቢያት፣የሕያዋን አበው፣የሕያዋን ሐዋርያት ፣የሕያዋን ሰማዕታት፣የሕያዋን ጻድቃን፣ የሕያዋን ምእመናን እናት– እመቤታች ንን::

እመቤታችን ጸጋችን ናት፣ ካሣ የተሰጠችን:: ለፈያታዊ ዘየማን ገነትን ሲሰጥ ለርሱ ብቻ አይደለም በቀኝ ለሚቆሙ ጻድቃን ሁሉ እንጂ:: ለቅዱስ ዮሐንስ እመቤታችንን ሲሰጥ ለርሱ ብቻ አይደለም፤እርሱን ለሚወዱ ክርስቲያኖች ሁሉ እንጂ:: ለዮሐንስ የተገለጠ ወንጌል ለዓለም ሁሉ እንደሆነ ለዮሐንስ የተሰጠች እመቤታችንም የተሰጠችው ለዓለም ሁሉ ነው:: ደቀ መዝሙሩም ወደ ቤቱ ወሰዳት–ሊያስጠጋት ነውን? አይደለም::

ኤልያስ ወደ ሰራፕታዋ መበለት ቤት ገባ:: የተጠቀመ ማነው? «ዱቄቱ ከማድጋው አልተጨረሰም፣ ዘይቱም አላለቀም» 1ነገ 17÷16 ይህ ቃል የሆነለት ለማን ነው? «በማድጋው ካለው ከእፍኝ ዱቄት በማሠሮም ካለው ጥቂት ዘይት በቀር እንጀራ የለኝም፣ እነሆም ገብቼ ለእኔና ለልጄ እጋግረው ዘንድ በልተነውም እንሞት ዘንድ እንጨት እሰበስባለሁ» ላለችው መበለት አይደለምን? የእግዚአብሔር ታቦት ከቤትህ ያደረ አቢዳራ ሆይ እባክህ ተነሥተህ ንገረን፤ታቦተ እግዚአብሔር በቤትህ በማደርዋ ተጠቀመች ወይስ አንተ በማሳደርህ ተጠቀምክ? «እግዚአብሔር የአቢዳራ ቤቱን ሁሉ ባረከ» 2ሳሙ 6÷11 የተባለ ለአንተ አይደለምን?

አማናዊቷ ታቦት እመቤታችን ወደ አቢዳራ ዮሐንስ ቤት ሄደች፤ትባርከው ቤቱንም ትባርክለት ዘንድ:: እስከ ዕለተ እረፍቷ በቤቱ ኖረችለት:: ማቴዎስ ወንጌ ላዊ ቅዱስ ዮሴፍን «እጮኛው ማርያምን ወሰደ» ማቴ 1÷24 ሲል የተናገረውም ለዚህ ነው:: «ወሰደ» ና «ወሰደ» በትርጉም ይስማማሉ::

የታደሉት በቤታቸው እመቤታችንን ያስተናግዳሉ:: ሥዕሏን በክብር ያኖራሉ:: ያልታደሉት ደግሞ እንደ አካን የሞታቸው መንሥኤ የሚሆን እርም ያስቀምጣሉ አቴቴውን፣ጨሌውን...እናታችን ሆይ እንደ አቢዳራ ቤት ቤታችንን ኑሮአችንን ባርኪ:: አሜን::

☩☩☩

# «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ»

ዘሌ. 19÷18

## አሥረኛው ትእዛዝ

(የመጨረሻ ክፍል)

ከዲ.እሸቱ ታደሰ

ስለ እግዚአብሔር ሕግ መጻፍ ስንጀምር እንደተገለጠው ይህ በዘሌ.19÷18 የተጻፈው «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» የተሰኘ ትእዛዝ በዘጸ.20÷15 ከተዘረዘሩት ጋር ተደምሮ ከአሠርቱ ትእዛዛት አንዱ ነው:: ይህን ትእዛዝ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ትእዛዛት በተናገረበት አንቀጽ ሕግ ሁሉ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ፣ በፍጹም ሀሳብ፣በፍጹም ነፍስም በመውደድና ባልንጀራን እንደ ራስ አድርጎ በማፍቀር የሚጠቃለል መሆኑን፤ ቀዳሚው እግዚአብሔርን መውደድ ሁለተኛውም ባልንጀራን ማፍቀር መሆኑን አስተምሮናል::

ይህን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት መሠረት በማድረግም ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን አሠርቱን ትእዛዛት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች በመፈረጅ የመጀመሪያውን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት /ፍቅረ እግዚአብሔር/ ሁለተኛውን በሰውና በሰው መካከል ያለውን ግንኙነት /ፍቅረ ቢጽ/ ብለውታል:: ስለሆነም በቤተክርስቲያናችን ትምህርት መሠረት አሥረኛው ትእዛዝ «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» የሚለው ነው::

በብሉይ ኪዳን ሰዎች ዘንድ «ባልንጀራ» የሚለው ቃል በቅርብ የሚኖር እሥራኤላዊን ብቻ የሚያመለክት ፍቺ ተሰጥቶት ነበር:: «ባልንጀ ራህን እንደራስህ ውደድ» በማለት የተሰጠው ትእዛዝም በመልካም ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ወዳጅነትን ብቻ የሚያመለክትና አብረው የሚኖሩ በንጹሕ ፍቅር እንዲኖሩ የማስቻል ዓላማ እንዳለው ይታሰብ ነበር:: ይሁን እንጂ «ባልንጀራ» የሚለው ቃል ሰፋ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን:: በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ለዓለም ሁሉ ማለትም ለደቂቀአዳም ድኅነት በመሆኑና ይህ ቤዛነትም ሕዝብንና አሕዛብን አንድ ያደረገ አምላካዊ ስጦታ ስለ ሆነ፤ ባልንጀራ የሚለው ቃል ፍቺ በክርስቶስ አንድ አካል የሆኑትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው:: በዚህ ትርጉም መሠረት ባልንጀራን መውደድ ማለት በሥላሴ አርአያ የተፈጠረ ሰውን ሁሉ በሰውነቱ መውደድ ሆኖ እናገኘዋለን:: ማቴ.5÷42–48::

እያንዳንዱ ክርስቲያን ባልንጀራውን መውደድ እንደሚገባው ቅዱሳን መጻሕፍት በሚገባ ያስተምራሉ:: ለምሳሌ ያህልም ጠቢቡ ሰሎሞን «ባልንጀራውን የሚንቅ ይበድላል» ሲል የተናገረው የዚህ ማረጋገጫ ይሆናል:: ምሳ.14÷21::

በቅዱስ ወንጌልም እንደተጻፈው የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ እንደሚገባው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለጠየቀው ጎልማሳ የተሰጠው መልስ ትእዛዛትን እንዲፈጽም ነበር:: ትእዛዛቱ እንዲዘረዘሩለት በመጠየቁ ጌታችን «አትግደል፣ አታመንዝር፣አትስረቅ፣በሐሰት አትመስክር፣እናትህንና አባትህን አክብር» በማለት ከዘረዘረለት በኋላ «ባልንጀራ ህን እንደራስህ ውደድ» ማለቱ ባልንጀ ራን መውደድ አምላካዊ ሕግና በተለይም ደግሞ የዘላለምን ሕይወት ለመው ረስ መሠረታዊ መሥፈርት መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ማቴ.19÷19::

በቅዱስ ወንጌል ታሪኩ የተጻፈለት ደጉ ሣምራዊ በመንገድ ላይ ወድቆ ያገኘውን ቁስለኛ አንሥቶ መልካም ነገር ስለአደረገለት፣ ከወንበዴዎችም እጅ ስለ አዳነው ምሕረትም ስለ አደረገለት ባልንጀራው እንደተባለ ተገልጧል:: ሉቃ.10÷25–37:: በደዌ ሥጋ ብቻ ሳይሆን በደዌ ነፍስም ተይዘው ለሚሰቃዩና ዕርዳታን ለሚሹ ሁሉ ደርሶ ከቃለ እግዚአብሔር ተመግበው፣ ጸጋና ረድኤተ እግዚአብሔር ተጎናጽፈው በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖሩ ማድ ረግ ባልንጀራን መውደድ ነው:: ወንበዴ ዲያብሎስ በተለያዩ ሁኔታዎች የሚያንገላታቸውን ደቂቀ አዳም ለመንፈሳዊ የሕይወት ለውጥ ማብቃትና ነፍሳቸውን በኃጢአት ከመሞት መታደግም ባልንጀራን መውደድ ነው:: በጥቅሉ ስንመለከተው በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረውን የሰው ወገን ሁሉ ማንንም ከማን ሳያበላልጡ እኩል በሆነ ፍቅር መመልከትና ማክበር ባልንጀራን መውደድ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል::

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «ነገር ግን መጽሐፍ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ እንደሚል የንጉሥ /የእግዚአብሔርን/ ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ፤ ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራላችሁ፤ ሕግም እንደተላላፊዎች ይወቅሳችኋል» በማለት የተናገረው ባልንጀራን መውደድ ማለት ሁሉን እኩል አድርጎ በአንድ የፍቅር ዓይን መመልከት እንደሆነ ለማስረዳት ነው:: ያዕ.2÷8–9:: ነገር ግን ብዙ ሰዎች ይህን ባለማስተዋል በየ ምክንያቱ አንዱን ከሌላው ሲያበላልጡ ÷ ሰዎችን ከሰዎች ሲለዩ ይታያል:: ለዚህም በየቦታው የሚታየውን ዘረኝነትን /በዘርና በጎሳ መለያየትና በዘመድ አዝማድ ማስተናገድና ፍርድ ማጓደል ን÷ በጸታ እየከፋፈሉ መበደልን፣ ሀብታምና ደሃ እያሉ መከፋፈልን ወዘተ... ማንሣት ይቻላል::

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው የመጽሐፍ ክፍሎች ባልንጀራን መውደድ ማለት ሰውን ሁሉ መውደድ እንደሆነ አረጋግጠውልናል:: አሥረኛው ትእዛዝ ደግሞ ባልንጀራን እንደራስ በመውደድ መፈጸም የሚገባው ነው:: «እንደራስ መውደድ» የሚለው የዚህ ትእዛዝ ሐረግ ፍቺም ሰፊ ትርጉም ያለው ነው:: የሰው ልጅ መልካም ነገርን ለራሱ ይመኛል፣ይህንንም ያደርጋል:: ባልንጀራን «እንደራስ መውደድ» ለራስ የሚሹትን መልካም ነገር ሁሉ ለባልንጀራ ማድረግ ማለት ነው:: በወንጌልም ጌታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ «እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና» በማለት ያስተማረው ይህንኑ የሚያመለክት ነው:: ማቴ.7÷12:: ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ማለት ለራስ ቢያገኙት የሚወዱትን ለባልንጀራ ማድረግ ነው:: ከራስ ወዳድነት፣ውዳሴ ከንቱን በመፈለግ ወይም በሌላ ምክንያት ለእኔ ብቻ ይሁን ማለት ይህንን ሕግ መተላለፍ ነው:: በመሆኑም ባልንጀራን «እንደራስ መውደድ» ማለት ለራስ ሊያገኙት የሚወዱትን ለባልንጀራ ማድረግ ነው::

እንዲሁም ባልንጀራን እንደ ራስ መውደድ ከዚህም ሌላ ተጨማሪ ትርጉም ተሰጥቶት እናገኛለን:: ይህንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ስንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ» በማለት አረጋግጦታል:: 1ቆሮ.10÷24:: ይህ ትምህርቱም ከፍቅር የተነሣ የባልንጀራን ጥቅም ከራስ አስበልጦ መመልከት የሚገባ መሆኑን አስገንዝ ቧል:: ለፊልጵስዩስ ምእመናን በጻፈው መልእክቱም «በአንድ ሃሳብ ተስማሙ፤ አንድ ፍቅር፣ አንድም ልብ፣አንድም ሃሳብ ይሁንላችሁ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር፣ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፣ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ» በማለት ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ማለት ከፍጹም ፍቅር በሚገኝ በትሕትና ባልንጀራን ከራስ እስከማ ስበለጥ ሊደርስ እንደሚችል ገልጦታል:: ፊልጵ.2÷2–4::

ስለሆነም ሰው ባልንጀራውን እንደራሱና ከራሱም በላይ የሚወደው ከሆነ የተቀደሰ የባልንጀራውን ሰውነትና መንፈሳዊ ሕይወት ያጠፋ ዘንድ አይገድለውም:: የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነ አካሉንም በዝሙት አያረክስበ

ትም:: ሀብቱንም ሆነ ንብረቱን አይሰርቅበትም:: በሐሰትም አይመሰክርበትም:: ንብረቱንና ቤቱንም በመመኘትና በመቅናት አይመቀኘውም::

ከአሥርቱ ትእዛዛት መካከል የሰዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚመለከቱትን ሁሉ በመተላለፍ የሚበድል ሰው የፍቅርን ሕግ ይጥሳል:: ባልንጀራውን የማይወድ ከሆነ ይህ ሰው ትእዛዛትን እንዳይጥስ፣ሕግም እንዳያፈርስ የሚከለክለው ገደብ የለም:: ስለዚህም ለሰው ፍቅር የሌለው ማንም ቢሆን ኀሊናውን የሚከብደውና በወን ድሙ ላይም ክፉን እንዳያደርግ የሚቃወመው ውሳጣዊ ስሜትና ሃሳብ ስለሌለ፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመተላለፍ ኃጢአትን እየፈጸመ የዲያብሎስ ባርያ ሆኖ ይኖራል:: ይህ እንዳይሆን ነው አምላካችን እግዚአብሔር «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» በማለት ያዘዘው::

ይህም ፍቅር የእግዚአብሔርን ሕግ በመፈጸም እውነተኛውን የክርስትና ሕይወት በተግባር የመግለጥ የመጨረሻ የዕድገት ደረጃ መሆኑን የሚያስረዳ ትምህርት ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀመዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በላከው መልእክቱ «የትእዛዛት ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልቡና ከበጎ ኀሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው» በማለት የተናገረው ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው:: 1ጢሞ.1÷5:: ስለ ዚህ በዚህ ፍቅር ትእዛዛትን በመፈጸም የሚገኘውን መንፈሳዊ ክብርና ሰማያዊ አክሊል ገንዘብ ለማድረግ መዘጋጀት ያስፈልገናል::

ፈጣሪአችን ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ «ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ እሥራኤል ሆይ ስማ:- ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ አን ተም በፍጹም ልብህ፣በፍጹምም ነፍ ስህ፣ በፍጹምም ሃሳብህ፣በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትለው ናት፤ ...ሁለተኛይቱም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የምትል እርሷን የምትመ ስል ይህች ናት» በማለት ትእዛዛት በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ መጠቃለላቸውን ከማሳየቱም በላይ ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝ መሆኑን አረጋግጦልናል:: ማር.12÷ 29-31:: ስለዚህ እያንዳንዳችን በዕድሜ፣ በዕውቀት፣በሥራ ቦታ፣በማኅበራዊ ኑሮ፣ ይህንም በመሳሰለው ሁሉ ባልንጀራ የሆነውን የሰው ዘር በመውደድ ትእዛዛትን መፈጸምና ሰማያዊውን መንፈሳዊ በረከት ለማግኘት እንድንዘጋጅ ያስፈልጋል::

በዚህ በአሥረኛው ትእዛዝ መሠረት ወንድምን መውደድ ወይም ባልንጀራን እንደራስ የመውደድ ፍቅር የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን በሚገባ ዐውቀናል:: ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም «የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፤ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም» ሲል የተና ገረው ለዚህ ነው:: የእግዚአብሔር ልጆች መንፈሳውያን ናቸውና በመንፈሳዊ ምግባራቸው፣ሰውን በመውደዳቸው ይታወቃሉ:: ቅዱስ ዮሐንስ በመቀጠልም «ከኛ ወንድሞችን የማይወድ በሞት ይኖራል፤ ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ፤» «ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራ ራለት ማንም ቢሆን የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አን ዋደድ» በማለት ፍቅር በተግባር መገለጥ የሚገባው መሆኑን አበክሮ አስገንዝቧል:: 1ዮሐ.3÷ 14-18::

ነቢየ እግዚአብሔር ሳሙኤል «በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ መታዘዝ ከመሥዋዕት ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል» ያለው የእግዚአብሔርን ሕግ መፈጸም በሥራ የሚገለጥ የከበረ ዋጋ ያለውና እግዚአብሔርንም የሚያስደስት መሆኑን ለማስረዳት ነው:: 1ሳሙ.15÷22:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ትምህርቱ ባልንጀራን እንደመውደድ እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ነገር የሌለ መሆኑን ሲገልጥ «አምላክን በፍጹም ልብ፣ በፍጹም አእምሮ፣ ፣በፍጹም ነፍስም፣ በፍጹም ኃይልም ውደድ፣ ባልንጀ ራንም እንደራስ መውደድ በሙሉ ከሚቃጠል መሥዋዕትና ከሌላው መሥ ዋዕት ሁሉ የሚበልጥ ነው» በማለት አስገንዝቦአል:: ማር.12÷33::

ባልንጀራን መውደድና እግዚአብሔርን መውደድ የማይነጣጠሉ ናቸው:: የአንዱ መኖር የሌላውን ሕልውና እየገለጠ ሁለቱም የሰውን ልጅ ከውድቀትና በኃጢአት የተነሣ ከሚመጣ ሞተ ነፍስ የሚታደጉ ሰማያውያን ስጦታዎች ናቸው:: ለዚህ ነው ቅዱስ ዮሐንስ «እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃለን» ያለው:: 1ዮሐ.5÷2-3:: አንዳንድ ሰዎች ይህንን ባለመገንዘብ አንዱን ከሌላው ነጥለው ሲፈጽሙ ይታያሉ:: በጣም የሚቀርባቸውንና የራሳቸው የሆነውን ሰው ይወዱታል:: ለእርሱም ሲሉ እግዚ አብሔርን እስከ መካድ፤ መናፍቅ እስከ መሆን፣ ትእዛዛቱን እስከመተላለፍ ይደርሳሉ:: ለአብነትም ከልጆቻቸው ፍቅር የተነሣ ሲታመሙባቸው በየቃልቻውና በየጠንቋዩ ቤት የሚሄዱ፣ ሃይማኖታቸውን እስከ መካድ የሚደርሱትን ማንሣት ይበቃል:: ይህም ባልንጀራን መውደድ /ፍቅር/ ሳይሆን ከአምልኮ ጣዖት ተለይቶ የማይታይ ነገር ነው::

እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙንም የሚጠላ እስከአሁን በጨለማ አለ፤ ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል፤ ማሰናከያም የለበትም፤ ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፤ በጨለማም ይመላለሳል፤ የሚሄድበ ትንም አያውቅም ጨለማው ዓይኖቹን አሳውሮታልና» በማለት ያስተማረው ትምህርት ባልንጀራን መውደድ ብሩህ የሆነ አምላካዊ ስጦታ መሆኑን የሚገልጥ ነው::1ዮሐ. 2÷9-11::

እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራንም እንደራስ መውደድ የሕግጋት ፍጻሜ ነው፤ ሕግጋት በሁለቱ ተጠቃልለዋልና:: ጌታችን «ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው:: ብሎ እንደተናገረው እግዚአብሔርን የሚወድ ሕጉንም ያከብራል፤ ይፈጽማልም:: ዮሐ.14÷21 :: እንዲሁም «ማንም እግዚአብሔርን እወደዋለሁ እያለ÷ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርን የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን» እንደ ተባለ ባልንጀራን መውደድ ሕግጋትን ለመፈጸም መሠረት ነው:: 1ዮሐ.4÷ 20-21::

ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉ ባልንጀሮቻችንን በመውደድና ትእዛዛቱን በመፈጸም የፍቅር ልጆች፣ እውነተኛም አፍቃሪዎች ለመሆን እንችል ዘንድ ልንበረታ ያስፈልጋል::

***ማጠቃለያ***

*አሥርቱ ትእዛዛት በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር አንደበት የተነገሩ÷ በጣቶቹም የተጻፉና በእርሱ የተሰጡ ናቸው:: ዘጸ.20÷10:: አስፈላጊ ከመሆናቸውም የተነሣ በእግዚአብሔር ጣቶች ከአንድ ጊዜ በላይ በጽላት ላይ ተጽፈው ለሙሴ ተሰጥተዋል:: ዘጸ.5÷6 -21::*

*እነዚህም ትእዛዛት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለው ተመልክተናል:: የመጀመሪያው የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የሚኖረውን አምልኮታዊ ግንኙነት የሚመለከቱ ሦስት ትእዛዛትን ያቀፈ ነው:: እነዚህም እኔ እግዚአ ብሔር አምላክህ ነኝ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ፣ የአምላክን ስም በከንቱ አትጥራ እና ሰንበትን አክብር ናቸው:: ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሰዎች እርስ በርሳቸው ስለሚኖራቸው ግንኙነት የሚያወሱትን ሰባት ትእዛዛት የያዘ ነው::*

*እነዚህ አሥርቱ ትእዛዛት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረጉ ኪዳናት ናቸው:: ዘጸ.24÷4-8:: እግዚአብሔርም ይህንን ቃል ኪዳኑን በዚያ ዘመን ከነበሩት ሰዎች ጋር ብቻ አላደረገም:: «አምላካችን እግዚአብሔር በኮሬብ ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ:: እግዚአብሔር ዛሬ በዚህ በሕይወት ካለ ነው ከእኛ ከሁላችን ጋር እንጂ ከአባቶቻችን ጋር ብቻ ይህችን ቃል ኪዳን አላደረገም::» ዘዳ.5÷2-30:: በመሆኑም በየዘመናቱ የተነሡ የሰው ልጆች ሁሉ ሊፈጽሙትና በረከትን ሊያገኙበት ይገባል:: ትእዛዛቱን ጠብቀን የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት እንችል ዘንድ እርሱ አምላካችን የቸርነቱን ሥራ ይሥራልን:: እነሣሥቶ ያስ ጀመረን አስጀምሮ ያስፈጸመን ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምሥጋና ይግባው::*

*ተፈጸመ::*

# «በአዲስ አበባ ተበራክተው ያሉ ካህናት በደቡብና በሌሎች እጥረት ባሉባቸው ቦታዎች ተዘዋውረው የሁለት እና የሦስት ወራት አገልግሎት እንዲሰጡ ተወስኖ በሥራ ለመተርጐም በዝግጅት ላይ ነን» *ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ*



በወሎ ክፍለ ሃገር ወረሂመኑ አውራጃ ቅን አንባ መድኃኔዓለም በሚባል ቦታ ከአባታቸው ከአቶ ታረቀኝ ወዳጆ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ሂሩት መንግስቱ በ1932 ዓም. ተወለዱ:: እኒህ የቤተክርስቲያን አባት በልዩ ልዩ የሰሜኑ የአገራችን ክፍል በመዘዋወር ዜማ፣ቅኔ፣ አቋቋምና የመጻሕፍት ትርጓሜ ተማሩ:: ዕውቀታቸው በተለይ ያወቁትን ለማሳወቅ ያላቸው ችሎታና ጉጉት በ1961 ዓም. ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ወላይታ አውራጃ በመሄድ በስብከተ ወንጌል አገልግሎት እንዲሰማሩ አደረጋቸው:: በዚያም ሰንበት ተማሪዎችን ካህናትንና ምእመናንን በማስተማር ለሰባት ዓመታት አገለገሉ:: በመቀጠልም ከወላይታ ወደ አዋሳ ተዛውረው ለዓመታት የወንጌልን ትምህርት ካስፋፉ በኋላ ወደ አዲስ አበባ መጡ:: መጥተውም በፓትርያርኩ ልዩ ጽ/ቤትና በስብከተ ወንጌል መምሪያ እስከ 1971 ዓም. ድረስ አገለገሉ:: በ1971 ዓም. በአስተዳዳሪነት ወደምስካዬ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም በመሄድ ለአንድ ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ በ1972 ዓም. ቀሞስ በመሆን በሸዋ ሀገረ ስብከት በሥራ አስኪያጅነት ለሁለት ዓመት ተኩል ሠሩ:: ከዚያም ወደ ጠቅላይ ቤተክህነት ተመልሰው በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ኃላፊ በመሆን ለሁለት ዓመት ተኩል ያህል እንዳገለገሉ በወቅቱ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስና በምእመናኑ ጥያቄ ወደቀደመ ቦታቸው ሸዋ ሀገረ ስብከት ተመልሰው በሥራ አስኪያጅነት ለሁለት ዓመት ተኩል፣ በኋላም ወደ ጠቅላይ ቤተክህነት ተመልሰው በሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ለአንድ ዓመት አገለገሉ:: በ1979 ዓም. ግንቦት 30 ቀን በተደረገው የጳጳሳት ሹመት በጵጵስና ከተሾሙ በኋላ ወደሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ተልከው በሊቀ ጳጳስነት እስከአሁን ድረስ ያገለግላሉ:: ከዚህ ሐዋርያዊ ተልእኮ በተጨማሪ ከ1990 ዓም. ጀምሮ የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛሉ:: ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ:: እኒህ ሥራ ወዳድ የሃይማኖት አባት የዚህ እትም እንግዳችን ናቸው::

<u>*ሐመር*</u> :- በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የሚታወቁት ለስብከተ ወንጌል ባለዎት ፍቅር ነው:: ይህ ፍቅር በልቡናዎ እንዴትና መቼ ሊያድር ቻለ?

<u>*አቡነ ቄርሎስ*</u> :- «እንዴት?» ለሚለው ጥያቄ «በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው » ነው መልሴ:: እግዚአብሔር ስለፈቀደ ለስብከተ ወንጌል የታጨሁ አደረገኝ:: ምናልባት ሥጋዊ ምክንያት ልስጥ ብል በልዩ ልዩ የአብነት ት/ቤቶች ተምሬ ወደ አዲስ አበባ ስመጣ በተለያዩ አድባራትና ገዳማት ያሉ መምህራን ሲያስተምሩ ሳይ እኔ ምንም አለመሆኔን አወኩኝና ተመልሼ ወደ ትምህርት ቤት ገባሁ:: በዚያም የትርጓሜ ትምህርትን እየተማርኩ ከሕጻናት ጋር በመዋል በእነሱ እየተማርኩ እነሱም በእኔ እየተማሩ ከስብከተ ወንጌል አገልግሎት ጋር እየተዋወኩ ሄድኩኝ:: ከዚያም ወደዚሁ በመመለስ ስብከተ ወንጌል ብዙ የሚያንጽ ብዙ የሚያተርፍ መሆኑን ተረድቼ ማስተማር ጀመርኩ:: እንዲያው ለጥያቄህ ይህን ያህል አልኩኝ እንጂ ስብከተ ወንጌል ሥራዬና የተጠራሁበት በመሆኑ ግዴታዬን እየተወጣሁ ነው ማለት ይሻላል::

<u>*ሐመር*</u> :- ብፁዕ አባታችን ለሕፃናት ልዩ ትኩረት ይሰጣሉ ይባላል:: ይህ ከምን የተነሣ ነው?

<u>*አቡነ ቄርሎስ*</u> :- በእውነቱ ለሕፃናት ያለኝ ፍቅር አሁን በቤተክርስ ቲያን አገልግሎት ከጀመርኩ የመጣ አይደለም::ለሕፃናት ልዩ ፍቅርና አክብሮት ያደረብኝ ገና ተማሪ ሳለሁ ነው:: ፊደል ያስቆጠሩኝ መምህሬ አባ ሙላቴ ጨፋ የተማሪ አስ ተማሪ አድርገውኝ ፊደል ይቆጥሩ ዘንድ ከአካባቢው የሚመጡ ሕፃናትን አስተምር ነበር:: በዚያ ጊዜ ምንም እንኳ ራሴም በሕጻንነት የዕድሜ ክልል ውስጥ ብሆንም እንደ ታላቅ ወንድም ሆኜ ሳስተምራቸው ደስ ይለኝ ነበር:: ሕጻናቱም ያከብሩኝና ይወዱኝ ነበር:: የነገርኳቸውን ሁሉ ይቀበሉኝ ነበር:: እና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ለሕጻናት ልዩ አክብሮትና እንክብካቤ መስጠት ጀመርኩኝ:: ሕጻናት ተምረው በጥሩ ሁኔታ በእንክብካቤ ቢያድጉ ለአገርም ሆነ ለቤተክርስቲያን ጠቃሚ ይሆናሉ:: በመሆኑም በቻልኩት ሁሉ ከሕጻናት ባልርቅ ደስ ይለኛል:: ከሕጻናት ጋር መዋል እኮ ነጻነትን ይሰጣል:: ለእነሱ ያለምንም ድካም የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ማስተላለፍ ይቻ ላል::

<u>*ሐመር*</u> :- በዚህ በረጅም ዘመናት የስብከተ ወንጌል አገልግሎትዎ በአንደበትም ከሚሰጡት የወንጌል ትምህርት ጐን ለተተኪው ትውልድ በማስረጃነት ያገለግል ዘንድ መጻሕፍት ጽፈው ለኅትመት አብቅተዋልን?

እንደ እኔ እምነት በአሁኑ ጊዜ በገጠርም ይሁን በከተማ በሰንበት ት/ቤቶች ያለውን የወጣቱን እንቅስቃሴ ያልተረዳው ካህንም ሆነ ምእመን ያለ አይመስለኝም:: ሁሉም ገብቶታል፤ ተረድቶታልም:: ወቅቱ ወጣቱ ቤተክርስቲያኑንእናቱ መመኪያዋ ያለበት እያለም ሲያገለግላት የተነሣበት ወቅት ነው

**አቡነ ቀርሎስ** ፡- በእውነቱ የመነኩሴ ልጅ መጽሐፍ በመሆኑ መጽሐፍ ጽፎ ለማሳተም ከፍተኛ ፍላጐት ነበረኝ:: ይሁንና ቤተክርስቲያኔ ከሰጠችኝ የሥራ ኃላፊነት አንጻር የማስባቸውን መጻሕፍት አዘጋጅቶ ለማሳተም ጊዜ የለኝም:: ሩጫዬ የተሰጠኝን የሥራ ኃላፊነት ለማሸነፍ ነውና:: የሆነው ሆኖ «ሴቶች በቤተክርስቲያን»፣«የቃል ዐዋዲ መነሻው ምንድን ነው ?» በአገራችን ከፍተኛ የቅድስና ሥራ ሠርተው ቢያልፉም ታሪካቸው ባለመታወቁ ስማቸው የማይዘከሩ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳንን ታሪክ የያዘ «አባቶችን እንወቅ» በሚል ርዕስ ያለቀላቸው ናቸው ባልልም ከሞላ ጎደልዘጋጅቻቸው የተገባደደ መጻሕፍት አሉ:: ይሁንና በጊዜ እጦት የተነሣ ማሳተም አልቻልኩም:: ሌላው የገንዘብ ችግርም አለብኝ:: ገንዘቤ ቋት የለውም:: አብሮ ከእኔው ጋር የሚያልቅ በመሆኑ የማሳትምበት ገንዘብም የለኝም::

**ሐመር** ፡- በአሁኑ ወቅት ጠቅላይ ቤተክህነት ምን ያህል መምሪያዎችና ሠራተኞች አሉት?

**አቡነ ቀርሎስ** ፡- አስራ ሁለት መምሪያዎችና ከሁለት መቶ በላይ ሠራተኞች አሉት::

**ሐመር** ፡- ቤተክህነት ሠራተኞቿን እንዴት ታስተዳድራለች? የደሞዝ አከፋፈል? የዕድገት ደረጃ? የጡረታ ጊዜ ወዘተ...ሠራተኞችን ስትቀጥርስ መስፈርቷ ምንድ ነው?

**አቡነ ቀርሎስ** ፡- ቤተክህነት የራሷ ሠራተኞች እስካሏት ድረስ በራሷ ደንብና መመሪያ መሠረት ታስተዳድራለች:: ደመወዛቸውን በሚመለከትየው እንደቤተክርስቲያኗ አቅም መሠረት እንደየደረጃቸው ያገኛሉ:: ዕድገታቸውን በሚመለከት እስከ አሁን ሲገኝ ሲገኝ እየታየ ይጨመርላቸዋል:: እንጂ እንደ ሌላው መሥሪያ ቤት በዓመት በሁለት ዓመት የደሞዝ ጭማሪ የለም:: ለወደፊቱ ግን የደሞዛቸውም ሆነ የዕድገታቸው ስኬል በመዘጋጀቱ በዚህ ዙሪያ የተሰናዳ ሥራ የምንሠራ ይመስለኛል:: በደሞዝ አከፋፈልና ዕድገት ብቻ ሳይሆን በአቀጣጠሩም ቢሆን በሥራ ላይ ሊውል በዝግጅት ላይ ያለው ጥናት ጥሩ ሥራ እንድንሠራ የሚያደርግ ይመስለኛል:: የሚውለው መስፈርት ግን ሃይማኖትን፣ምግባርንና ሌሎችን መሠረታዊ መስፈርቶች ያሟላ በመሆኑ ችግሩ ይቃለላል የሚል ግምት አለኝ::

**ሐመር** ፡- በአጥቢያ ደረጃ በከተማ አድባራት በሚገኙና በገጠር አድባራት በሚገኙ የካህናት ቁጥር መካከል እጅግ የላቀ ልዩነት አለ ይባላል:: ይህ ጉዳይ ምን ያህል እውነት ነው?

**አቡነ ቀርሎስ** ፡- በከተማና በገጠር አድባራት የካህናት ቁጥር መካከል ያለው ልዩነት በግልጽ የሚታይ በመሆኑ እውነትነት አለው:: ቤተክርስቲያን በከተማም ትኑር በገጠር፣በወርቅና በዕንቁ ትሠራ በጭቃ ወይም በጨፈቃ በውስጧ የሚጠራው ስመ እግዚአብሔር ነው፤ የሚፈተተው የጌታችንና የመድኃኒታችን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው:: ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያቶች በከተማው ያለውና በገጠር ያለው የካህናት ቁጥር የተጣጣመ አይደለም::: ከምክንያቶቹ አንዱና ዋንኛው በከተማ አካባቢ የካህናቱ ደሞዝ በጥሬ ገንዘብ መሆኑና ጠቀም ማለቱ ነው:: አንድ ካህን በወር እስከ ስምንት መቶና እዚያ አካባቢ ያገኛል:: የገጠሩ ግን በብዛት የወር ደሞዝ የተተመነለት አይደለም:: የገጠሩ ካህን ደሞዙ እህል ነው:: በዓመት አንድ ጊዜ እህል ይሰፈርለታል:: ያንን እንደ ሀሳቡ እያደረገ ያገለግላል::



በ17ኛው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ

ምንም እንኳን በከተማውና በገጠሩ ያሉት ካህናት ቤተክርስቲያኗ የምትሰጠውን ትምህርት እኩል ተከታትለው ሥልጣኑን የተቀበሉት ቢሆንም የቤተክርስቲያናችን የበጀት ብጀታ ማዕከላዊ ባለመሆኑ በከተማ ባለው ካህንና በገጠር ባለው ካህን ቁጥር መካከል የጐላ ልዩነት እንዲፈጠር ሆኗል:: ያም ይኸውና ካህናት በከተማ አድባራት በወር አንድ ጊዜ እንኳ ሊደርሳቸው እስከማይችል ተበራክተው ሲገኙ በገጠር አድባራት ደግሞ ከወር አንድ ጊዜ ብቻ የሚቀድስ አንድ ካህን ብቻ እንዲኖር አድርጓል:: አንዱም ጠፍቶ የሚዘጋው ደብር ብዙ ነው::

**ሐመር** ፡- ይህንን ከፍተኛ ችግር ለመፍታት ምን እየተደረገ ነው?

**አቡነ ቀርሎስ** ፡- በእውነቱ ይህንን የቁጥር አለመመጣጠን ለማስተካከል ብዙ ጥረትና ድካም ያስፈልገዋል:: በአሁኑ ወቅት ቤተክርስቲያን ለዚህ ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሰጥታ ጉዳዩን የሚያጠና ኮሚቴ ተቋቁሞ እውነትነቱ በመረጋገጡ ጥናቱ በአስተዳደር ጉባኤ ታይቶና ጸድቆ ወደቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቧል:: ጥናቱ ለአንድ ደብር ምን ያህል መሆን እንዳለበትም ተሠርቶ ቀርቧል:: በአዲስ አበባ ተበራክተው ያሉ ካህናትም በደቡብና በሌሎች የካህናት እጥረት ባሉባቸው ቦታዎች ተዘዋውረው የሁለትና የሦስት ወራት አገልግሎት እንዲሰጡ ተወስኖ አሁን በሥራ ለመተርጐም በዝግጅት ላይ ነን::

**ሐመር** ፡- በተለያዩ ጊዜያት በመንግሥት ደረጃ ለውይይት ቀርበው የሚወሰኑ ውሳኔዎች አሉ:: ለምሳሌ የወሊድ ቁጥጥር ፖሊሲ ሊጠቀስ ይችላል::እነዚህን ውሳኔዎች በሚመለከት ቤተክርስቲያን ንቁ ተሳትፎ የላትም የሚል አስተያየት ይሰማል:: በእነዚያ ቦታዎች ቤተክርስቲያን ወክላ የምትልካቸው ስምም ለጉዳዮች ባዕድ የሆኑ፣ስምተው ብቻ የሚመለሱ እንጂ ተከራክረውና አሳምነው ውሳኔዎች ከቤተክርስቲያን አንፃር እንዲወሰኑ የሚያደርጉ አይደሉም ሲባል ይሰማል:: ይህንን አስተያየት እንዴት ያዩታል?

**አቡነ ቀርሎስ** ፡- ቤተክርስቲያናችን ተናግረው የማያስረዱ ተከራክረው የማያሸንፉ አባቶች የሏትም:: ከጉባኤ ሂደው

በዚያ ጊዜ ምንም እንኳ ራሴም በሕጻንነት የዕድሜ ክልል ውስጥ ብሆንም እንደ ታላቅ ወንድም ሆኜ ሳስተምራቸው ደስ ይለኝ ነበር:: ሕጻናቱም ያከብሩኛና ይወዱኛ ነበር:: የነገርኳቸውን ሁሉ ይቀበሉኝ ነበር:: እና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ለሕጻናት ልዩ አክብሮትና እንክብካቤ መስጠት ጀመርኩኝ::

አፍረው የሚመጡ አባቶች የሉም:: እና እንደተባለው ብዙዎች ብዙ ብዙ ሊሉን ይችላሉ:: የዓለሙ ጠባይ ነውና:: በማንኛውም ቤተክርስቲያን አቋሟን ልትገልጥባቸው በሚገቡ አጀንዳዎች ቤተክርስቲያን በንቃት ያልተሳተፈችበት ጊዜ የለም:: እንደምሳሌ የተነሳውን የወሊድ ቁጥጥርን በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱሳዊት ቤተክርስቲያናችን ከመጽሐፍ ባገኘችው ትዕዛዝ መሠረት ልጆቿ ማንኛውንም የወሊድ መቆጣጠሪያ መድኃኒት እንዳይጠቀሙ ታዝዛለች:: ይህም በቅዱስ ሲኖዶስ የተወሰነ ነው:: የእግዚአብሔር ቃል በይግባኝ የሚታይ አይደለም:: እግዚአብሔር ያዘዘውን ቃል መፈጸም እንጂ:: ስለዚህ ቤተክርስቲያን በማንኛውም ውሳኔዎችና ዐዋጆች ላይ ንቁ ተሳትፎ ታደርግ ነበር፤ አሁንም እያደረገች ነው፣ወደፊትም ታደርጋለች::

*ሐመር* :- በአሁኑ ወቅት የቤተክርስቲያኒቱን ይዞታ በተለይ ቤቶችን በሚመለከት ክርክርና ችግር እየተፈጠረ ነው ይባላል:: እውነታው ምን ያህል ነው?

*አቡነ ቄርሎስ* :- መቼም፤ በዓለም ላይ ክርክር የሌለበት ነገር የለም:: በመሆኑም ምንም እንኳን ጥቂት የተረከብናቸው ቢኖሩም በብዛት ቤቶቻችን ከእጃችን ስላልገቡ በክርክር ላይ እንገኛለን:: ከላይ መንግሥት ቢጽፍልንም ከታች ያለው ውጣ ውረድ እንድንረከብ አላስቻለንም:: የተረከብናቸውም ቢሆኑ በብዛት የተጐዱ ናቸው:: በተደረገው የመንግሥት ለውጥ ግለሰቦች የሸጧቸውም አሉ:: የሆነው ሆኖ ያልተረከብናቸውን እንድንረከብ በውዝ ግብ ላይ ነው ያለነው:: ቤቶቹ የእናንተ ለመሆናቸው ማስረጃ አቅርቡ ብለው ናል:: እኛም በተቋቋመው ኮሚቴ አማካኝነት ማስረጃዎቻችንን እያቀረብን እንገኛለን::

*ሐመር* :- ቤተክርስቲያኒቱ የምታከራያቸው ቤቶች ነጋዴዎቹ /ተጠቃሚዎቹ/ ሊከፍሉ ከሚችሉት በላይ /ውድ ናቸው ይባላል:: ይህ ምን ያህል እውነትነት አለው?

*አቡነ ቄርሎስ* :- ይህን ጉዳይ እኛም ሰምተነዋል:: ሰምተንም ዝም ብለን አልተቀመጥንም:: ጉዳዩን አጥንቶ አፋጣኝ መልስ የሚሰጥ ቦርድ አቋቁምን:: ቦርዱ አጥንቶ እንዳቀረበው ከሆነ እውነትም የበዛባቸው አሉ:: በመሆኑም ይህ ቦርድ ሁኔታዎችን እያየ ለጥያቄያቸው ተገቢውን መልስ ሰጥቷል፤ እየሰጠም ነው ያለው::

*ሐመር* :- በታሪክ እንደምናነበው ቀደም ባሉት ጊዜያት ቤተክርስቲያን በአገሪቱ በሚከናወኑ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ውስጥ ላቅ ያለ ሚና ነበራት:: ያ ጉዳይ አሁን ቀዝቅዟል ይባላል:: ለዚህ ጉዳይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?

*አቡነ ቄርሎስ* :- ብዙዎች ብዙ ሊናገሩ ይችላሉ:: እኛ ግን ካለን ይዞታ ወደ ኋላ ያልንበት ጊዜ የለም:: ለምሳሌ ቀደም ሲል ተዘግተው የነበሩ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች እንደ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ እና ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ት/ቤት ከፍታ በዲፕሎም፣በዲግሪም እያስለጠነች እየላከች ነው:: ምሩቃኑ በሥራ ሲሰማሩ አገሪቷን በልዩ ልዩ መንገዶች ይጠቅማሉ:: እንደ ዚሁም በአገሪቷ በልዩ ልዩ ቦታዎች የሚገኙና ሥራቸውን አቁመው የነበሩ ስድስት የካህናት ማሠልጠኛ ተቋማት ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል:: ሰንበት ት/ቤቶችም በየአጥቢያው እየተስፋፉ ነው:: ወጣቱ በቤተክርስቲያን መሰባሰቡ ለአገር ትልቅ ጥቅም አለው:: ዛሬ በተለያዩ አጥቢያት የተቋቋሙ ሰንበት ት/ቤቶች አባላት ችግኝ በመትከል፣ለችግረኞች ልዩ ልዩ የመርጃ ተቋማት በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ:: ይህም ለአገር ዕድገት ያለው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም::

በማኅበራዊ ኑሮ ተሳትፎም በልዩ ልዩ አኅጉረ ስብከቶች ቤተክርስቲያን የተለያዩ የልማት አውታሮችን በመዘርጋት ለምእመናን አገልግሎት በመስጠት ላይ ትገኛለች:: ክሊኒክ ትምህርት ቤቶች፣ውኃና ሌሎችም:: በእውነቱ ኢትዮጵያን ከቤተክርስቲያን ቤተክርስቲያንን ከኢትዮጵያ ለይቶ የሚያይ ካለ ተሳስቷል:: ሕዝቡ ሲያዝን የምታዝን ሲሰደድ የምትሰደድ ናት:: የሚያወራ ያውራ የሚሠራ ይሥራ ይህ የዓለሙ ጠባይ ነው::

*ሐመር* :- ቤተክርስቲያን በአንዳንድ የግል ጋዜጦች ለሚሰነዘሩባት ውንጀላዎች መልስ ለመስጠት ምን ያህል ብቁ ናት?

*አቡነ ቄርሎስ* :- ቤተክርስቲያን መብቷን ለማስከበር ያላት ብቁነት በማስተማሯ ይገለጣል:: እንደክርስትና ብቁነት ማለት ጠላትን መውደድ ያጠፋን መምከር ነው:: በመሆኑም ከሚያብዱት ጋር አብሮ ማበድ ፍሬ የለውምና በተለያዩ ጋዜጦች ላቀረቡብን ውንጀላዎችና ትችቶች ያን ያህል ተከታትለን ፍርድ ቤት የቀረብንበት ጊዜ የለም:: የሰዎች የውንጀላ ሥራ የዓለሙ ጠባይ ከመሆኑ ባሻገር የእግዚአብሔር ቃል «የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤በትዕግሥት ሆናችሁ ከቻላችሁ ክብርን ትወርሳላችሁ» ይለናልና ሁሉንም በቅሬታ ዓይን አንመለከተውም::

እንደተባለው በአሁኑ ወቅት ዴሞክራሲ የሚለውን ዘይቤ በመያዝ በተለይ አንዳንድ የግል ጋዜጦች የሚያሳትሙት ተሳዳቢዎቹ ሆነዋል:: በእውነቱ እኔ ባለኝ ዕድሜ እንደዚህ አይነት የአንተ አንተ ስድብ አይቼ አላውቅም:: ይህ ነገር ለእኔ እንግዳ ነው:: እኔ ሳድግ አንዱ ሌላውን ፈርቶና አክብሮ ነበር የሚኖረው:: የሰውን ክብር የሚነካ የራሱም ክብር የለውም::

*ሐመር* :- በአሁኑ ወቅት ንዋያተ ቅድሳት እየተዘረፉ በሕገ ወጥ መንገድ ከአገር እየወጡ ነው:: ለዚህ ጉዳይ ምክንያቱና መፍትሂው ምንድን ነው ይላሉ?

*አቡነ ቄርሎስ* :- የዚህ ጉዳይ ምክንያቶች ብዙዎች ናቸው:: አንደኛው በሕገ መንግሥቱ ሌቦችን በተመለከተ ተደንግጐ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መላላት ነው:: አሁን በመሥራት ላይ ያለው የሌቦች አንቀጽ ቀደም ሲል ሌቦች ባልበዙበት ፈሪሃ እግዚአብሔር በነበረበት ዘመን ነው የወጣ :: አሁን ግን ያ ሁሉ ጠፍቶ ሰው ሰውን እስከ መስረቅ የደረሰበት ጊዜ ነው:: አንድ ንዋያተ ቅድሳትን ሲሠርቅ እጅ ከፍንጅ ተይዞ ቅጣቱ ብዙም ከባድ አይደለም:: በመሆኑም የሕጋችን የቅርሳ ቅርስን ዘረፋ የመከላከል ልልነት የመጀመሪያው ምክንያት ነው:: ጠላቶቹ ቤተክርስቲያንን ብቻ የጐዱ እየመሰላቸው ለአገራቸው ሳይቀር ክብርና ኩራት የሆኑትን የቤተክርስቲያን ቅርሶች ይዘርፋሉ:: የንዋያተ ቅድሳቱ ጠባቂዎች ራሳቸው ድሆች ስለሆኑ ዘራፊዎች እነሱንም ይገዟቸዋል:: በዚህ የተነሣ በአባቶቻችን ተጋድሎ የቆዩን ሀብቶቻችን ተዳፍረዋል::

መፍትሄውን የሚመለከት ንዋያተ ቅድሳት የሁሉም ሀብት ናቸውና ሁሉም ኢትዮጵያዊ በየአካባቢው ያሉትን ቢጠብቅ መልካም ነው:: ካህናት እንደ ኖላዊነታቸው ንዋያተ ቅድሳቱንም መጠበቅ አለባቸው:: ቤተክርስቲያንም ለዘረፋው መስፋፋት ውስጣዊ ምክንያቶች የሆኑትን ማስተካከል ይኖርበታል:: እንዳልኩት በገንዘብ የማይተመኑ ንዋያተ ቅድሳትን የሚጠብቁት አባቶች በቀላል ደሞዝ በመሆኑ የእነሱን ደሞዝ ማስተካከል፣ለሌባ በተጋለጠ ሁኔታ የተቀመጡትን ንዋያተ ቅድሳት የሚገባቸውን ቦታ ሠርቶ ማስቀመጥ ፣ምእመናን ንዋያተ ቅድሳቱ የራሳቸው መሆናቸውን እንድያውቁ ማድረግና ሌሎችም ከቤተክርስቲያን ይጠበቃሉ::

ቤተክርስቲያን መብቷን ለማስከበር ያላት ብቁነት በማስተማሯ ይገለጣል:: እንደክርስትና ብቁነት ማለት ጠላትን መውደድ ያጠፋን መምከር ነው:: በመሆኑም ከሚያብዱት ጋር አብሮ ማበድፍሬ የለውምና በተለያዩ ጋዜጦች ላቀረቡብን ውንጀላዎችና ትችቶች ያን ያህል ተከታትለን ፍርድ ቤት የቀረብንበት ጊዜ የለም::

*ሐመር* :- በሊቀጵጵስና ዘመንዎ አብዛኛ
ውን ጊዜ ያሳለፉት ሰሜን ወሎ ነው::
በዚያ ስለነበርም ሐዋርያዊ ተልእኮ ዘር
ዘር አድርገው ቢያስረዱን?

*አቡነ ቄርሎስ* :- 1979 ዓ.ም. በሊቀ
ጵጵስና ማዕረግ ከተሾምሁ በኋላ በቀጥታ
የተላኩት ወደዚሁ ሀገረ ስብከት ነበር::
በእውነቱ ሀገረ ስብከቱ የነበረበት ሁኔታ
እጅግ ብዙ ተጋድሎና ሩጫ የሚያስ
ፈልገው ሆኖ ነበር ያገኘሁት:: እንደ
ልብ ተዟዙሮ ማገልገል ይቻል ዘንድ
መንገዶችና ሌሎች መገናኛ መስ
መሮች አልነበሩም:: ዛሬ ለሀገረ ስብከቱ
እንቅስቃሴ የተሻለ መሆን ከፍተኛ
ድርሻ ያላቸው የሰንበት ት/ቤቶች አልተ
ጠናከሩም ነበር:: ምእመናን ልጆቻቸውን
አስተምረው ለወግ ለማዕረግ የሚያበ
ቁባቸው ትምህርት ቤቶች፣ቢታመሙ
የሚታከሙባቸው ክሊኒኮች፣ውኃ፣ወፍጮ
የመሳሰሉትን አልነበሯቸውም:: በመሆ
ኑም እኔም ሆንኩ ሌሎች በቦታው
የነበሩ ወንድሞቼ ትኩረታችን ከስብከተ

*ሐመር* :- የሥራ እስኪያጅነት ሥራዎ
ሰሜን ወሎ ባለው የሊቀጵጵስና አገልግ
ሎትዎ ላይ ተጽዕኖ አላሳደረብትም
ይላሉ? ለመሆኑ የሀገረ ስብከቱን እንቅ
ስቃሴ እንዴት ይመሩታል?

*አቡነ ቄርሎስ* :- በእውነቱ ሁለቱን
ሥራዎች ደራርቦ መያዙ በሁለቱም
ሥራዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል::
መጀመሪያ እኔ ለዚህኛው ታላቅ ኃላፊ
ነት ስመረጥ ሀገረ ስብከቱ ሊጐዳ ይች
ላል በሚል ሌላ ሊቀ ጳጳስ እንዲቀመ
ጥበት ተደርጐ ነበር:: ነገር ግን የሀገረ
ስብከቱ ምእመናንና ካህናት ሰላማዊ
ሰልፍ አድርገው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ
ጳውሎስን በደብዳቤ ጠይቀው ለቅዱስ
ሲኖዶስ ቀርቦ የምእመናንና የቀሳውስቱ
መላ ሀገረ ስብከት ፈቃድ ሁሉንም ያገ
ልግሉ በማለት ስለተወሰነ ነው::
ምንም እንኳን የሥራ አስኪያጅነቱን ኃላ
ፊነት ባልተውም ሀገረ ስብከቱን መልሼ
እንድልኀዝ ሆኛለሁ:: የሆነው ሆኖ እንደ
ቀደሙ አብሬያቸው እየዋልኩ እያደርኩ

ም? እንኳን በ30 ዓመት በ30 ቀን
ብዙ ይወሳል:: ለማንኛውም በ196
ዓ.ም. በነበረው የመንግሥት ለውጥ በ
ቡብ የአገራችን ክፍል በነበርኩበት ጊ
ብዙ ችግሮች ደርሰውብኛል:: ነገር ግ
የማልረሳው በኋላ ለታላቅ ክብር የበ
ትን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖ
/እዚያ በነበሩበት ጊዜ አባ መላኩን
እኔን ባላወቅነው ምክንያት በባለሥል
ናቱ እንድንሞት ተፈርዶብን የሚገድለ
ሰው ተመርጦ ገዳያችን የሚመቸ
ቦታና ሰዓት ሲፈልግልን እሱ ራ
ሊሞት በቅቷል:: እንዲሁም አንድ ጊ
በዚያው ክልል በሐሰት ወንጅለውኝ የ
ባት ወረዳ ካህናት በተሰበሰቡበት ጉባ
ፊት አቁመውኝ ነበር:: ነገር ግን የባሕ
ንን ጠማር የለወጠ አምላክ የእኔን
ውን ጀላ ሐሰት እንደሆነ ገልጾ አት
ፎኛል:: በተረፈ ለስብከተ ወንጌ
በምዘዋወርበት ጊዜ ማደሪያ አጥቼ በዛ
ተጠልዬ ያደርኩባቸው ቀናት ብዙዎ
ናቸው:: ነገር ግን ከዚያ ሁሉ በኋላ እ



*በካህናት ሥልጠና ተገንተው ሲያስተምሩ (ሰሜን ወሎ)*

ወንጌል አገልግሎቱ ጋር ከላይ የጠቀስ
ኳቸው ማኅበራዊ አውታሮች እንዲያገኙ
ማድረግ ነበር:: ሀገረ ስብከቱን ተዘዋው
ረን ካየን በኋላ እግዚአብሔር በፈቀደ
በቤተክርስቲያናችን የልማት ኮሚሽንና
በኖርዌይ የእርዳታ ድርጅት አማካኝ
ነት ልዩ ልዩ ማኅበራዊ አውታሮች ተቋ
ቋሙ:: በአሁኑ ወቅት እንደ ትምህርት
ቤት፣ክሊኒክ፣ውኃና ወፍጮ ባሉት የማ
ኅበራዊ አውታሮችን በሚመለከት የሀገረ
ስብከቱ ምእመናን በተወሰነ ደረጃ ችግሩ
ተቃልሎላቸዋል:: መንፈሳዊ ሕይወታቸ
ውን በሚመለከትም ባላቸው የሃይማኖት
መሠረት ላይ ፀንተው ይኖራሉ:: የም
እመናኑ ሕይወት በወንጌል መጽናትና ፣
በሥርዓተ ቤተክርስቲያን መጓዝ በአካባ
ቢው የሚገኙ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት
ልጆቼ የሚመሰገኑ ናቸው::

ባልሠራም ብቅ እያልኩ አያቸዋለሁ ስል
ግን እንደ ሊቀጳጳስነቴ ማየት የሚገባኝን
ያህል አይደለም::

*ሐመር* :- በዚያው አካባቢ እንደመወ
ለድዎ እዚያ በነበሩባቸው ዓመታትም
ሆነ አሁን ከሥጋ ዘመዶችዎ ጋር ይገና
ኛሉ?

*አቡነ ቄርሎስ* :- አንድ ሰው ከመነኮሰ
ምን የሥጋ ዘመድ አለው ብለህ ነው?
መነኮስ ሞተ'ኮ ነው:: እንኳንስ ከመነኮ
ስኩ ቀድሞ ተማሪ ቤት እያለሁም
ብዙም አንገናኝም ነበር::

*ሐመር* :- በሕይወት ዘመንዎ ሲያስታ
ውሱት የሚኖር አሳዛኝ ነገር ካለ ቢነግ
ሩን? የሚያስደስትዎትስ?

*አቡነ ቄርሎስ* :- ስንቱ ይወሳል ብለህ
ነው? የሰው ሰውነት ምን ጊዜም ቢሆን
የመከራና የደስታ መተላለፊያ አይደለ

ዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ያስተማርኳቸ
ለፍሬ ሲበቁ፣እኔም ለዚህ መብቃቴ
ላይ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ::

*ሐመር* :- በአንዳንድ አህጉረ ስብከቶ
የወጣቱ በቤተክርስቲያን አካባቢ መሰ
ሰብ እንደትርፍ ነገር ይታያል:: ይህን
ነገር በሚመለከት እንደአባትነትዎና እ
ደሥራ አስኪያጅነትዎ የሚሰጡት አስ
ያየት ምንድን ነው?

*አቡነ ቄርሎስ* :- እንደ እኔ እምነ
በአሁኑ ጊዜ በገጠርም ይሁን በከተ
በሰንበት ት/ቤቶች ያለውን የወጣቱ
እንቅስቃሴ ያልተረዳው ካህንም ሆ
ምእመን ያለ አይመስለኝም:: ሁሉ
ገብቶታል፤ ተረድቶታልም:: ወቅ
ወጣቱ ቤተክርስቲያኑንእናቴ መመኪያ
ያለበት እያለም ሊያገለግላት የተነሣበ
ወቅት ነው:: የወጣቱ በቤተክርስቲያ
አካባቢ መሰባሰብ ትልቅ የቤተክርስቲያ

*ወደ ገጽ 23 ዞሯል*

አሁን ግን ያ ሁሉ ጠፍቶ ሰው ሰውን እስከ መስረቅ የደረሰበት ጊዜ ነው:: አንድ ንዋያ
ቅድሳትን ሲሠርቅ እጅ ከፍንጅ ተይዞ ቅጣቱ ብዙም ከባድ አይደለም:: በመሆኑም የሕጋች
የቅርሳ ቅርስን ዘረፋ የመከላከል ልል ነት የመጀመሪያው ምክንያት ነው::

## ነጻ ፈቃድ ማለት ምን ማለት ነው?

*__ጥያቄ 1__ : የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ አለው ሲባል እሰማለሁ:: ለመሆኑ ነጻ ፈቃድ ማለት ምን ማለት ነው? ይህ የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ገደቡ እስከምን ድረስ ነው?*

*መሠረት አለባቸው*

*አ.አ*

__መልስ__ : የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረ ነው:: ዘፍ 1÷26:: ሲፈጥረውም የሚያስብና የሚያስተውል ሆኖ ነው:: ከዚህም የተነሣ ክፉውንና ደጉን ማወቅ በሚችልበት አእምሮው ከሁለት አንዱን መርጦ እንዲጓዝ ነጻነት አለው:: እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረው በኋላ የሚጠቀመውንና የሚጎዳውን ነግሮ በነጻነት አኑሮታል:: ከዚህም በኋላ የሚበጀውን መምረጥ የእርሱ ድርሻ ነበር:: በሕይወት ለመኖርም ሆነ ለሞት የሚያበቃውን ሥራ ለመሥራት መወሰን በእጁ ነው:: እንግዲህ ይህ ነው የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ የሚባለው::

በመሆኑም ነጻ ፈቃድ ማለት አንድ ሰው አንድን ድርጊት ለመፈጸም ወይም ላለመፈጸም ያለው የፍላጎት ነጻነት ነው:: የሰው ልጅ ሊያስመሰግን ወይም ሊያስወቅስ÷ዋጋ ሊያሰጥ ወይም ሊያስቀጣ÷ ሊጎዳ ወይም ሊጠቅም የሚችለውን አድራጎት ለማድረግም ሆነ ላለማድረግ ነጻ ፈቃድ አለው:: አንድን ድርጊት የሚያደርገው ወይም የማያደርገው ማንም ሳያስገድደው በፍላጎቱ ነው:: የነጻ ፈቃዱም ውጤት እንደ ምርጫው ሕይወት ወይም ሞት ሊሆን ይችላል:: ይኸንን በተመለከተ በኦሪቱ «ተመልከት ዛሬ በፊትህ ሕይወትን መልካምነትን÷ሞትን ክፋትን አኑሬልሃለሁ» ተብሏል:: ዘዳ 30÷15::

አዳም በዚህ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ነጻ ፈቃዱ አትንካ የተባለውን ነካ:: አትብላ የተባለውን በላ:: ኃጢአትን ሠራ:: እግዚአብሔርም መከልከል ሲችል ለሰው ልጅ የተሰጠውን ነጻ ፈቃድ አልተጋፋውም:: በለስን ቀጥፎ ወደ ሞት ሲጓዝ አልተቃወመውም::

አዳም በበደሉ ምክንያት ፀጋውንና ክብሩን አጣ:: ተሰጥቶት የነበረውም ሙሉ ነጻ ፈቃዱ ጎዶሎ ሆነበት:: ምክንያቱም ሕይወትን አጥቷልና:: ምርጫው ምንም ይሁን ምን ወደ ሞት የሚጓዝ የሞት ባርያ ሆነ:: ኤፌ 2÷1:: ነገር ግን በበደሉ ተጸጽቶ ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔር የቀደሞውን ሙሉ ነጻነቱን ሊመልስለት ተስፋ ሰጠው:: ሕይወትንና ሞትንም በፊቱ አኑሮ የፈቀደውን እንዲመርጥ ሥልጣኑን ሊሰጠው ከሰማየ ሰማያት ወርዶ÷ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ አዳነው::

በመሆኑም እግዚአብሔር አምላክ ለአዳም የቀድሞውን ሙሉ ነጻ ፈቃዱን ሊመልስ ማድረግ የሚገባውን ሁሉ አድርጎለታል:: በሞቱ ዕዳውን ከፍሎለታል:: 1ቆሮ 15÷22:: በፍቅሩ እንዲኖር÷መንገዱንም እንዲያውቅ በባሕርይ ልጁ አስተምሮታል:: ዮሐ 3÷31÷36:: ዮሐ 524:: የሕይወትን መንገድ ከፍቶ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» ብሎ ቢበድል ከበደሉ የሚነጻበትን የንስሐ በር ከፍቶለታል:: ማቴ 4÷17:: ኃይልና ብርታትን አግኝቶ ዲያብሎስን እንዲያሸንፍ ከእርሱ ጋር አንድ ሆኖ ይኖር ዘንድ ሥጋውንና ደሙን ሰጥቶታል:: ዮሐ 6÷53–59::

በዚህ መልኩ ወደ ቀድሞ ክብሩና ጸጋው መለሰው:: ሕይወትና ሞትን መምረጥ እንዲችል በሙሉ ነጻ ፈቃድ አኖረው:: «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» በማለት በግድ ሳይሆን በፍቅር እንዲገዛለት ትእዛዙንም ሰጠው:: ለአብነትም አንድ ሰው ወደ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቦ «የዘላለም ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ» ብሎ ሲጠይቀው የመለሰለትን ማንሣት ይቻላል:: «ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ» ብሎ መልሶለታል:: ማቴ 19÷16–17:: በዚህ ውስጥ «ብትወድ» የሚለው ቃል ለሰው ልጅ የሰጠውን የፈቃድ ነጻነት ያመለክታል::

በዚህም የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን መንገድ የመከተል ወይም ያለመከተል ነጻነት እንዳለው ሲገልጽ «የሚወደኝ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ» ሲል በፍቅር ጠርቶታል:: በመሆኑም ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ በተሰጠው በዚህ ነጻ ፈቃድ መሠረት ሕይወትን የማይፈቅድ በአመጽ ተገዞ ሞትን መምረጥ እንዲችል እያንዳንዱ በራሱ ላይ ስልጣን አለው::

ስለዚህ የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ሲኖር ለሞትም ሆነ ለሕይወት ሙሉ ነጻ ፈቃድ አለው:: ይህም ነጻ ፈቃዱ እስከዚህ ተብሎ የሚገደብ አይደለም:: የሰው ልጅ ሕይወትን ወይም ሞትን ለማግኘት የፈለገውን መምረጥ ይችላል:: እግዚአብሔርም ይህንን ለሰው ልጅ የሰጠውን ነጻ ፈቃድ አይጋፋውም:: «ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ነቢያትን የምትገድል÷ወደ እርሷ የተላኩትንም የምትወግር÷ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደ ምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድኩ÷አልወደዳችሁምም» የሚለው የጌታ ቃልም ይህንኑ ያመለክታል:: ማቴ 23÷37::

ምን አልባትም ይህ ሲባል «በነጻ ፈቃድ ለመኖር እችላለሁ» በማለት ከሚገባው አልፎ የሰው ድንበር ይገፋ ማለት አይደለም:: ሞትን መርጦ በኃጢአት ሲኖር እንኳን ከመጠን አልፎ በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ቢነሣ÷ ክርስቲያኖችን ቢያሳድድ÷ ቤተ ክርስቲያንን የሚጎዳ ሥራ ቢሠራ ÷ ከራሱ አልፎ ሌላውንም እየጎዳ ነውና ምንም በሲኦል በገሃነም እሳት መቀጣቱ ባይቀር÷ በምድርም በሥጋው ይቀጣል:: ለዚህም እግዚአብሔር ስለ ቅዱሳኑ ሲል ነገሥታትን እንደገሰጸ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል:: መዝ 104÷14:: ይህም ማለት የሌሎችን ነጻ ፈቃድ አይጋፋ ማለት እንጂ ነጻ ፈቃዱ ጐዶሎ ነው ማለት አይደለም::

እንዲሁም የሰው ልጅ በፈቃዱ የመወለድ÷ስለ መልኩ መጠቀርና መንጣት ወይም ስለ ቁመቱ መርዘምና ማጠር÷ ወዘተ. የመወሰን ሥልጣን የለውም:: ይህም ከተሰጠው ነጻ ፈቃድ ጋር የማይገናኝ ከዐቅሙ በላይ የሆነ የእግዚአብሔር ሥራ ነውና:: ነገር ግን ምኞት እንደሆነበት ይቀራል እንጂ እንዲሆንለት ከማሰብ የሚከለክለው የለም:: በነጻ ፈቃዱ ውጤቱ ሞትም ይሁን ሕይወት ማሰብ ይችላል:: ዐቅሙ አይደለምና ያሰበውን ሁሉ ማድረግ ግን አይችልም:: ማቴ 6÷27::

በአጠቃላይ ነጻ ፈቃድ የሰው ልጅ ዋጋ ሊያገኝ /ሞት ወይም ሕይወት ሊሆን ይችላል/ ከሚፈጽማቸው ድርጊቶችና ሥራዎች ጋር የተገናኘ ነው:: ሕግጋተ እግዚአብሔር መኖሩ÷ ኃጢአትና ጽድቅ መለየቱ÷ ፍርድ /ኩነኔ ወይም ክብር/ መኖሩ ይህንን ነጻ ፈቃድ የሚያመለክቱ ናቸው:: በመሆኑም የሰው ልጅ በተሰጡት ሕግጋት መሠረት የሚጠቀመውን ከሚጎዳው÷ ጽድቅን ከኃጢአት ለይቶና መርጦ ይፈጽማል:: የሚገባውንም ዋጋ ከእግዚአብሔር ያገኛል::

እንግዲህ አንድ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ነጻ ፈቃድ ተጠቅሞ ሕይወትን መርጦ የሚኖር ሰው ነው:: በክርስትና ሕይወት ሲኖርም በነጻ ፈቃዱ የሚጠቀመውን ከሚጎዳው÷ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚበጀውን ከማይበጀው እየለየ ይኖራል:: «ሁሉ ተፈቅዶልኛል÷ ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፤ሁሉ ተፈቅዶልኛል÷ነገር ግን ሁሉ የሚያንጽ አይደለም» የሚለውን የሐዋርያውን ቃል መሠረት በማድረግ ሁሉ ቢፈቀድለትም ለሕይወቱ የሚጠቅመውን ብቻ ይፈጽማል::

1ቆሮ 10÷23:: ስለሆነም የክርስትና ሕይወት የነጻነት ሕይወት ነው:: ገላ 5÷1::

የሰው ልጆችን መጥፋት የማይፈልገው አምላክም ፈቃዱ ይኸው ነው:: በመሆኑም የሰው ልጆች በነጻ ፈቃዳቸው መልካም ሠርተው ዘላለማዊውን ሕይወት እንዲያገኙ መንገዱን ያዘጋጅላቸዋል:: ዮና 3÷10:: ሕዝ 36÷25:: «ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና÷ይህም ጸጋ÷ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን÷ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒ ታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን÷ ራሳችንን በመግዛ ትና በጽድቅም እግዚአብሔርንም በመ ምስል በአሁኑ ዘመን እንዴት እንድን ኖር ያስተምረናል፤ መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን÷ መልካሙን ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆ ነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ÷ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል» ቲቶ 2÷11–14::

## ለምን በዓለት ተመሰለ ?

*<u>ጥያቄ-2</u> በመጽሐፍ ቅዱስ 1ቆሮ.10÷2–4 ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለት/ድንጋይ/ ተመስሎ እናገኘዋለን:: ለመሆኑ ጌታችን በዓለት /ድንጋይ/ መመሰሉ ለምንድን ነው?*

<u>መልስ</u> መጽሐፍ ቅዱስ መስሎ መናገር ልማዱ ነው:: ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሊቀ ነቢያት ሙሴ የተመሰለበት ጊዜ አለ፣በነሐስ እባብ የተመሰለበት ጊዜ አለ፣በጥበብ የተመሰለበት ጊዜ አለ፣ በሙሽራም የተመሰለበት ጊዜ አለ:: ከዚህም ሌላ በሌሎችም በርካታ ምሳሌዎች ተመስሏል:: ከእነዚህም መካከል አንዱ የጌታችን በዓለት መመሰል ነው:: ቢሆንም ምሳሌ ሁል ጊዜ ከሚመስልለት ነገር ያነሰ መሆኑን ማወቅ ይገባል:: ይኸንንም አባቶች ምሳሌ ዘየሀጽጽ /ጐዶሎ ምሳሌ/ ይሉታል::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ በተለያየ ሥፍራ በዓለት ተመስሎ ይገኛል:: ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው ጠያቂያችን ያነሡት ጥቅስ ነው:: እርሱም ማኅቶተ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስ «...ሁሉም ሙሴን ይተ ባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፣ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፣ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፣ ይከተላቸው ከነበረው መንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፣ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበር::» ያለው ነው:: /1ቆሮ.10÷2–4/

ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው እስራኤል ከግብጽ ወጥተው ባሕረ ኤርትራን ተሻግረው ለአርባ ዓመት ከሰማይ የወረደ መና እየበሉ ኖረዋል:: በዚህም ጊዜ ራፊዲም በተባለው አካባቢ በሰፈሩበት ወቅት እስራኤል የሚጠጡት ውኃ አጡ:: በዚህም ምክንያት በሙሴ ላይ አንጐራጉረው «ለምንስ ከግብጽ አወጣኸን?» አሉት:: ሙሴም «ሊወግሩኝ ተቃርበዋልና ለዚህ ሕዝብ ምን ላድርግ?» ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ:: እግዚአብሔርም ሙሴን «በሕዝቡ ፊት እለፍ፣ ከእሥራኤልም ሽማግሌዎች ከአንተ ጋር ውሰድ፤ ወንዙንም የመታህበትን በትር በእጅህ ይዘሃት ሂድ:: እነሆ እኔ በዚያ በኰሬብ ዓለት ላይ በፊትህ እቆማለሁ:: ዓለቱንም ትመታለህ፣ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከእርሱ ውኃ ይወጣል አለው::» ዘጸ.17÷2–6:: ከዚያም ውኃ ሕዝቡ ሁሉ ጠጥቶረካ:: እንግዲህ ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ታሪክ አስታውሶ ነው ለቆሮንቶስ ምእመናን የጻፈላቸው::

ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ «ይከተላቸው ከነበረው መንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፤ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ፤» ያለው ያለ ምክንያት አይደለም:: እሥራኤል ዘሥጋ ከግብፅ ከባርነት ቤት ሲወጡ አንዲት ድንጋይ ይዘው ወጥተው ነበር:: እርሷም ከአሥራ ሁለት ላይ ነቅታ ለአሥራ ሁለቱ ነገድ ሁሉ ታጠጣቸው ነበር፤ ሌሊት ዓምደ ብርሃን ሁና ቀንም ዓምደ ደመና ሁና ትመራቸው ነበር:: በየደረሱበትም ያገኙዋት ስለነበር ሐዋርያው «ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፤» አለ:: /የቅዱስ ጳውሎስ ትርጓሜ ተመልከት/ እንግዲህ እሥራኤል ዘሥጋ ከዚህ ዓለት ጠጥተው እንደረኩ ሁሉ እሥራኤል ዘነፍስ ምእመናን ደግሞ ከጐኑ በፈሰሰ ውኃ ተጠምቀው፣ በመስቀል ላይ የተቆረሰ ሥጋውን በልተው፣ደሙንም ጠጥተው በነፍሳቸው በመጥገባቸውና በመርካታቸው ዓለቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ተነግሯል::

ከዚህ በተጨማሪ ጌታችንን በተለያዩ ቦታዎች በዓለት ተመስሎ እናገኘዋለን:: ዓለት በመሬት ውስጥ የተነጠፈ ትልቅ ድንጋይ ማለት ነው:: ዓለትን ከስፍራው ማነቃነቅ አይቻልም:: ኢዮ. 18÷4 እንደዚሁም ሁሉ እግዚአብሔር ወልድ በባሕርዩ ሕልፈት ውላጤ፣ በመንግሥቱ ሽረት የሌለበት በመሆኑ የዘላለም አምላክ ነው እንላለን:: ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ «እግዚአብሔር ዓለቴ አምባዬና መድኃኒቴ ነው::» ያለው ለዚህ ነው 2ሳሙ.22÷2::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመሠረት ድንጋይ እና በማዕዘን ድንጋይም ተመስሏል:: ይኸንንም በተመለከተ በነቢዩ በኢሳይያስ «እነሆ በጽዮን ድንጋይን ለመሠረት አስቀምጣለሁ ፣ የተፈተነውን ፣የከበረውን ፣መሠረቱ የጸናውን የማዕዘን ድንጋይ የሚያምንም አያፍርም::» ተብሏል:: ኢሳ.28÷16:: ይህ የመሠረት ድንጋይ የተባለ ማን እንደ ሆነም ሲነግረን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ከተመሠረተው መሠረት በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::»ሲል ተርጉሞልናል:: 1ቆሮ.3÷11

አንድ ሕንፃ ሲታነጽ በመጀመሪያ የሚሠራው መሠረቱ ነው:: መሠረቱ ደግሞ አጠቃላይ የሕንፃውን ክብደት የሚሸከም ነው:: መሠረቱ ደካማ ከሆነ ቤቱ ይፈርሳል:: ይህም በመሆኑ ምንጊዜም ቢሆን ብልህ ሰው ቤቱን የሚመሠርተው በጠንካራ መሠረት ላይ ነው:: በጠንካራ ዓለት ላይ ቤትን መሥራትም ከዝናብ፣ ከጐርፍ፣ ከነፋስና ከመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ያድናል:: ማቴ.7÷24:: እንደዚሁም ሁሉ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ሁሉ በደል የተሸከመ በመሆኑ በጽኑ የመሠረት ድንጋይ ተመስሏል:: ነቢዩ ኢሳይያስ «በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕማማችንንም ተሸከሟል::» ያለው ለዚህ ነው:: ኢሳ.53÷4::

ራሱ ጌታችንም በወንጌል «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፣ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋ ለሁ» ብሏል:: /ማቴ.11÷28/

በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማዕዘን ድንጋይ ተመስሎ ተጽፏል:: ቃሉም «ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ» ይላል:: መዝ.117÷22፣ ማቴ. 21÷42፣ 1ጴጥ.2÷5–7 ፣የሐዋ.4÷11፣ ሮሜ.9÷33:: ቅዱስ ጳው ሎስ «የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፣ በእርሱም ሕንፃ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተመቅደስ እንዲሆን ያድጋል» ብሏል:: ኤፌ.2÷21 ሕንፃ ሲገነባ በየማዕዘኑ ላይ ምሰሶ ይቀመጣል:: ይህም ከላይ ከጣራው የሚመጣውን ክብደት የሚሸከምና በተለያየ አቅጣጫ ከየማዕዘኑ የሚመጣውን ግድግዳ ደግፎ በመያዝ የሚያገጣጥም ነው::የማዕዘን ድንጋይ ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጡትን ግድግዳዎች ደግፎ እንደሚያገጣጥም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሕዝብና አሕዛብን በመስቀል አንድ አድርጓል::

ቤት ያለመሠረትና ያለ ማዕዘን ድንጋይ እንደማይጸና ሁሉ ምእመናንም ያለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጽናት ብርታት አይኖራቸውም:: «ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ» መባሉም አይሁድ ፈሪሳዊያን ጌታችንን ሥጋ በመዋሐዱ ዕሩቅ ብእሲ /አምላክነት የሌለው/ ብለው ቢንቁትም እርሱ ግን ዲያብሎስን በመስቀሉ ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶ፣ አዳምን ነፃ አውጥቶ፣ ሞትን ድል ነስቶ ሕዝብና አሕዛብን አንድ ያደረገ በኩረ ምእመናን መሆኑን ለማጠየቅ ነው::

ምነው ዲ.ዳንኤል በኢሉባቦር ጫካዎች ውስጥ በመንፈስ ወስደህ አብ ረህ የሶስናን ጭንቀት እንድንካፈል የምታደርገው ባልከፋ ነበር:: እኔ ግን በጣም እየጨነቀኝ ነው:: ባለፈው እትም 6ኛ ዓመት ቁጥር 5 ላይ እነ ዚያን የሰንበት ተማሪዎች አግኝታ ደስ ብሏት ስትዘምር ሁኔታው አሳዝኖኝ እንባዬ መጣ:: የአሁኑ ደግሞ ማለት አሰለፈች ጋብዛት ያ ኡመታ የሚሉት፣ ድመት አይጥ እንደምትጠበቅ አድፍጦ ሲጠብቅ ድንቁ የሚሉት ልጅ ጭልፊት በድንገት መጥታ ነጥቃ እንደምትሄድ እሱም ነጥቆ ሲሄድ ኧረ ስንቱ ይሄ ሁሉ ሲሆን እኔ ወዲያው ራሴን አመመኝ:: እንዴት ትሆን ብዬ ሳስብ መጨረሻው ጋር ስደርስ አልተደፈረችም የሚለውን ሳነበው ነፍሴ ገባች:: ዲ.ዳንኤል እኔ ነግሬሃለሁ ከነዚያ ከዘን ዶዎች አፍ ነጥቀህ አውጥተህ ሶስናን ለክብር ካላበቃሃት ዋ! ወርቅ በእሳት ተፈትኖ እንደሚወጣ ሁሉ እሷም ከዚህ ፈተና ወጥታ ለድል ትበቃለች:: እባክህ ስቃይዋን እያበዛህ አታስጨንቀን:: ቢቻልህ ታሪኳን ጨርስልን በመጥፎ እንዳ ይሆን አደራ:: ታሪኳ ባያምር ግን እኔጃ!.. እኛ ሴቶች ከሶስና ጥንካሬን፣ ትእግሥትን፣ የሃይማኖት ፍቅርን፣ ትኅትናን፣ አስተዋይነትን ብቻ ብዙ ነገር እንማራለን መጨረሻዋን ብቻ እግዚአብሔር አምላክ ያሳምርልን::

የወይን ሐረግ ስሜ /አ.አ/

በሶስት ተከታታይ የመጽሔቱ እትሞች የወጣው የዲ. ዳንኤል «በኢሉባቦር ጫካዎች ውስጥ» አጭር ልቦለድ ሶስናን ባለታሪክ አድርጎ አምላክ እስራኤል የማይተኛ የማያንቀላፋ ጠባቂ መሆኑን እኛነታችንን በመንፈስ እያጓጓዘ በኢሉባቦር ጫካዎች ውስጥ አስቀምጦ በዓይነ ሕሊናችን እንድናየው እያደረገን ነው:: ልበ አምላክ ዳዊት «በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉውን አልፈራም» መዝ 22 እንዳለ:: የወጣቷ መምህርት ክርስቲያናዊ ጽናትና እምነት ጥንካሬ የነብዩ ዳዊትን መልዕክት እንድናስተውል እያደረገን ነው:: እግዚአብሔር አምላክ ወጣቷ ሶስናን ከተማሪዎቿ ጋር የሚመለከበት፣ ስሙ የሚጠራበትና ቅዱስ ሥጋውና ደሙ የሚፈተትበትን ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ሲያስነሣ... ለክፉ ነገር ወደ ኋላ የማይለው ሰይጣንም ባለ ድቤ የቦረንን ቃልቻና አንዳንድ የሥራ ባልደረቦቿን በማነሣሣት በሶስና ክርስቲያናዊ ሕይወት አኗኗር ላይ የተለያዩ ፈተናዎችን ጋረጠ::

ወጣቷ መምህርት ሶስና የተደቀነባትን የጥል ፍልፎሽ መሰናክል፣ የተጋረጠባትን ጋሬጣ ትወጣ ዘንድ የእምነቷን ጥን ካሬ አይቶ በእሱ መመካቷን የሚያውቅ እግዚአብሔር በጥበቃው በቸርነቱ አሰባት:: እናም ጋሬጣዎቿን እየቀነሰ ከፊቷ ገለባ ሲያደርግ አስተዋልን:: እንግዲህ እስከ አሁን የእግዚአብሔርን ጥበቃና የሶስናን ክርስቲያናዊ ጥንካሬ አየን:: በሚቀጥለው እንዴት ይሆን?

አስራት ከበደ
/አ.አ/

# በኢሉባቦር ጫካዎች ውስጥ

የመጨረሻ ክፍል /ክፍል 4/

ዲ.ዳንኤል ክብረት

«መቼም ልጄ» አሉ:: ከሁሉም በዕድሜ ጠና ያሉት ሽማግሌ "አንቺ ለዚህ ሀገር የሠራሽውን ሥራ የማያ ደንቅ የለም:: ደግሞም ክፉ ሲነካሽ ማየትም አንወድም:: የቦረን ጌታ" አሉና ለጥቂት ጊዜ ጸጥ አሉ:: «ያለ እኔ ፈቃድ በተስኪያን አይሠራ ብለው መርገማቸውን አንቺም በጆሮሽ ሰም ተሽዋል:: አንቺ መቼም ጠንካራ ሰው ነሽ ከመጤፍ ሳትቆጥሪው ሥራሽን ቀጠልሽ:: እይውልሽ አሁን አሁን ደግሞ ይህች ልጅ ካላቆመች ሣር ልበጥስባት ነው አሉንእና ምን ይመስልሻል?»

ሁሉም ቀና ብለው በአትኩሮት ተመለከቷት:: አሳዘኗት:: ጭንቀታቸው ገብቷታል:: ግማሽ እምነት ግማሽ ፍርሃት ሲመላለስባቸው ታያት:: ባንድ በኩል ርግማኑን ፈሩ:: በሌላ በኩል እርስዋን ይወድዋታል::

«እንደው ልጄ እርሳቸው ረግመውሽ ይኼ ሁሉ በጐ ሥራ ከሚበላሽ እኛም አንቺን የመሰልሽ ልጃችንን ከምናጣ ምናለ ብናስታርቃችሁ» አሉ ሌላኛው ሽማግሌ:: ሁሉም ራሳቸውን በመስማማት ነቀነቁ::

«አባቶቼ ስለ እኔ በመጨነቃችሁ አመሰግናችኋለሁ:: ዕድሜያችሁን ያርዝምልኝ:: ርግማኑን ግን አትፍሩት:: እግዚአብሔር የመረቀውን ማንም ሊረግመው አይችልም:: ቤተ እግዚአብሔርን መሥራት የተመረቀ ሥራ፣ሠሪዎቹም ብሩካን ናቸው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ አንድ ታሪክ ልንገራችሁ:: በለዓም የተባለ ነቢይ እሥራኤላውያንን ሊረግም ባላቅ በሚባል ሰው ተመክሮ ወጣ:: መንገድ ላይ ግን የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጾ:: «እግዚአብሔር የባረከውን ልትረግመው አትችልም» በማለት ርግማኑን ወደ ምርቃት ቀየረበት»

«በኛም ላይ ይሄው ነው ሚፈጸመው:: የቦረኑ ጌታ ይርገሙን እኛ የተባረከ ሥራ ከሠራን ርግማናቸው ምርቃት ይሆናል:: ይልቅስ እየታገሉ ያሉት ከሶስና ጋር ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን ንገሩዋቸው:: እግዚአብሔርን ታግሎ ያሸነፈ የለም:: እናንተም አትደንግጡ ነገር ግን በእምነታችሁ ጽኑ»

ገርሟቸው በአድናቆት ያዩዋታል::

«በጄ ሁላችንም እንደአንቺ ጽኑ ብንሆን እንዴት መልካም ነበር» አሉ በዕድሜ ጠና ያሉት ሽማግሌ ተሰናብተዋት ሲወጡ::

በዚያው ዕለት ጉዳዩ ለቦረኑ ጌታ ደረሰው:: እንደቀትር እባብ አቅበዘበዘው:: ካዳሚዎቹ ሁሉ ደነገጡ:: ምንድነው ማድረግ የሚቻለው? አራቱ ጋሻ ጃግሬዎቹ ዙሪያውን ከብበው ተቀመጡ:: ዓይኖቹ የብረት አሎሎ መስለዋል:: እጁ እንደ ባሕር ቄጤማ ይርገፈገፋል:: አንገቱ የንፋስ አቅጣጫ መለያ መሣሪያ ይመስል ከግራ ወደቀኝ ይወዛወዛል::

«ምን ይሻላል:: ምን አፍጥጣችሁ ታዩኛላችሁ? አንባረቀባቸው:: አራቱም በግንባራቸው ተደፉ:: «ይዘዙን እንፈጽማለን»

«ሴት እንዴት ታሸንፈኝ:: የሀገር የወንዝ መሳቂያ እንዴት ታድርገኝ»

«ይዘዙን እንፈጽማለን»

«ልክ ያላገባኋት እንደሆነ እኔ አይደለሁም»

«ይዘዙን እንፈጽማለን»

«ከየትም ከየትም ብላችሁ በሦስት ቀን ውስጥ ይህችን ሰው ፊቴ እንድታቀርቡ»

«ይዘዙንን እንፈጽማለን»

✦ ✦ ✦ ✦

የሐሎ ሥላሴ የሰንበት ተማሪዎች እስከ ግማሽ መንገድ ሸኝተዋት ተመለሱ:: ከዚያ በኋላ ብቻዋን ነበረች:: ሁልጊዜም እንዲሁ ነው የምታደርገው:: ፍርሃትና እርስዋ ከተሰነባበቱ ዘመናት አልፈዋል:: ጥቅጥቅ ያለውን

የዲዲቤ ጫካ እየዘመረች ብቻዋን ማቋ
ረጡን ልማድ አድርጋዋለች:: በጸጥ
ታው ውስጥ መዘመር ደስ ያሰኛታል::
አዕዋፍ ከርስዋ ጋር ይዘምሩ ወይም
ለብቻቸው ባይታወቅም ያጅቧታል::

ከት/ቤት ሰባት ሰዓት ወጥታ
የሁለት ሰዓት መንገድ ከተጓዘች በኋላ
ነበር ሐሎ ሥላሴ የገባችው:: ከተተከለ
ከ100 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ በዕድ
ሜም በዕውቀትም የጸሰሉ አበው መና
ኸርያ ነው ሐሎ ሥላሴ:: የአካባቢው
ምእመን የሚያስገርም ሕይወት ነው
ያለው::

ለእሑድ ቅዳሴ ሲመጣ ሁሉም
ምግቡን በአገልግሉ ቋጥሮ ነው:: ቅዳ
ሴው ሲያበቃ መምህርት ሶስና ባሳየቻ
ቸው መሠረት ትምህርት ይሰጣል::
ከዚያ በኋላ የሁሉም ምግብ ተቀላቅሎ
ማዕድ ይሠራና ተባርኮ ይበላል–
አጋፔ::

ትምህርት በመውደድ የሐሎ
ሥላሴን ሕዝብ የሚወዳደረው የለም::
በእያንዳንዷ ጐጆ ውስጥ መንፈሳዊ
መጽሔቶች፣ ጋዜጦችና መጻሕፍት
አሉ:: የቻለ ያነባል:: ያልቻለ ያስነብ
ባል:: መሠረተ ትምህርትን ለጽድቅ
የተጠቀመ ሕዝብ ቢኖር የሐሎ ሕዝብ
ነው::

ወጣቶቹ በሳምንት አንድ ቀን
ሐሙስ ከሰዓት በኋላ ነው የሚማሩት::
ትምህርቱ ሲያበቃ መምህራቸውን
ግማሽ መንገድ ድረስ ጥያቄ እየጠየቁ
ይሸኙዋታል:: ከዚያ በኋላ እርስዋም
እየዘመረች ትሄዳለች:: እነርሱም እየዘ
መሩ ይመለሳሉ::

አራቱ ጋሻ ጃግሬዎች ለዓይን
ያዝ እያደረገ ባለው ምሽት ውስጥ
አድፍጠዋል:: ግዳይ ሊጥሉ:: የዝማ
ሬው ድምጽ ከሩቅ ተሰማቸው:: ያን
ቀን ተማሪዎቿን የገበሬ ማኅበሩ ለሥራ
አስፈቅዶ ወሰዷቸው ስለነበር ብቻዋን
ናት:: ባለፈው ከተፈጠረው ችግር
ወዲህ ብቻዋን ስትጓዝ የመጀመሪያዋ
ነው:: «የሕዝቡን ችግር ካላቃለልን ክር
ስቲያንነታችን የት ላይ ነው» ትላ
ቸዋለች::

የዝማሬው ድምጽ እየቀረበ
መጣ::

ጋሻ ጃግሬዎቹ ፈርተዋል::
ለነርሱ ሶስና ምትሐተኛ ናት:: ከዚህ
በፊት በሁለቱ መምህራን ላይ የሆነውን
ሰምተዋል:: እናም በእነርሱ ላይ አንድ
ምትሐት ቢወርድስ? ከዛር ክፉ ሴቲቱ
ዛር ናት እየተባለ ሲነገራቸው አድገ
ዋል:: ማን ያውቃል በርስዋ ላይ ያለ
ችው ሴቲቱ ዛር ከሆነችስ? ግን ደግሞ
የቦረኑ ጌታ ሲናገር እንደሰሙት ሴት
ዛር በወንድ ላይ እንጂ በሴት ላይ
አታድርም::

ዝማሬው አፍንጫቸው ሥር
ደረሰ::

አንዱ ሮጥ ብሎ አፏን እፍን
አደረጋት:: ሁለተኛው እጆቿን አሠረ::
የቀሩት ሁለቱ ተሸከሙዋት:: ከዚያም
ሽምጥ ጋለቡ::

የቦረኑ ጌታ ፊት ቀረበች::

ዓይኖቹ የእሳት አሎሎ መስለ
ዋል:: ግንባሩ በንዴት እየታረሰ ነው::
እንደ ቀትር እባብ ያቅበዘብዘዋል::

«እህ አንቺ ነሽ አገር የምትበ
ጠብጭው:: አሳዛኝ» እንደምትሸጥ በግ
ዙሪያዋን ዞሯት:: እጅዋ ም እግርዋም
ታሥሯል:: «ውሰድና እልፍኝ ቆልፍ
ባት»:: ተሸክመው ይዘዋት ገቡ:: የሰን
ደሉ ጢስ ቤቱን አፍኖታል:: ጫቱ
እንደ እህል ተከምሯል:: በአራት ወገን
ማሾ ይበራል:: አራቱንም ግድግዳዎች
የአራዊት ቆዳ ሸፍኖአቸዋል:: ጣራው
ቀይ ቀለም ነው የተቀባው::

አፈናትና ሊያስታውካት ደረሰ::
ኩርትም ብላ ተቀመጠች:: ሳታስበው
ዕንባዋ ፈሰሰ:: ሰውነትዋ ተቆራርጧል::
የታሠረችበት ገመድ እጅና እግርዋን
መሠርሠር ጀምሯል::

ዲቤው ቀለጠ:: ዛሩ ወረደ
ተባለ:: አካባቢው ተደበላለቀ:: ዙሪያ
ውን ለተሰበሰበው ካዳሚ የቦረኑ ጌታ
ሶስናን በነፋስ አውታር አስጭነው አመ
ጧት ተብሎ ተነገረው:: ጉድ አለ
ጉድ:: ሌሊቱን እንዲችው ሲጨፍሩ
ነው ያደሩት::

ሁለቱ ጋሻ ጃግሬዎች በእኩለ
ሌሊት በሩን በርግደው ገቡ:: ኩርትም
ብላ ትዘምራለች:: ጧ.ጧ.ጧ. ከየጐና
ቸው ጅራፋቸውን መዠለጡና እንደ
ድግስ ሙቀጫ ተራ በተራ ተረባረ
ቡባት:: ጧ.ጧ.ጧ ታሥራለች መንቀ
ሳቀስ አልቻለችም:: ልብስዋን ዘልቆ
ገላዋን መተልተል ጀምሯል:: እጃቸው
እስኪዝል ገርፈዋት ወጡ::

ዕንባዋ መንታ መንታ ሆኖ
ይወርዳል:: «የሠራዊት ጌታ ልዑል
እግዚአብሔር ሆይ ሶስናን ከረበናት
እጅ፣ዳንኤልን ከአንበሳ ጉድጓድ
ሠለስቱ ደቂቅን ከእቶን እሳት እን
ዳወጣህ አውጣኝ» አለች ሶስና:: «ስለ
እኔ ስለባርያህ ሳይሆን ስለ የዋሐን ሕዝ
ብህ ስትል አሳልፈህ አትስጠኝ» ስቅስቅ
ብላ አለቀሰች:: የቁስሉ ጥዝጣዜ ሰላም
ነሣት:: ስቃዩ ከዐቅሟ በላይ ሆነ::

መሬቱ ድው ድው አለ::
እርም እርም

«ስለ ኃጢአቴ እኔን ብቻዬን
ቅጣኝ ሕዝብህን ግን አድን:: ገና
በእምነት ያልጠነከሩ ልጆችህን ታደግ::
ዲያብሎስ ደስ አይበለው:: መከራው
ከብዶኝ እንዳልሸነፍ:: እመብርሃን
የጭንቅ አማላጅዋ ታውቂበት የለም
ሰውን ከመከራ ማዳን... እባክሽን አትር
ሺኝ...አባቶቻችን ያስተ...ማሩን ታሪክ..
ዛሬ በእኔም ላይ ይፈጸም... ለጠላት
አሳልፈሽ አትስጭኝ...አደራ ድንግል
አደራ

አደራ ድንግል አደራ
በፈተና ጊዜ ሥጋዬ እንዳይፈራ
አደራ ድንግል አደራ
አደራ ድንግል አደራ
ሰይጣንን ድል ነሥተሺ
አውጭኝ ከመከራ
አደራ ድንግል አደራ»

ዕንባ የተቀላቀለው ከትኩስ
ልብ የሚወጣ መዝሙር:: መሬቱ ድው
ድው አለ:: የቦረኑ ጌታ ከአራቱ ጋሻ
ጃግሬዎቹ ጋር ገባ::

«ምን እንደ ድንቢጥ ይሸጉ
ጥሻል?» አለ አንዱ ጋሻ ጃግሬ ጐትቶ
መሐል አደረጋት:: «በል ያዘዝኩህን
አምጣ» አለ የቦረኑ ጌታ: አንዱ ጋሻ
ጃግሬ ሮጥ ብሎ ወጣ::

አንድ ገበታ ፊቷ ቀረበ:: የቦ
ረን ጌታ አኝኮ የተፋው ጫት::

የቦረን ሕዝብ ሲሸበር አመሸ::
ሶስና የት ጠፋች:: ወጣቶቹ ያለቅሳሉ::
የሐሎን መንገድ በባትሪ በችቦ በጧፍ
ያምሱት ጀመር:: የሁለት ሰዓቱ መን
ገድ እጥፍ ወሰደ:: ሶስና ግን የለችም::
ገና በጊዜ ነው የሸኙዋት:: የት ገባች?

ዑዑታው ከመንደር መንደር
እየተቀባበለ ደረሰ:: መምህርት ሶስና
ጠፋች:: አውሬ ይብላት መከራ ያግ
ኛት አልታወቀም:: አሳሾቹ በመጨረሻ
ወደ ቦረን ጌታ ዘንድ አመሩ::

ያን ጊዜ ነው አብዛኞቹ የደነ
ገጡት:: የቦረን ጌታ በአራቱ የነፋስ
አውታራት አስጭኖ ሶስናን ወስዶ
አታል:: ካዳሚው በሙሉ የሚያወራው
ይኼንኑ ነው:: ዕጢያቸው ዱብ አለ::
ከነፋስ አውታር ማን ያመልጣል::
ጭንቅ ሆነ::

«ድሮም ተይ ስንላት አልሰማ
ብላ ነው» አሉ ሁለት ሽማግሌዎች::
«ምናለ ሴት ናት በዐቅሟ ብትኖር»
አንዳንድ ባልቴቶች ተማረሩ:: ታዲያ
አሁን ምን ይሻላል::የሰንበት ተማሪዎቹ
ልባቸው በንዴት ጦፏል:: በነፋስ አው
ታር የሚለው ወሬ ሊዋጥላቸው ቀርቶ
ከንፈራቸው ላይ አልደረሰም::

ጨብ ጨብ ጨብ
ጋሻ ጃግሬው ከፍ ያለ ድንጋይ ላይ
ወጣ::

«ቦረን ስማ ተብለሃል:: የሶስ
ናን ነገር ነገ ታየዋለህ አሁን በሰላም
ወደ ቤትህ ግባ:: ያለበለዚያ በርስዋ
የደረሰ ባንተም ይደገማል:: ተብለሃል»

ጥቂቱ አማን ብሎ ሰገደና
ጉዞውን አቀና ወጣቶቹና የኪዳነ ምሕ
ረት ጉባኤ አባላት የሆኑ ጐልማሶችና
ሽማግሌዎች ግን ወደ ኋላ ቀሩ:: ምን
እናድርግ? በመጨረሻ ሽማግሌዎቹ
ወደ ሠፈር ተመልሰው ሕዝቡን እንዲ
ያረጋጉ ተወሰነ:: ጐልማሶቹና ወጣቶቹ
ደግሞ ከቦረን ጌታ ግቢ ራቅ ብለው
እሳት አንድደው ተቀመጡ::

ዕንባዋ ቀጥ አለ:: በጠላት
ፊት ማልቀስ ለዲያብሎስ የልብ ልብ
መስጠት ነው፤ሕመሙዋን ቻለችው
ስቃይዋን አመቀችው:: ጋሻ ጃግሬው
ጫቱን በእጁ ጠቀለለና ሊያጐርሳት
ቀረበ:: ልታማትብ አሰበች ነገር ግን
እጅዋ ታስሯል:: ያን ጊዜ ነው ታላቁ
ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ ትዝ ያላት::

እጅና እግሩ በታሠረ ጊዜ እንዴት እንዳ ማተበ:: በአገጭዋ አማተበች:: ውስጥዋ ደግሞ ጸሎተ ማርያምን እየደገመ ነበር:: ከሩቅ የእግዚእታ ድምጽ ይሰማታል::

«አጉርሳት እንጂ» የቦረኑ ጌታ እንደ ነጐድጓድ ጮኸ

«እሺ» አለ ጋሻ ጃግሬው ጠጋ አለ:: መልሶ ደግሞ ቆመ:: የቦረኑ ጌታ አንገቱን አነቀና ወረወረው:: «ተነሥ አን ተኛው» ሁለተኛውን ጋሻ ጃግሬ አዘዘ:: «አንሣና አጉርሳት»::

የተቆጣ ዓይን፣ ኰስታራ ግንባር የተረጋጋ ልብ ከፊቱ ተደቀነ:: ጠጋ አለ ሊያጐርሳት:: አማተበች:: ውስጥዋ ደግሞ ጸሎተ ማርያምን ይደግማል:: የቦረኑ ጌታ እንደ ጥይት ተተኰሶ ተነሣ:: ጋሻ ጃግሬው እንደአጐነበሰ ቀረ:: እርሱንም አሽቀንጥሮ ጣለው::

በመጨረሻ ራሱ ገባበት «አስ ማታም» አለና ጮኸ::

ውዳሴሃ ለእግዝእትነ ማርያም
ድንግል ወላዲተ አምላክ
ዘይትነበብ በዕለተ ዓርብ:: ቡር
ክት አንቲ እምአንስት
ወቡሩክ ፍሬ ከርስኪ:: ኦ ማር
ያም ድንግል ወላዲተ አምላክ
ዘእንበለ ርኩስ:: ሠረቀ ለነ እም
ኔኪ ፀሐየ ጽድቅ
ወአቅረበነ ታኅተ ክነፊሁ:: እስመ
ውእቱ ፈጠረነ:: ሰአሊ ለነ ቅድስት::

ሶስና ድምጽዋን ከፍ አድረጋ ውዳሴ ማርያም መድገም ጀመረች:: ከውጭ የእግዚእታ ድምጽ ይሰማታል::

የቦረኑ ጌታ ወደቀ

ለኪ ለባሕቲትኪ ኦ እግዝእትነ ወላዲተ አምላክ እሙ ለብርሃን አንቲ ናዐብየኪ በስብሐት ወበ ውዳሴ

የቦረኑ ጌታ ዐረፋ መድፈቅ ጀመረ::

ቡርክት አንቲ ተዐብዩ እም ሰማይ ወትከብሪ እምድር ወላዕለ ኩሉ ኅሊናት መኑ ዘይክል ነቢበ ዕበየኪ:: ወአልቦ ዘይመስል ኪያኪ:: ኦ ማርያም መላእክት ይዐብዩኪ:: ወ ሱራፌል ይሴ ብሑኪ::

አራቱ ጋሻ ጃግሬዎች ይንቀጠ ቀጣሉ::

እስመ ዘይነብር ዲበ ኪሩቤል ወሱራፌል መጽአ ወኀደረ ውስተ ከር ስኪ:: መፍቀሬ ሰብእ አፍቀርነ ኅቤሁ ዘዚአነ ሞተ ነሥአ ወእንቲአሁ ሕይወተ ወሀበነ::

ተቃጠልኩ ተቃጠልኩ ዑ ዑ ዑ ዑ የቦረኑ ጌታ እሪታውን አቀለጠው:: እንደ እንዝርት መሬት ላይ ተሽከረከረ:: አራቱ ጋሻ ጃግሬዎቹ ተከ ተሉት:: ከሥጋ እንደወጣ ትል መሬት ላይ ተተራመሱ:: ዑ ዑ ዑ ዑ ዑ ዑ ዑ

ዘለዉቱ ክብር ወስብሐት ሰአሊ ለነ ቅድስት::

ካዳሚዎቹ እየተንጋጉ ሲመጡ ተሰማት:: የእግዚእታውም ድምጽ እያየለ ነው::

ስምዐነ አምላክነ ወመድኃኒነ
ስምዐነ አምላክነ ወመድኃኒነ

በሩ ተከፈተ:: ካዳሚዎቹ ተን ጋግተው ገቡ:: የቦረኑ ጌታ ከነጋሻ ጃግሬዎቹ ይጮኻሉ፤ ዐረፋ ይደፍቃሉ:: ይሽከረከራሉ:: ተቃጠልን:: ነደድን ዑ ዑ ዑ ዑ ዑ

በነፋስ አውታር ተጭና መጣች የተባለችው ሴት ደግሞ እጅና እግርዋ ታሥሮ እንዲህ ትላለች::

ቡርክት አንቲ ማርያም ወቡ ርክ ፍሬ ከርስኪ:: ኦ ድንግል ወላዲተ አምላክ ምክሐን ለደናግል::

ካዳሚዎቹ በፍርሃት መንቀጥቀጥ ጀመሩ:: ሶስና ውዳሴ ማርያምን ጨርሳ ይዌድስዋ መላእክትን መጸለይ ስትጀምር የቦረኑ ጌታና ጋሻ ጃግሬዎቹ የሞቱ ያህል በድን ሆኑ:: ጸጥ ረጭ:: ፈንግል እንደያዘው ዶሮ በያሉበት ክል ትው ክልትው አሉ::

እንደቸርነትህ አቤቱ ማረን::

የውጩ ጸሎት እያለቀ ነው:: ሶስና ጸሎቷን ጨረሰች:: በሩጋ የቆመውን ጐረምሳ «ና ፍታኝ» አለችው ሶስና:: ፈርቶ አፍጥጦ ያያት ጀመር:: «ምንም አትሆንም ና ፍታኝ» መሄዱም መቅረቱም አስጨ ነቀው ለሦስተኛ ጊዜ «ና» ስትለው እግሩን እየጐተተ ወደ ርስዋ አመራና ፈታት:: «በውጭ የቆማችሁ ግቡ» አለች ሶስና:: የቤቱ ወለል እስኪሸፈን ድረስ በሰው ተሞላ::

«እኔና እናንተን የፈጠረን እግዚአብሔር ነው:: እስከ ዛሬ ስትሰ ግዱ የኖራችሁት ግን ለሰይጣን ነው:: እነዚህ ሰዎች የሰይጣን ማደርያዎች ናቸው:: ምንም ኃይል የላቸውም አትፍሩ:: እኔን እዚህ ቦታ ያመጡኝ ከመንገድ ጠልፈው እንጂ በነፋስ ጭነው አይደለም፤እናንተም ሰው ናችሁ እነርሱም ሰዎች ናቸው:: ለምን ድነው የምትፈሩዋቸው? ለምንድነው እንደ እግዚአብሔር የምትቆጥሯቸው? እና ንተ ተርባችሁ ለነርሱ ቅቤ ታመጣላችሁ:: እናንተ ተጠምታችሁ ለነርሱ ጠጅ ትቀዳ ላችሁ:: ለምን ሞኝ ትሆና ላችሁ?»

«እነዚህ ሰዎች እስከ ዛሬ ሲያታ ልሉ ኖረዋል:: ያላደረጉትን አድ ርገናል የማያደርጉትን እናደርጋለን እያሉ:: ሁሉን ማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው» ሶስና ወደ አምስቱ ሰዎች እየጠቆመች ማስተማርዋን ቀጠለች:: ሁሉም ደንግጠ ዋል:: ገርሟቸ ዋል:: ተአምር ሆኖባቸዋል::

የእግዚእታው ድምጽ ጸጥ አለ::

የቦረኑ ጌታ ከተጋደመበት ተነሣ:: ነገር ዓለሙ ዞረበትና መልሶ መሬት ያዘ:: ዙሪያውን በሰው ተከቧል:: ሶስና ቆማለች:: ጋሻ ጃግሬዎቹ በየአቅጣጫው ተጋድመዋል:: ሲነሣ ትከሻው ቀለለው:: ጭንቅላቱ ያነሠ እግሩ የተከረከመ ሰውነቱ የተፋቀ መስሎ ተሰማው::

«የቦረን ጌታ አሁንም እግዚ አብሔርን አትፈራም:: አሁንም የያዘህ ሰይጣን አልለቀቀህም» ሶስና ትክ ብላ አየችው ጸጥ አለ የቦረኑ ጌታ:: ጸጥ አለ::

ዓይኖቹ ደብዝዘዋል:: ግንባሩ በላ በት ተሞልቷል:: እጆቹ ይንቀጠቀጣሉ:: ኰስሷል የቦረኑ ጌታ::

«ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ያሸ ነፈ ማነው? የእግዚአብሔር ቤት እንዳይሠራ ለመከልከል ሥልጣን ያለው ፍጡር ማነው?» ሶስና አንድ ጊዜ ወደርሱ ሌላ ጊዜ ወደ ሕዝቡ ተመለከተች:: ይጠ ዘጥዛት የነበረው ቁስል እየጠፋ እየጠፋ መጣ::

ጨለማው በንጋት እየተተካ መጣ

አራቱ ጋሻ ጃግሬዎች አንገታ ቸውን ደፍተው እንደተቆጡት ልጅ መሬት መሬት ያያሉ::

«የቦረን ጌታ እስኪ አሁን እንኳን እውነቱን ተናገር? አንተ ከእግዚአብሔር ትበልጣለህ?» ሶስና ጠየቀችው::

«አ..ል.በ..ል..ጥ..ም»

«ለመሆኑ እኔን በነፋስ አው ታር ነው ያመጣችሁኝ ተናገሩ እስኪ?» ጋሻ ጃግሬዎቹ ጸጥ አሉ::

ሕዝቡ ደንግጧል:: የቦረን ጌታ ተሸነፈ::

«እኛ..ነን..ያመጣን...» አጠገ ብዋ የቆመው ጋሻ ጃግሬ መናገር ጀመረ:: ሕዝቡ አንገቱን ደፋ::

«አታላዮች» አሉ አንድ ሽማግሌ:: ድንገት ተናደው:: ሊማቱ ዱላቸውን ሲሰ ነዝሩ ከፊት ያለው ሰው ያዛቸው::

የቦረን የሰንበት ተማሪዎች ጨለማው ለንጋት ቦታውን ሲለቅ እየዘመሩ ወደ ቦረን ጌታ ግቢ መጡ:: ሐሳባቸው በሩ አጠገብ ቆመው ሲዘ ምሩ መዋል ነው:: እዚያ ለተሰበሰበው ሰው ስለ ቦረኑ ጌታ ሊነግሩት ነው::

ግቢው ግን ጸጥ ብሎ ነበር::

«እንግባ» አለ አንዱ:: ጥቂት ቆም አሉና ተከታትለው ገቡ:: ግቢው ጸጥ ብሏል:: ወደ ቤት ዘለቁ:: አሁንም ሰው የለም አዳራሹን አልፈው ገቡ ሰው ተሰብስቧል::ግን ጸጥታ ነግሦአል:: አንዱን ጠጋ ብለው «ምንድነው?» ሲሉ ጠየቁት::

«እረ ጉድ ነው?» አላቸው:: የቆመውን ሰው እየሰነጠቁ ወደ መሐል ገሠገሡ.

እውነትም ጉድ ነው::

የቦረኑ ጌታ ከነጋሻ ጃግሬዎቹ ለፍርድ እንደሚቀርብ ወንጀለኛ ተከበው ቆመዋል:: ሶስና ለቆመው ሕዘብ እያስ ተማረች ነው::

ድንገት አካባቢው በዝማሬ ተናወጠ::

በጠላታችን ላይ ኃይልን ለሚሰጠን
በድንቅ ጥበቡ ከሞት ለሚያወጣን

ለልዑል እግዚአብሔር እንዘምራለን
ጠላታችን ይፈር አንወድቅም
ፈጽሞ
ወደቁ ከንባል ያነሣናል ደግሞ::
የእመቤታችንን ሥዕል ከፍ
አድርገው ቤቱን በዝማሬ አናወጡት::
እንዲህም ሆነ

የቦረኑ ጌታ በቅሎ ባማረ ምንጣፍ አጌጠ ች:: የእመቤታችን ሥዕል ከኰርቻው ላይ መደገፊያ ተሠርቶላት ተቀመጠች:: እልፍኝ ውስጥ የነበረው ጧፍ ወጣ:: ግራና ቀኝ መዘምራን ጧፋቸውን እያበሩ በቅሎዋን አጀቡዋት:: የጥንቆላ ዕቃዎች በሳጥን ተሞልተው በገመድ በበቅሎዋ እንዲጐተቱ ሆነው ታሠሩ::

የቦረን ጌታ በቅሎዋን እየሳበ ጉዞ ወደ ኪዳነ ምሕረት:: ቤቱ ባዶውን ቀረ:: ካዳሚዎቹ ሁሉ አጃቢዎች ሆኑ:: የቦረን ሕዝብ የዝማሬውንና የዕልልታውን ድምጽ ሊሰማ ሶስና ተገኝች እያለ ከየቤቱ ድምፁን ወደሰማበት ቦታ ገሠገሠ:: ያየው ታሪክ ግን ያልጠበቀው ያላሰበው ነበር:: የቦረን ጌታ ተሸነፈ:: በምትኩ እመቤታችን በበቅሎው ላይ ተቀመጠች:: እነሆ እርሱም ሰው መሆኑን አወቀ:: ለርስዋ ተዋረደ:: ከእግ ዚአብሔር ጋር ታግሎ ያሸነፈ ማነው?

ልዩ የሆነ ማለዳ ::

ተፈጸመ::

# እናስተዋውቃችሁ


# አባ ጀሮም

*ለእረፍቱ*

ጀሮም «ና» ተባለ
በዓቱ ጭሮ አለ
አትሮንስ ባዶ ዋለ
ፀሐይ ግርዶሽ ዋጣት
ጭጋግ ተዘበበ
በቤተልሔም ግራ
ጽልመት አረበበ
ሰማይ ደረት መታ
ዕንባ እያዝነበ ::

የተባለለት ቅዱስ አባት አባ ጀሮም /በፓኖኒያ /ድልማጥያ/ ስትሪዶን በሚባል ሥፍራ ከባለፀጋ ቤተሰቦቹ በ345 ዓ.ም. ተወለደ:: አባቱ እና እናቱ ክርስቲያኖች ቢሆኑም ጀሮም በልጅነቱ አልተጠመቀም ነበር:: ይሁንና በክርስቲያን ወላጆቹ ግፊትና መነሣሣት ጀሮም በዘመኑ ይሰጥ የነበረውን የሰዋስው ትምህርት በሚገባ እያጠና አድጓል:: አባ ጀሮም ዕድሜው ከፍ ሲል ከቅርብ ጓደኛው ከቦንሰስ ጋር በመሆን ወደሮም አቅንቶ የንግግርን ጥበብ አጠና::

አባ ጀሮም በ366 ዓ.ም. በአንድ የሰንበት ቀን ከሌሎች ክርስቲያን ጓደኞቹ ጋር በመሆን በግበበ ምድር /Catacomb/ ውስጥ የሚገኘውን የሰማዕታት መቃብር ሊጐበኝ ሄደ:: ለአንዲቷ እምነት ሲሉ ከአናብስት ጋር ታግለው በሰማዕትነት ያለፉትን የቅዱሳን መቃብር ከጐበኘ በኋላ ስለእሷ ሲሉ ነፍሳቸውን አሳልፈው የሰጡላትን እምነት እሱም ተቀብሎ የቻለውን ሁሉ ሊያደርግ ወሰነ:: ጊዜ ሳይወስድም በዘመኑ በነበረው ጳጳስ ተጠመቀ ፀጋ መንፈስ ቅዱስንና የእግዚአብሔርን ልጅነት አገኘ:: ክርስትናን መስማት ብቻ ሳይሆን ይኖረውም ጀመረ:: ከዚያም ቀድሞ የንግግርን ጥበብ እንዲማር ምክንያት ከሆነው ጓደኛው ከቦንሰስ ጋር በመሆን ሮማን ትቶ ወደ ጐል ተጓዘ::




አባ ጀሮም በሮም የተቀበለውን ክርስትና አጠንክሮ በመያዝ የራሱን መዳን ብቻ ሳያስብ ሌሎችም ክርስትናን እንዲያውቋት ዐውቀውም እንዲኖሩባት ማስተማር ጀመረ:: ከሚያስተምርባቸውም መንገዶች አንዱ ወደኋላ ይበልጥ በታወቀበት ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተር ጐም ነበር:: ወደ ቨልጌት ቋንቋ የተረጐመው ትንቢተ አብድዩ በምሳሌነት ይጠቀሳል::

አባ ጀሮም ከጓደኛው ቦንሰስ ጋር በጐል ወይም በቤተልሔም ዋሻ ለዓመታት ከቆዩ በኋላ በ373 ዓ.ም. ወደመካከለኛው ምሥራቅ አቀና:: ነገር ግን እሱና ጓደኛው ቦንሰስ አንድ ላይ የጀመሩትን ጉዞ አንድ ላይ አልጨረሱትም:: ረጅሙን ጉዞ ተጉዘው አድሪያቲክ ደሴት ሲደርሱ ቦንሰስ በዚያች አገር በብህትውና ቀሪ የሕይወት ዘመኑን ሊያሳልፍ ተለየው:: አባ ጀሮም ግን የጀመረውን ጉዞ ሳያቆም ተርሴስን፣ጳንጦስን፣ቢታንያንና ገላትያን ጐብኝቶ ኢየሩሳሌም ደረሰ:: ነገር ግን ኢየሩሳሌም እንደደረሰ በፀና ታመመ::

ወራቱ ክርስቲያኖች የሁዳዴን ጾም የያዙበት ነበር:: አባ ጀሮም ካሕመሙ የተነሣ አልጋው ላይ ተኝቶ በዘመኑ በኑፋቄ ፍልስፍናው ስሙ ገኖ የነበረውን የሲሴሮን የፍልስፍና መጽሐፍ ያነብ ነበር:: ጀሮም ካለው የማንበብ ፍቅር የተነሣ የሲሴሮን የፍልስፍና መጽሐፍ ቢያነብም ፀረ ሲሴሮአዊ አቋም እንዲኖረው ያደረገ ራእይ በዚያው ምሽት ተገለጠለት:: ጀሮም በመልእክቱ ስለራእዩ ሲያስታውስ እንዲህ ብሏል::

«በመንፈስ ወደፍርድ ወንበርና ወደፈራጁ ቀረብሁ:: በዚያም ያለው ብርሃን ኃያል ነበር:: በዙሪያው ያሉትም የሚያበሩ ነበሩ:: ወዲያውም እንዳቀረቀርሁ፤ «ማነህ?» ተብዬ ተጠየቅሁ:: «ክርስቲያን ነኝ» ብዬ መለስሁ:: ነገር ግን በፍርድ ወንበር ላይ የተቀመጠው «አንተ ዋሾ! አንተ የሲሴሮ እንጂ የክርስቶስ ተከታይ አይደለህም፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና» ብሎ መለሰልኝ:: የምናገረው አጥቼ ዲዳ ሆኜ ሳለ ፈራጁ ወደፍዳ እንድሄድ አዘዘ:: በሕመም ውስጥ ሆኜ በሲኦል ውስጥ ማን ያመሰግንሃል? የሚለውን የዳዊትን መዝሙር አሰብኩ:: «ማረኝ ጌታ ሆይ ማረኝ» ብዬ ጮህኩ:: በመጨረሻም በዚያ የቆሙት ከፈራጁ እግር ስር ወድቀው ስለብላቴናነቱ እንዲያዝንለት ስህተቱን የሚፍቅበትን ጊዜ እንዲሰጠው ለመኑለት:: ዳግመኛም የአሕዛብ ሥራዎችን ካነበብሁ ግን ፍዳውን እንዲመልስበት ነገሩት:: እኔም «ጌታ ሆይ ከእንግዲህ ዳግመኛ የዓለማውያንን መጻሕፍት የራሴ ካደረግሁ፣ ካነበብሁ ክጄሀለሁ» ብዬ ቃል ገባሁ:: ወዲያውም ወደነበርኩበት ተመለስሁ»

አባ ጀሮም ከዚህ ፀረ ሲሴሮ ራእዩ በኋላ ጊዜ ሳያጠፋ ጓደኛውን አድሪያቲክ ደሴት ላይ እንዲቀር ያደረገውን የብሕትውና ሕይወት እንዲኖረው ቆረጠ:: ውሳኔውን በተግባር ሊያውልም በምሥራቅ አንጾኪያ ወደሚገኘውና በርከት ያሉ መነኮሳት ወደሚኖሩበት የቻሊክስ ምድረ በዳ ተጓዘ:: ለመኖር ለገዳሙ አበምኔት ለቴዎዶስዮስ እንዲቀበለው ልመና አቀረበ:: አባ ጀሮም ለጥያቄው የአሽታ መልስ አግኝቶ የገ ጾም ሕይወቱን ጀመረ::

ይህ ቅዱስ በጀመረው ሕይወት ፀንቶ ከ374 ዓ.ም. እስከ 379 ዓ.ም. ድረስ ቆየ:: በአምስት ዓመት ቆይታውም በልዩ ልዩ ከተሞች ከሚገኙ የሃይማኖት አባቶች ጋር መልእክ

ታትን በጽሑፍ ይለዋወጥ፣መጻሕፍትንም ይጽፍ ነበር:: ከዚያም ጋር አብሮት ይኖር የነበረና ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት አይሁዳዊ ከነበረ ባሕታዊ የዕብራይስጥን ቋንቋ አጠና:: ይሁንና አባ ጄሮም በ380 ዓ.ም. ባዕቱን ለቆ በመውጣት አቡሊናርዮስ ወደተወገዘበት ወደ ቁስ ጥንጥኒያ በመሄድ ከጎርጎርዮስ ዘእንዚ ናዙ ቅዱሳት መጻሕፍትን አጠና:: ከዚ ያም በ381 ዓ.ም. ወደሮም ተመልሶ በወቅቱ የነበረው ጳጳስ ዳማስስ ስለ ትምህርተ መለኮት ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን እየጠየቀው እስከ 385 ዓ.ም. ድረስ በደብዳቤም በቃልም መልስ ሰጥቶታል::

በዚያ ወቅት በተለይ ሄልቪድየስ ተነሥቶ «ቅድስት ማርያም ክርስቶስን ከወለደች በኋላ ዮሴፍን አግብታ ልጆች ወልዳለች» የሚለ ውን የኑፋቄ ትምህርት ያስተምር ነበር:: ጄሮም የሄልቪድየስን ሥራ ካየ በኋላ ራሱ ሄልቪድየስ ያነሣቸውን ጥቅሶች ይዞ «የቅድስት ድንግል ማርያም ዘላለማዊ ድንግልና» በሚል ርዕስ ጠንካራ መልስ ጻፈ::

አባ ጄሮም ሌሎችም መሰል መልሶች ለየመናፍቃኑ በመስጠት ላይ እያለ በዳማሰስ መንበር ሲራሲየስ ተተካ:: ይሁን እንጂ ሲራሲየስ ለአባ ጄሮም የሚበጅ ሰው አልነበረም:: ብዙዎቹ የጄሮም ጠላቶች ጄሮም በጳጳሱ እንዲ ጠላ ስላደረጉት ሲራሲየስ ጄሮምን እንደባላንጣ ያየው ገባ::

አንድ ቀን ብላሴላ የተባለችው የጄሮም ደቀመዝሙር ታርፋለች:: ሕዝቡ ብላሴላን የገደላት አስቸጋሪው የምንኩስና ሕይወት ነው በማለት በዚያ በሚኖሩ መነኮሳት በተለይ በአባ ጄሮም አንጐራጐሩበት:: በዚህ ጊዜ ጄሮም ሮማን እስከወዲያኛው ተሰናብቶ ወደ ፓላስ ፍልስ ጥኤም ምድር አፈገፈገ:: ከዚያም ወደ ቤተ ልሔም ተጉዞ በዚያ ከሕይወቱ የቀረውን 34 ዓመታት ያሳለፈበትን ገዳም በ386 ዓ.ም. መሠረተ:: ለዚያም ጳውላ የተባለች እንስት የነበራትን ሀብት ሁሉ ሽጣ ደግ ፋዋለች::

ከልዩ ልዩ የዓለም ክፍላት ወደቅድስቲቱ አገር የሚመጡ መናንያን የሚኖሩበትና ሲያርፉም የሚቀበሩበት ቦታ ተዘጋጅቶ ለወንድ መናንያን አበምኔት አባ ጄሮም ለመናንያቱ እመምኔት ደግሞ ቅድስት ጳውላ ሆነው አዲስ ገዳማዊ ሕይወት ጀመሩ:: አባ ጄሮም በልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት በተከበበው በአቱ ውስጥ ሲኖር ጐመንና ዳቦ ብቻ እየተመገበ ነበር:: በገዳሙ ለሚኖሩ መነኮሳት ዘወትር ቅዱሳት መጻሕፍትን እየገለጠ ያስተምራቸው ነበር:: ሴልፔስየስ የተባለ መንፈሳዊ ወንድሙ ስለሱ ሲናገር ሁል ጊዜ በንባብና በጽሑፍ ተመስጦ እንደ ኖረ ሌት ተቀን እረፍት እንዳል ነበረው ይናገራል:: አባ ጄሮም የልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉሞችን፣የመናፍቃን ምላሾችንና መጻሕፍትን ጽፏል::

አባ ጄሮም በሕይወት ዘመኑ ግልጽና የማያዳግም ምላሽ ከሰጣቸው መናፍቃን፤ መካከል ሮማዊ ባሕታዊ ለነበረውና በኋላ ቆቡን ወርውሮ ድንግልና፣ጋብቻ ጋለሞታነት በእምነትና በፍርሃት ከኖሩ ባቸው በእግዚአብሔር ዘንድ እኩል ናቸው፣እንዲሁም መብላትና መጾም ከምስጋና ጋር ከሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ልዩነት የላቸውም ብሎ ላስ ተማረው ጂቪኒያን አንዱ ነው:: በዚህ መናፍቅ ስብከት ብዙዎቹ ተመስጠው ድንግልና ሕይወታቸውን በመተው እስከ ማግባት ደርሰው የነበረ ቢሆንም አባ ጄሮም በ393 ዓ.ም. በጻፈው ሁለት ቅጽ ምላሽ የተሳሳቱት ንስሐ እንዲገቡ ያልተሳሳቱት ደግሞ እንዲጸኑ አድር ጓቸዋል::

ሌላው አባ ጄሮም መልስ የሰጠው መናፍቅ ደግሞ አርጌንስ /orgien/ ይባላል:: አርጌንስ ከኑፋቄያዊ ትምህርቶቹ ሰይጣን ወደቀደመ ክብሩ ተመልሷል፣በሥላሴ መካከል የሥልጣን ተዋረድ አለ የሚሉት ይገኙበት ነበር:: ነገር ግን አባ ጄሮም ለእነዚህና ለሌሎችም የአርጌስ የኑፋቄ ትምህርቶች ጠንካራ መልስ ሰጥቶ እንዲ ወገዝ አድርጓል::

ለአብነት ያህል ከላይ የተጠቀሱትን መናፍቃን አቀረብን እንጂ አባ ጄሮም በዘመኑ ተነሥተው ለነበሩ በርካታ መናፍቃን የሚገባቸውን መልስ እየሰጠ ምእመናንን ታድጓል::

ከ405 እስከ 420 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት የአባ ጄሮም የመጨረሻ የሕይወት ዘመናት እንደመሆናቸው መጠን ያሳለፋቸው በከባድ ጉስቁልናና ችግር ነበር:: ብቸኝነት፣ደዌና፣ድህነት የማይለዩት ባልንጀሮቹ ነበሩ:: ሰውነቱ ደክመ፣የዓይኑ የማየት ኃይል እየቀነሰ መጣ ጠላቶቹም በየአቅጣጫው ተነሡበት:: ወቅቱ አረመኔዎቹ ወራሪዎች ባርባሪያንስ የሮማን ግዛት እንደደራሽ ውኃ ያጥለቀለቁበት ነበርና ስደተኞች ከሮም በሕመም ተይዞ ይኖርበት ወደ ነበረች ቤተልሔም ሲጐርፉ ሲያይ እጅግ ያዝን ነበር::

ይህ ታላቅ የቤተክርስቲያን አባት መስከረም 20 ቀን 420 ዓ.ም. አርፎ እነ ጳውላና ሌሎች ደቀመዛሙርቱ ከተቀበ ሩበት ቦታ ቢቀበርም ከጊዜ በኋላ አጽሙ ወደሮማ ተወስዶ በቅድስት ማርያም /ሳንታማርያ/ ቅጥር ውስጥ እንዳረፈ ተጽ ፏል::

*ምንጭ* *st.Jerome*

✠ ✠ ✠

## ሥራ ፈትነት...

ከገጽ 28 የዞረ

ሕንፃዎች...አባቶቻችን ምን ያህል ሥራ ወዳዶችና ታታሪዎች እንደነበሩ የሚያመለክቱ ናቸው:: የዘመኑ ችግር ያለፉትን አባቶች ታሪክ እያስታወሱ እነርሱን ሆኖ አለመገኘት ነው:: ከስንፍና የተነሣ እንኳን አዲስ ሊሠራ÷ እነርሱ ያቆዩልንን እንኳን መጠበቅ ተስኖናል::

እንግዲህ የሥራ ባሕል መጥፋትና የስንፍና መንገሥ ከላይ የተዘረዘሩትን ዓይነት ሥራፈቶችና የስም ሠራተኞች እንዲበዙ አድርጓቸዋል:: እንግዲህ ሥራ ፈትነት የወቅቱ የሕዝባችን ማኅበራዊ ችግር ከመሆኑ የተነሣም ብዙዎችን ሠርተው ከማደር ይልቅ በወጣትነታቸው ጡረተኞች ሆነው በሌሎች ገቢ ላይ ተንጠልጥለው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል:: አገራችንንም ወደኋላ እንድትጓዝ፣ሁልጊዜም ከተበዳሪዎችና ከተረጂዎች መዝገብ ውስጥ እንዳትወጣ አድርጓታል::

በመሠረቱ ሥራ ፈትነት እንደየአገሩ ሁኔታ የተለያየ ምክንያትና ትርጉም ይኖረዋል:: በአድጉት አገሮች ሥራ ፈትነት የሚከሰተው ሥራ በማ ማረጥ ለረጅም ጊዜ ሳይሠሩ /ሳይቀጠሩ/ በመቆየት ወይም የሥራ ዕድሜ ላይ ሆነው የዘመኑን የሙያ ብቃት በማጣት ወይም በልዩ ልዩ ምክንየት ያለ ሥራ በመኖር ነው::

በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች ደግሞ የሥራ ፈትነት ሁኔታ ከዚህ የተለየና ውስብስብነው:: የሙያ ብቃት በማጣት አለመሥራትን፣በባሕል ምክንያት መሥራት ሲችሉ ተቀምጦ መዋልን፣ በበዓላት ሰበብ ሥራ መፍታትን፣ በተዛባ ፖለቲካና አለመረጋገት ከሥራ መራቅንና የሌሎች ተረጂ መሆንን፣ በባዕድ አምልኮ ምክንያት ሥራ ፈትቶ በየቃልቻውና ጠንቋዩ ቤት ተሰብስቦ በመዋል ጊዜን ማባከንን፣ዝናብ እየጠበቁ ከፊል ዓመት መቦዘንን÷ ወዘተ... ያጠቃልላል::

ምክንያቱ ምንም ይሁን ሥራ መፍታት ኃጢአት ነው:: በስንፍና ሳይሠሩ መብላት «በፊትህ ወዝ እንጀ ራህን ትበላለህ» የሚለውን አምላካዊ ሕግ መተላለፍ ነውና:: ዘፍ.3÷19:: ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» ያለው:: 2ተሰሎ.3÷10::

በመሆኑም «ሰው ወደ ተግባሩ እስኪመሽም ድረስ ወደ ሥራው ይወጣል» እንደተባለው ሥራ ፈትነትን አስወግደን ሥራን የኑሮአችን መሠረት ልናደርግ ያስፈልጋል:: መዝ.103÷23:: አንድ ሰው ካልሠራ የመኖር ትርጉሙ ይጠፋበታል:: ከሰውም ከእግዚአብሔ ርም ዘንድ ዋጋንና ክብርን ያጣል:: ማቴ.23÷1፣26፣መኃል.5÷1–5:: ስለዚህ ተግተን በመሥራት ለራሳችን÷ ብሎም ለቤተክርስቲያናችን የሚገባንን እናድርግ::

ወስብሐት ለእግዚአብሐር

✠ ✠ ✠

# ዴር–ኤል–ሡልጣን

## በደም የተከተረ ዐጽመ ርስታችን

እንደምን ሰነበታችሁ?

ባለፈው እትማችን፤ከክርስቶስ ልደት አንድ ሺ ስምንት ዓመት በፊት የንጉሥ ሰሎሞን ዜና ጥበብ ከመካከለኛው ምሥራቅ ለዓለም ተሰማ:: በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ነገሥታት ወደ ቅድስት አገር ኢየሩሳሌም ተጉዘው የንጉሱን ጥበብ አይተው የጥበቡን ምንጭ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ከንጉሡ የግብገ ጥሪ ይላክላቸው ነበር:: የግብገ ጥሪ ከደረሳቸው አገሮች አንዷ አገራችን ኢትዮጵያ ነበረች:: በዘመኑ የኢትዮጵያ ንግሥት የነበረች ንግሥተ ሳባ /ንግሥተ አዜብ/ ቀድሞ ወደዚያ ይሄድ ከነበረው ተምሪን ከተባለ ኢትዮጵያዊ ነጋዴ ያንን ዜና እየሰማች ታደንቅ ነበርና ጥሪው እንደደረሳት ልዩ ልዩ ገጸ በረከት አስይዛ ረጅሙን የባህርና የየብስ ጉዞ ጀመረች::

ንግሥቲቱ ኢየሩሳሌም እንደደረሰች ንጉሡ በታላቅ አክብሮትና ትኅትና ተቀበላት:: የያዘችውን 120 መክሊት ወርቅና ብዙ ሽቱ እንዲሁም የከበረ እንቁ ለንጉሡ አቀረበች:: ንጉሡም እንደ ታላቅ ገጸ በረከት አቅራቢነቷ እሷ ካመጣችለት ገጸ በረከት የሚበልጥ ስጦታ፤ ተከትለዋት የሄዱት አሽከሮችና ከብቶች እንዲያርፉበት፣ለጉብኝቷም የታሪክ አሻራ ይሆን ዘንድ አንድ ታላቅ ርስት ሰጣት:: በርካታ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት እጅግ በሚያስቅቅ ሁኔታ ያለቁበት፣ አያሌ የታሪክ መዛግብት በግፍ የወደሙበት አጽመ ርስታችን:: ዴር–ኤል–ሡልጣን:: በኢየሩሳሌም የሃይማኖትና የታሪክ ይዞታችን::

ይህ ቦታ ኢትዮጵያ በ34 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንግሥት ስድስተኛ ሕንደኬ /የገንዘብ ሚኒስቴር/ በሆነው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አማካኝነት ክርስትናን እስከምትቀበልበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያውያን እንደ ኦሪቱ ሥርዓት ለበዓል ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዙ የሚያርፉበት ነበር:: አገራችን ክርስትናን ከተቀበለች በኋላ ግን ወደ ቦታው የሚሄደው ምእመን ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ በ4ኛው መቶ ዓመት መጨረሻና በ5ኛው መቶ ዓመት መግቢያ ባሉ ዓመታት ታላቁ የዴር–ኤል–ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም በኢየሩሳሌም ተቋቋመ:: ከዚያ በኋላ የኢትዮጵያ ገዳም ማኅበር በኢየሩሳሌም ቅዱስ ቦታ ተብሎ በሚታመንበት ሥፍራ ሁሉ ይዞታቸውን እያስፋፉ መኖር ጀመሩ: ይሁንና በ1830 ዓ.ም ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ርስታቸውን ጠብቀው ሲኖሩ ለታሪክ ጠባሳ የተወ ችግር መጣባቸው:: በተጠቀሰው ዓመት በገዳሙ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ወረርሽኝ ገብቶ ፈጃቸው:: በሕይወት ከተረፉት ሁለት መነኮሳት ወንዱ ቦታውን የሚረከቡ መነኮሳት ሊወስዱ ወደ ኢትዮጵያ መጡ:: የእማሆይን በብቸኝነት በሰፊው ገዳም መቀመጥ የተረዱት ግብጾች «የሐበሾችን ርስት ለመውረስና እነሱንም ከቦታው ለመንቀል ጊዜው ዛሬ ነው» በማለት እማሆይን ደብድበው ካባረሩ በኋላ ርስታችንን በቁጥጥር ስር አደረጉት:: ከዚያስ? ከዚያማ ሐመር 7ተኛ ዓመት ቁጥር1 ትቀጥላለች::

ከዚያማ እነዚያ ሰይጣን የላካቸው ግብጾች ተንኮላቸው ታሪክ በሚመረምር ይፋ እንዳይሆንባቸው አንድ መሰሪ ሀሳብ ይዘው በወቅቱ ወደ ነበረው የእስላም ንጉሥ ቀረቡ:: «ሐበሾችን የፈጀው ወረርሽኝ ተዛምቶ ለአገር እንዳይተርፍ ባለበት እናቃለው?» ንጉሡም ተስማምቶ በገዳሙ ቤቶች ያሉ ዕቃዎች በሙሉ ተበርብረው ወጥተው እንዲቃጠሉ አዘዘ:: ገንዘብ የማይገዛቸውና የርስቱን የእኛ መሆን የሚመሰክሩ አያሌ የታሪክ ማስረጃዎች በግብጻውያኑ በተለኮሰ እሳት ጋዩ:: የአገሪቱ የመተዳደሪያ ደንብ /ስታትስኮ/ አልፈቅድላቸው አለ እንጂ ቤቶቹንም ቢያፈርሱ በወደዱ:: ታሪክ የመዘገበው ትውልድም የማይረሳው ግፍ::

በገንዘብ ተገዝቶ ለግብጻውያን መሣሪያ የሆነው ባሻ የፈጸመው ግፍ የተሰማ እንደሆነ ችግር ያጋጥመኛል ብሎ ስለፈራ ከግብጻውያኑ ጋር ተማክሮ የዴር–ኤል–ሡልጣንን ገዳም ዘግቶ ቁልፉን ይዞ ተቀመጠ :: ይህንን አጋጣሚ ለመጠቀም የፈለገው ግብጻዊው ቄስ ባስልዮስ ከእስክንድርያ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ:: ሹሙንም ካህን እያለ ቤተክርስቲያን መዘጋት የለበትምና ገብቼ ልቀድስ ብሎ አስፈቀደ:: ሹሙም ጥያቄውን ተቀብሎ ቁልፎቹን አስረከበው::

ባስልዮስ ይኼንን ዕድል ሲያገኝ የኢትዮጵያን ገዳም ሥሪት መለወጥ ጀመረ:: ኢትዮጵያውያን ገብተው እንዳይጸልዩ የቤተክርስቲያኑን በር ዘጋው:: የጥንቱን የገዳሙን በር አፍርሶ ሌላ በር ሠራ :: መነኮሳትን ለመውሰድ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው መነኩሴ እንዳሰበው መነኮሳቱን ይዞ ኢየሩሳሌም ሲገባ ልክ እንደእስራኤላውያን ርስታቸው በሌሎች ተነጥቆ ጠበቃቸው:: ምንም ዐቅማቸው ደካማ ቢሆን ለየባለሥልጣናቱ አቤት ማለት ጀመሩ: ግብጻውያኑ ግን «የሐበሻ ርስት የለውም» እያሉ ኢትዮጵያውያኑን ደብድበው አባረሯቸው:: በተለይም አባ ዳውድ የተባለ የግብጽ ጳጳስ መነኮሳቱን በአለንጋ እያስደበደበ ከርስታቸው እንዳይደርሱ አሳደዳቸው:: ከርስታችሁ ራቁ ተብለው የሚሰቃዩት መነኮሳት ግን ባዩትና በሚያጋጥማቸው ሁሉ ተስፋ ሳይቆርጡ ከርስታቸው ወሰን ሳይርቁ በጌታ መቃብር አጠገብ በሚገኝ አንድ ቦታ ዋሻ ፈልፍለው ጐጆ ቀልሰው መኖር ጀመሩ:

በዚያ ዓይነት ዓመታት ካለፉ በኋላ ግን የኢትዮጵያውያኑ ጩኸት ጠንክሮ በመምጣቱ ከልዩ ልዩ አገሮች መንግሥታት ግፊቱ እያየለ በመምጣቱ ግብጻውያኑ በርስታችን ውስጥ ከሚገኙት ባዶ ቤቶች በተወሰኑት እንዲኖሩ ፈቀዱላቸው:: ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያኑ መነኮሳት በገዛ ርስታቸው



በደብረ ሥልጣን ኢትዮጵያ ገዳም ዐውደ ምህረት የትንሣኤው ብርሃን ወጥቶ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት፥ ልዑካን መዘምራን በዝማሬ፥ ምእመናን በዕልልታ ሁደት ሲያደርጉ (1988 ዓ ም)

፣በገዛ ቤተክርስቲያናቸው እንደልባቸው
አይገቡም፣አይወጡም:: ግብጻውያኑ በፈ
ቀዱ ጊዜ ይከፍቱላቸዋል:: ባልፈቀዱ
ጊዜ ይከለክሏቸዋል:: ይህን አባቶቻችን
በከፍተኛ ተጋድሎ ያስገኙትና ያቆዩት
የቅድስናና የታሪክ ይዞታ ከኢትዮጵያ
ከወጣ ጀምሮ በየዘመኑ የነገሡ ነገሥ
ታት ለሚመለከተው አቤት ሲሉ ቆይ
ተዋል::

አፄ ምኒልክ በኢትዮጵያ በነ
ገሡ ጊዜ የቱርክ መንግሥት በኢየሩ
ሳሌም የሚኖሩ የኢትዮጵያውያን ማኅ
በረ መነኮሳት ስቃይ ተመልክቶ በኢት
ዮጵያውያኑ ላይ እየተፈጸመ ያለውን
ግፍን እንዲያስቆም፣ቦታውም በርስት
ነት የተገኘ ታላቅ ርስታችን በመሆኑ
ቁልፉ ወደባለቤቶቹ እንዲያስመልስ
እንዲያደርግ አቤቱታቸውን አቀረቡ::
ምንም እንኳ ለጥያቄያቸው ፈጣንና
ሙሉ ምላሽ ባያገኙም የቱርክ መንግ
ሥት ግብጻውያኑ በዴር ሡልጣን በም
ሥራቅ በኩል አዲስ በር እንዲከፈት
አድርጓል:: አፄ ምኒልክና እቴጌ
ጣይቱ ይህንን በሰሙ ጊዜ 41 ጊዜ የደ
ስታ መግለጫ መድፍ አስተኩሰዋል::

ይሁን እንጂ ምንም እንኳን
ለኢትዮጵያውያን ከሰፊው ርስታቸው
ተቆርጦ ኩሽና የማታህል ቦታ ቢሰ
ጣቸውም ክርክሩ አልተቋረጠም ነበር::
ይልቁንም በዚያ የሚኖሩ ኢትዮጵያ
ውያን መነኮሳት የመንግሥታቸውን
ድጋፍ እያገኙ ስለመጡ ክርክራቸውንና
አቤቱታቸውን የበለጠ እያጠነከሩ
መጡ:: በ1872 ዓ.ም የኢትዮጵያውያን
መነኮሳትን ችግር የተገነዘቡት አጼ
ዮሐንስ ሰፊ ቦታ ገዝተው ደብረ ገነት
ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያንን ሰሩ::
ከቱርክ ጋር ተዋግተው የማረኩትን 6
ሳጥን ሙሉ የእንግሊዝ ወርቅ ለገዳ
ማውያኑ መተዳደሪያ ኢየሩሳሌም
ላኩት:: ሳጥኖቹ እስከ ዛሬ ድረስ በዚ
ያው ይገኛሉ:: ከዴር-ኤል-ሡልጣን
አቅራቢያ የሚገኘውን የገዳማቱ
ጽ/ቤትና መንበረ ጵጵስና ቦታ ገዝተው
ያበረከቱትም አጼ ዮሐንስ ናቸው::

በቅድስት አገር ያለችዋ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክ
ርስቲያን በሊቀ ጳጳስ እንድትመራ
ተወስኖ በ1944 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ
በኢየ ሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት
የመጀመ ሪያው ጳጳስ ሆነው ተሾመው
ከሄዱ በኋላ የክርክሩ ምዕራፍ መልክ
እየያዘና ጠንክር እያለ ሄደ:: ብፁዕ
ነታቸው ነገሩን በቅርበት እየተከታተሉ
ርስታችን መሆኑን የሚመሰ ክሩ ልዩ
ልዩ መረጃዎች እየሰበሰቡ ሳለ በ1952
ዓ.ም በወቅቱ የእስራኤል ንጉሥ ሁሴን
የአፍሪካን አገሮች ሊጐበኙ ወደ አፍ ሪካ
እንደሚያቀኑ ተሰማ:: አጋጣሚ ውን
በመጠቀም ጃንሆይ እኒህን ንጉሥ ወደ
ኢትዮጵያ ጋብዘው ጉዳቱን እንዲያስረዱ
አቸው ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ለቀዳማዊ
ኃይለ ሥላሴ ደብዳቤ ላኩላቸው::
ጃንሆይም ማሳሰቢያውን በመቀበል ከሌ
ሎች አገሮች ጋር ኢትዮጵያንም እን
ዲጐበኙ ለንጉሥ ሁሴን ጋበዟቸው::
ንጉሡም ግብዣውን ተቀ ብለው መጡ::
ጃንሆይ ኢየሩሳሌም ባለው ርስታችን ላይ
ያለውን ችግር ገለፀው ትክክለኛውን
ፍርድ እንዲያገኙ አሳሰቡ::

ንጉሥ ሁሴን ወደ አገራቸው
እንደተመለሱ የዴር ሡልጣን ጉዳይ በአስ
ቸኳይ ትክክለኛውን ውሳኔ እንዲያገኝ
ለጠቅ ላይ ምኒስትራቸው ትእዛዝ ሰጡ::
ጠቅላይ ምኒስትሩም በወቅቱ የኢየሩ
ሳሌም ገገር ለነበረው ሐሰን ሐትብ ጉዳ
ዩን አጥንቶ እንዲያቀርብ ትእዛዝ አስተ
ላለፉ:: ወዲያው ይህንን ጉዳይ አጥንቶ
ውሳኔ የሚሰጥ የምኒስትሮች ኮሚቴ
ተቋቋመ:: ኮሚቴው ሰፊ ጥናትና ውይ
ይት አድርጐ በ1952 ዓ.ም ዴር ሡልጣን
የኢትዮጵያውያን ርስት ነው ብሎ ውሳኔ
ሰጠ:: በውሳኔው መሠረት ምንም እንኳን
አስር ዓመታት ቢቆይም በ1962 ዓ.ም
ለብዙ ጊዜ ተዘግተው የኖሩትን የቅዱስ
ሚካኤልንና የአርባዕቱ እንስሳን አብያተ
ክርስቲያናት ቁልፎች የጆርዳን መንግ
ሥት ለኢትዮጵያ አስረከበ:: ኢትዮጵ
ያውያኑም ተዘግተው በኖሩበት ቤተመቅ
ደሶቻቸው ለ40 ቀናት ያህል ስብሐተ
እግዚ አብሔር ሲያቀርቡ ቆዩ:: ይሁን
እንጂ ፈቃጁ የእስላም መንግሥት ስለ
ነበረ ከእስላሙ የግብጽ መንግሥት ጋር
በመመካከር ኢትዮጵያውያኑ እንዲነጠቁ
አደረገ:: በነገሩ እጅግ ያዘኑት ኢትዮ
ጵያውያን በብፁዕነታቸው አማካኝነት ወደ
አምላካቸው እየጮኹ እያለ በኢየሩሳሌም
ነግሶ የነበረው የእስላም መንግሥት ድል
ተነስቶ በኢየሩሳሌም በእስራኤላውያን
እጅ ሆነች::

በመሆኑም አያሌ ኢትዮጵያው
ያን መነኮሳት የሞቱበት፣የተራቡ የተጠ
ሙበት ርስታችን ቦታቸውን ከእሥራኤል
መንግሥት ተረከቡ:: እስከ አሁን ድረስ
በግብጽ በአርመንና በሞስ ኮብ እጅ
ተይዘው የተመለሱ ቦታዎች አሉን::
በመሆኑም ይህንን ክርክሩ ገና ያላለ
ቀለትን ርስት ታግሎ መረከብ የዚህ
ትውልድ ድርሻ ነው:: የተረከብ ነውን
ገዳም እንኳን ማደስ አንችልም:: ጣራው
ሲነደል፣ ግድግዳው ሲፈርስ እያለ ቀሱ
ከማየት ውጪ ማደስ አይቻልም::
በምድረ ኢየሩሳሌም ያሉ ገዳማት
በየጊዜው ሲጠገኑና ሲሻሻሉ የኢትዮጵያ
ገዳም ብቻ ስታትስኰ /ባለበት ማቆየት/
በሚለው ሕግ ታሥሮ እየፈረሰ ይገኛል::
ከጥቁሩ ዓለም በኢየሩሳሌም ርስት ያላት
ኢትዮጵያ በመሆንዋ የዴር-ኤል-ሡል
ጣን ርስት የአፍሪካ ውያን ጭምር መመ
ኪያ ነው:: በመሆኑም አበው በደማቸው
ያቆዩንን ርስት ተረክበን ለማስረከብ መዘ
ጋጀት አለብን:: ኢየሩሳሌም ሆይ ብረሳሽ
ቀኜ ትርሳኝ በማለት ቅዱስ ዳዊት
እንደተናገረ ልባችን ዘወትር ከዴር-
ኤል-ሡልጣን መለየት የለበትም::

በኢየሩሳሌም የሚገኙ ሌሎች የኢትዮጵያ
አብያተ ክርስቲያናትን ወደፊት የምንዳስ
ሳቸው ይሆናል:: እስከዚያ ቸር ያሰን
ብተን:: ☩☩☩

## በአዲስ አበባ ...

ከገጽ 14 የዞረ

ያለበት እያለም ሊያገለግላት የተነ
ሣበት ወቅት ነው:: የወጣቱ በቤተ
ክርስቲያን አካባቢ መሰባሰብ ትልቅ
የቤተክርስቲያን ዋስትና ነው::
መቼም በአባቶች ፈንታ ልጆች ካልተ
ተኩ ቤተክርስቲያን ችግር ይገጥማ
ታል:: ምክንያቱም ዛሬ ወጣቶች
ናቸው በቋንቋውም ሆነ በባህሉ መስ
ለው የሚሄዱ:: ሌሎችንም የቤተክርስ
ቲያን ጠላቶች መንገዳቸውን የሚያ
ውቋቸውና የሚዘጉባቸው:: ለዚህም
ነው ቅዱስ ሲኖዶስ በጉዳዩ አምኖ
በአሁኑ ወቅት የወጣቱን በቤቷ
ክርስቲያኑ ሥር መሰባሰብ የፈቀ
ደው:: እኔ ከ1961 ዓ.ም. ጀምሮ
ከልጆቼ ጋር ብዙ በመቆየቴ የወጣቱን
ጥቅም ቀደም አድርጌ ነው የተረ
ዳሁት:: እንደእኔ እንደእኔ የእነሱን
ችግር ወይም ጥያቄ መመለስና ማሟ
ላት የቤተክርስቲያንን ችግር መመለስ
ነው:: ስለዚህ ምናልባት እንደተባለው
የወጣቱን ተሳትፎ እንደጉዳ የሚያ
የው ካለ ስህተት ነው:: ይኸ አንድ
ሰው የሚያዝዘው ሳይሆን ቤተክር
ስቲያን ወይም ቅዱስ ሲኖዶስ የሚያ
ዝዘው ነው:: ቤተክርስቲያን ልጆቿን
አቅፋ ከምታገለግልባቸው መድረኮች
አንዱ ሰንበት ት/ቤት ነውና ወጣቶች
በቤተክርስቲያናቸው አጸድ ሲሰባሰቡ
መንከባከብ በዚያ የሚኖሩ አባቶች
ኃላፊነት ነው::

*__ሐመር__*:-ለካህናት፣ለምእመናን፣ለወጣቶ
ች የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?

*__አቡነ ቄርሎስ__* :- ለካህናት፤ዘመኑ ነጣቂ
የበዛበት በመሆኑ የጠባቂነት አደራቸውን
እንዲወጡ እላለሁ:: በቤተክር ስቲያን የሚ
ሰጡትን አገልግሎት ሁሉ በፍቅር በአንድ
ነትና በመተሳሰብ እንዲያ ደርጉትም
አደራ እላለሁ:: ከዚያም በተጨማሪ ቤተ
ክርስቲያናችንን በውስጥም በውጭም
ሆነው ሊመዘብሩ የሚሹትን እየተከታተሉ
እንዲያጋልጡና ከቤተክርስ ቲያንም ማስ
ወጣት ይጠበቅ ባቸዋል:: ምእመናን
ደግሞ በምክረ ካህን እየኖሩ በሥጋ
ወደሙ ተወስነው የእግዚአብሔርን መን
ግሥት እንዲጠብቁ እመክራ ለሁ:: ለቤተ
ክርስቲያን ያላቸውን ፍቅርና እንክብካቤ
እንዲጨምሩ፣ለአገር ሰላም ለቤተክርስ
ቲያን አንድነት አብዝተው እንዲጸልዩ
ልጆ ቻቸውን እየመከሩ በቤተ ክርስቲያን
ትምህርት ተኮትኩተው እንዲያድጉ ማድ
ረግ ይጠበቅባቸዋል እላለሁ:: ወጣቶቹ
ደግሞ አባቶቻቸውን እንዲያከብሩ ከሥራ
ቸው እየተቀመጡ እንዲማሩ፣ መንፈሳዊና
ሥጋዊ ዕውቀታቸውን እያዳበሩ እንዲኖሩ
አደራዬ ጥብቅ ነው:: ሰላም ለኢትዮጵያ
ሰላም ለቤተክርስቲያን ማኅበራችሁን
የሰላም የአንድነት የፍቅር ያድርግላችሁ
በርቱ::

*__ሐመር__* :- ረጅም ዕድሜ ይስጥልን::

*__አቡነ ቄርሎስ__* :- አሜን::

☩ ☩ ☩

# የኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ከ«መፈቃቀድ» እና ከ«መጠናናት» አንጻር

/ዲ.ኤፍሬም እሸቴ/

ለሐመር /የክርስቲያናዊ ኑሮ እና ምንተ ንግበር መጽሔትም/ ሆነ ለስምዐ ጽድቅ /የክርስቲያናዊ ሕይወትና ምሥጢሬን ላካፍላችሁ/ ዓምዶች ከሚመጡ ጥያቄዎችና አስተያየቶች መካከል በቁጥር አብዛኛውን እጅ የሚይዙት ቅድመ ጋብቻ የሚፈጠረውን የተቃራኒ ጾታ ግንኙነትን የተመለከቱ ናቸው:: ግንኙነት ስለመጀመር፣ ግንኙነትን ስለማቋረጥ፣ ስለመማማል፣ ስለመ ከዳዳት፣ቃል ስለ መገባባት፣ ቃልን ስለማጠፍ ወዘተ... ይጠይቃሉ:: ይህ ጽሑፍም የሚመለከተው ይህንኑ ነው::

ብዙ ወጣቶች በተለያዩ ምክንያቶች ከዕድሜ አቻዎቻቸው ጋር ግንኙነት ይጀምራሉ:: ይህ የጀመሩት ግንኙነት ጊዜ የሚገታው፣ምንም ዓይነት ዕንቅፋት ፍቅራቸውን የሚያደናቅፍ አይመስላቸውም:: ስለዚህም ይማማ ላሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ ገልጠው፣የቤተክ ርስቲያን በር «ከፍተውና-ዘግተው» ወይም ወደ ታወቁ ገዳማት ሔደው ቃል ይገባባሉ:: አንዳንዶቹም የንስሐ አባት ሳያውቀው፣ ቤተክርስቲያን ሳታዘው፣የራሣቸውን ሥርዓት ፈጥረው «አብረን ቆረብን» ይላሉ:: በአንድ ቀን፣ በአንድ ቦታ መቁረባቸውን እንደ ቃል ኪዳን ይቆጥሩታል::

ጊዜ አልፎ ከዚህ ሐሳባቸው መውጣት ሲጀምሩ ዙሪያው ገደል ይሆ ንባቸዋል::የተማማሉትን መሐላ፣ የገቡትን ቃል እንደ ወጥመድ ይመለከቱታል:: እናም «ምን ይሻለኛል?» ይላሉ:: መውጪያ ቀዳዳ ይፈልጋሉ:: ገሚሶቹ በራሣቸው ፈቃድ የራሣቸውን መንገድ ይከተላሉ:: አንዳንዶቹ ግን ኃጢአት የሠሩ ስለሚመስላቸው የሚያደርጉት ይጠፋቸዋል::

በነዚህ ወጣቶች ግንኙነት ውስጥ የተሣሣተው ነገር ምንድር ነው? ምን ማድረግ ነበረባቸው? ይህ ጽሑፍ እነዚህን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል::

ወጣትነት የውሳኔ ዕድሜ ነው:: የተለያዩ ውሳኔዎች የሚወሰንበት አስቸጋሪ ጊዜ ነው:: በዚህ «ቁርጥ ጊዜ» የሚፈጸሙ ስሕተቶች መዘዛቸው ለኋለኞቹም ዓመታት ይተርፋል:: መል ካሞቹ ውሳኔዎች ደግሞ ፍሬያቸው ተዝቆ አያልቅም:: ይህም ወጣትነት በማንኛውም ሰው ሕይወት ውስጥ የሚኖረውን ጉልህ ሥፍራ ያመለክተናል:: ትምህርት ለመማር፣ሥራ ለመሥ ራት፣ዳገቱን ወጥቶ ቁልቁለቱን ወርዶ ራስን ለማሸነፍ ወጣትነት አመቺ ነው:: የትዳር ጓደኛን ለመምረጥ፣ጥሩ ቤተሰብ ለመመሥረት፣ጎጆ ለመውጣት ወጣትነት ትክክለኛው ዕድሜ ነው:: ግን እንዴት?

መልካም ትዳር መስርቶ፣ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ፣በደስታ በተድላ መኖር የሁሉም ሰው ምኞት ነው:: ወደዚህ ለመድረስ ግን ብዙ አስቸጋሪ ነገሮች ይገጥማሉ:: በተለይም ራስን በንጽሕና ጠብቆ ለመኖር ለሚወስን መንፈሳዊ ሰው ቅድመ ጋብቻ ያለው ሕይወት አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜ ይበዛል:: ስለዚህም ትልቅ ጥንቃቄ ይጠይ ቃል:: በእግዚአብሔር ቸርነት፣በቅዱሳን አማላጅነት ፣በትምህርተ ቤተክርስቲያን መሪነት ካልሆነ በስተቀር መሠናክሉን ለማለፍ አዳጋች ነው::

ነገር ግን በቅዱሳን ጸሎት፣ በመላእክቱ ጥበቃ ከሁሉም በላይ ደግሞ በወደዳትና በመረጣት በእናቱ በወላዲተ አምላክ ጸሎትና አማላጅነት የሚታደገን አምላካችን አይተወንምና በቸርነቱ ይጎበኘናል:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ቸር ነው እያልን ራሳችንን ጥለን ተዘልለን መቀመጥ አይገባንምና እርሱ በሰጠን አእምሮ ተጠቅመን ራሣችንን መጠበቅ ያስፈልገናል:: ይህንንም ለመረዳት ያስችለን ዘንድ ቅድመ ጋብቻ ሊመጡ ስለሚገባቸው /ይገባቸዋል ብለን ስለምናስባቸው/ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች እናነሣለን:: ስለ «መፈቃቀድ እና መጠናናት»::

ሁለት ወጣቶች አብረው ለመኖር ከመወሰናቸው አስቀድሞ «መፈቃቀድ» አለባቸው:: ለመፈቃቀድ ደግሞ አንዱ ሌላውን «ማወቅ» ይኖርባቸዋል ብለን እናስባለን:: ሌላ ሰው ለነርሱ ተገብቶ የሚወስን ካልሆነ በስተቀር:: ለዚህም ደግሞ ወጣቶቹ የሚመለከቷቸው የተለያዩ መስፈርቶች ይኖራሉ:: ከሁሉ የሚበልጠውና ምንም ጊዜ የማይለወጠው ግን ሃይማኖት ነው:: ይህንን ሁሉ ተመልክተው አንዱሌላውን የራሣቸው ለማድረግ ሲመርጡ መፍቀዳቸውን ይገልጣሉ:: ይህ አንዱ ሌላውን የወደፊት የትዳር አጋሩ አድርጎ ለመቀበል የሚወስነውን ውሳኔ «መፈቃቀድ» ልንለው እንችላለን::

መፈቃቀድ አእምሮን ሰብስቦ በአንድ ሰው ላይ ለማድረግ ያስችላል:: ልቡና ወጪና ወራጁን በሙሉ ከመመልከት ተቆጥቦ በአንድ ላይ ያርፋል:: እርሱን ብቻ ይመለከታል:: ወዲህ ወዲያ ማለቱን ያቆማል:: ይህም ያንን /የፈቀዱትን/ ሰው ለማወቅ ዕድል ይሰጣል:: ደካማም ሆነ ጠንካራ ጎኑን ለማጥናት ያስችላል::

የምንኖረው እውነተኛው ከሐሰተኛው፣ጥሩው ከመጥፎው በተደበላለቀበት ዓለም ነውና መንፈሳውያን ወጣቶች ለጓደኝነት የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ሁሉ ከመቀበላቸው በፊት ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባቸዋል:: የተለያዩ ሰዎች ጥያቄያቸውን የሚሠነዝሩት ለተለያዩ ዓላማ ነውና:: ለአብነትም የሚከተሉትን ሦስት ጥያቄዎች እናንሣ::

## ሀ/ የ«ወንድ/ሴት ጓደኛ አላቸው» ለመባል ብቻ

ወጣቶች ራሣቸውን ከጥገኝነት አላቅቀውና በሁለት እግራቸው ቆመው «ትልቆች ሆነው» መታየት ይሻሉ:: በቤተሰብ ውስጥም ቢሆን እንደ ሕጻን መታየት አይፈልጉም:: የሌላው ሰው ምክር ሬት ሬት የሚላቸውም ለዚህ ነው:: «ለራሴ ራሴ አውቃለሁ!» ማለት ያበዛሉ:: ቀንበራቸውን ሰብረው ከሚወጡባቸውና ለራሳቸው ነፃነትን ከሚያውጁባቸው ነገሮች አንዱ ደግሞ የ«ወንድ ወይም ሴት» ጓደኛ መያዝ ነው::

ስሙ ራሱ ያስደስታቸዋል:: መንገድ ላይ የሚያዩትን፣በመጻሕፍት የሚያነቡትን፣በፊልም የሚመለከቱትን ተግባራዊ ለማድረግ ይሻሉ:: ከጓደኞቻቸው ጋር ሲጫዋወቱ የሚፎክሩበት «ገድል» ነውና ዘወትር ያስጨንቃቻዋል:: ስለዚህ ወጥተውም ሆነ ወርደው «ጓደኛ መያዝ» ይፈልጋሉ::

ይህ ዓይነቱ መፈቃቀድ በለጋ የወጣትነት ፍላጎት የሚመራ ነው:: ለወ ደፊቱ ዓላማ ተብሎ የተያዘ ነገር ላይ ኖረው ይችላል:: ጥንቃቄ የጎደለው፣የበላይ መካሪ የሌለበት በመሆኑ ለጉዳት ያጋልጣል:: ብዙ እኅቶቻችን ያለ ዕድሜያቸው አርግዘው አበባ ዕድሜያቸውን በአጭሩ የሚቀጩት በዚህ ዓይነቱ ግንኙነት ተጠልፈው እየወደቁ ነው::

ዘመናችን ከሥልጣኔ ጋር /በሥልጣኔ ስም/ አብረው በመጡ የተለያዩ አስተሳሰቦች ተጣብቧል:: ከነዚህም አስተ ሳሰቦች መካከል «ወጣቶች ገና በለጋ ዕድሜያቸው ስለተቃራኒ ጾታ ግንኙነት መጨነቃቸው፣ ለትምህርታቸው ሊሰጡት ከሚገባው ትኩረት ይልቅ ስለዚህ ግንኙነት ማሠባቸው፣ያለ ዕድሜያቸው መግባት

ወደሌለባቸው ሕይወት እንዲገቡ መገደዳቸው ዋነኞቹ ናቸው::

ብዙ ሰዎች ገና ከጠዋቱ የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት መጀመርን «አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው» እውነት አድርገውታል:: ስለዚህም በለጋ ዕድሜያቸው ግንኙነት ከሚጀ ምሩት ይልቅ የማይጀምሩት ያስገርሟቸዋል:: ለዚህም በመንፈሳዊ ሕይወት የሚመላለሱ ወጣቶች የተለያዩ የቃላት ውጊያዎች ሊገጥማቸው ይችላል:: ሐዋርያው አስቀድሞ ስለ ሎጥ ሲናገር «ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማው ዕለት ዕለት በዓመፀኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበርና» /2ኛጴጥ 2÷7/ እንዳለ የሚያዩትና የሚሰሙት ሁሉ የሚያስጨንቅ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን የምናመልከውን እናውቃለንና ራሣችንን በትዕዛዙእያጸናን ሰውነታችንን በንጽሕና እንጠብቅ:: ይህ ንን ዓይነቱን ግንኙነት ከመጀመራችን በፊት ዓላማው ይግባን:: «ይህንን ግንኙነት የመሠረትሁት ለምንድን ነው?» ብለን ራሣችንን እንጠይቅ:: የሚያመጣውን ውጤት እንመርምር:: ማስቀደም የለብንን ነገር እንመዝነው:: ጉዳዩ ከአቅማችን በላይ ሆኖ ካገኘነው ንስሐ አባቶቻችን፣ ለመምህራን ቤተክርስቲያን ወይም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አርአያ ለሆኑ ወንድሞች እና እኅቶች እናማክር:: ይህም ሊመጣ ከሚችል ብዙ ጉዳት ይጠብቀናል::

<u>ለ/ ሩካቤ ሥጋን ለመፈፀም ብቻ</u>

አንዳንዳቹ ደግሞ ዓላማቸው አንድ ብቻ ነው:: የሌላውን «ፈቃድ» የሚጠይቁት ይህንኑ መሠረት አድርገው ነው:: በብዙ ወጣቶች ዘንድም ተቀባይነቱ ከፍ እያለ መጥቷል:: ጓደኝነትን ለሩካቤ ሥጋ ብቻ ብሎ ማሠብ:: እንዲህ ዓይነት ሐሳብ ያላቸው ሰዎች ማንኛውንም ዓይነት ጓደኝነት የሚመዝኑት ከዚህ አንፃር ብቻ ነው::

ይህ ዓይነቱ ግንኙነት ከክርስትና ትምህርት ጋር ይጋጫል:: መንፈሳውያን ወጣቶችም ይህንን በጥንቃቄ ሊመለከቱት ይገባል:: ፈቃዳቸውን የሰጡት ሰው ዋና ዓላማው ጊዜያዊ የሆነው የሥጋ ፍላጎትን መፈጸም ከሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ትልቅ ፈተና መሆኑን መረዳት አለባቸው::

ቅድመ ጋብቻ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የሚወተውቱ ጓደኞች ብዙዎቹ የወደፊቱ የተቀደሰው ትዳር አይታያቸውም:: ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ከመጣሳቸውም በተጨማሪ በሥጋቸው ሊገጥማቸው የሚችለውን ፈተና ሁሉ ይዘነጉታል /ይንቁታል/:: ያልተፈለገ እርግዝና፣ያልተጠበቀ በሽታ፣የትምህርትና የሥራ መሠናከል ሊገጥማቸው እንደሚችል አያስቡም:: ስለዚህም መንፈሳውያኑ ከጋብቻ በፊት የሚመጡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ጥያቄዎችን በመንፈሳዊ ዓይን መመልከት ያስፈልጋቸዋል::

<u>ሐ/ የትዳር ጓደኛ ለማግኘት</u>

ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ሌላውን ለጓደኝነት የሚጠይቁት ለትዳር አጋርነት ሲያስቡት /ስለሚያስቡት/ ብቻ ነው:: የመፈቃቀድ ብቸኛው ዓላማም ይህ ነው:: ነገር ግን ይህ አስተያየት በሌሎቹም የሚነገር በመሆኑ በእውነት ለተቀደሰ ጋብቻ የሚፈልገውን ከሐሰተኛው ለመለየት አስቸጋሪ ይሆናል::

መንፈሳውያኑ ራሣቸው ሌላውን ለጓደኝነት የፈለጉበትን ዓላማ ለማወቅ መጣር አለባቸው:: በጊዜያዊ መቀራረቦች፣በአፍአዊ ውበቶች ወይም በሌላ ምድራዊ መመዘኛዎች ላይ ብቻ ተመ ርኩዘው የወጡት ከሆነ ዘላቂ አይደለምና የራሣቸውንም ሆነ የሌላውን ሰው መንፈሳዊ ሕይወት ሊፈትኑ ይችላሉ::

መፈቃቀዱ ከላይ በፊደል ተራ ከሀ–ሐ ከተዘረዘሩት በየትኛውም ምክንያት የተጀመረ ቢሆን ሁለቱ ተፈቃቃጆች /ጓደኞሞች/ እርስ በርሣቸውለመተያየት፣ ለመተዋወቅ፣ ለመግባባት፣ለወደፊቱ ጋብቻ መሠረት ለመጣል የሚችሉበት ጊዜ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል:: አንዱ ሌላውን የፈለገው /ከላይ ከተቀጠሱት/ ለየትኛው መሆኑ ራሱ የሚታወቀው አንዱ ሌላውን ለመረዳት ጊዜ ሲያገኙ ብቻ ነው:: ይህ እንዱ ሌላውን ለማወቅ፣ ለመረዳት፣ ለመግባባት፣ለትዳር ይሆን አይሆን እንደሆነ የሚገነዘቡበት መንገድም «መጠናናት» ሊባል ይቻላል::

በመንፈሳዊ ዓይን፣ስንመለከተው አንዱ ሌላውን የሚያጠናው ከምን አንፃር ነው? ማጥናት ማለት ራሱ ምን ማለት ነው? መመዘኛውስ? የአጥኚዎችስ ድርሻ ምንድር ነው? «ፈቃደ እግዚአብሔር» ብለን ሐሳባችንን ሁሉ ለአምላካችን አሣልፈን ከመስጠታችን ጋር ሲነፃፀር «ላጥና» ብሎ ማሰቡ አይጋ ጭምን? መጠናናቱ ወደ እጮኝነት ከዚያም ወደ ጋብቻ የሚያድገው ወይም ተቋርጦ መለያየት የሚመጣው መቼና ምን ሲሆን ነው? እነሆ::

«መጠናናት» የሚለው ቃል ራሱ ግልጽ አይደለም:: በዓለሙ የሚሰጠው ትርጉም ተሣሥቷል:: በሩካቤ–ሥጋ መተዋወቅን፣ለተወሰኑ ጊዜያት ያለ ሕጋዊ ጋብቻ አብሮ መኖርን መጠናናት የሚል ሥያሜ ሰጥተውታል:: ከመጠናናት በኋላ ሊመጣ የሚገባውን ነገር አስቀድመው እየፈጸሙ ራሣቸውን ይሸነግሉበታል::

ከትምህርተ–ክርስትና አንጻር ስንገመግመው ግን «መጠናናት» ለትዳር የፈቀዱት ሰው በሕገ– እግዚአብሔርና በሥርዓተ ቤተክርስቲያን አብሮ ለመኖር፣መልካም ቤተሰብ ለመመሥረት፣አረፍተ–ሞት እስኪገታቸው በፍቅር ለመዝለቅ የሚችል ይሁን አይሁን ለመለየት ፈቃደ እግዚአብሔር የሚጠየቅበት፣ጠባይ ለጠባይ የሚግባቡበት የትምህርትና የጸሎት ጊዜ ነው:: አንዱ የሌላውን ደካማ ጎን አውቆ ለመሸሽ ሳይሆን ለማረቅ /ለማስተካከል/ የሚሞክ ሩበት ወቅትም ነው::

ይህ ጊዜ ፈቃደ እግዚአብሔርን መጠየቂያ ነው:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ማለት ግን የእኛ ፈቃድ ማለት አይደለም:: ለእኛ መልካም የመሰለን፣ ችግሩ ያልታየን ነገር እግዚአብሔርን ላያስደስት ይችላል:: እኛ ለራሳችን ይበጃል ብለን የምንሠራው ሥራ ሁሉ መልካም ላይሆን ይችላል:: ይህንን የሚያውቀው መጻዒያት ሁሉ በፊቱ ክሡት የሆኑ ፈጣሪ ብቻ ነው:: የሁለት ወጣ ቶች መፈቃቀድም አድኅ ለትዳር ይበቃ እንደሆነ አለያም አንዱ ለአንደ ኛው ያልተፈጠሩ ይሁኑ እርሱ ያውቃ ልና ሁሉን በጥበቡ ያከናውነዋል::

*መጠናናት የሌሳውን ደካማ ጎን ለመንቀስ መምከር ብቻ አይደለም:: የራስንም መመልከት፣ነቅሦ ማው ጣት፣እርምት መስጠትም እንጂ:: ለትዳር አጋርነት የመረጡት ሰው የሚወደውንና የሚጠላውን ማወቅም ነው:: ይህም በወደፊቱ የትዳር ሕይወት ላይ ትልቅ ሥፍራ ይኖረዋል:: የሚወደውን ለማድረግ፣የሚጠላውን ለመተው ያስችላልና::*

ስለዚህም መንገድን ሁሉ ለርሱ አሣልፎ መስጠት ይገባል:: «ጌታ ሆይ ፈቃድህ ቢሆን?» እንበል እንጂ «የእኛ ፈቃድ ካልተፈጸመች» አንበል::

አንዳንድ ወጣቶች እንዲፈጸም የሚፈልጉት የራሣቸው ሐሳብ ብቻ ነው:: የወደዱት ሁሉ የነርሱ ቢሆን ደስታቸው ነው:: የእነርሱ ምኞት–ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አልገናኝ ሲል ኃዘን ይውጣቸዋል:: «ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ» አያስተውሉም:: ሁሉን የሚያስተካክለው ከማንም በላይ ስለኛ የሚጨነቀው የሰማይ አባታችን መሆኑን ይዘነጉታል::

ከዚህ አንፃር እነዚህ ወጣቶች ሊያስተውሉት የሚገባ አንድ ነጥብ መኖሩን ማስተዋል ያስፈልጋቸዋል::

መፈቃቀድ ሁሉ ወደ እጮኝነት ወይም ወደ ጋብቻ ላይደርስ ይችላል:: ሐሳባችን ለዚያ እንድንደርስ ቢሆንም ካልተፈቀደልን ግን ወደ ምሬትና ኃዘን ግፋም ሲል መንፈሳዊ ሕይወትን ወደ ሚያነዋውጽ ፈተና ከማለፍ ይልቅ «የእግዚአብሔር ፈቃድ አልሆነም» ማለት አለብን:: ወደ ትዳር ጎዳና አብረን ለመዝለቅ ያልቻልናቸውንም ሰዎች በጠላትነት ከመመልከት ይልቅ በመንፈሳዊ ወንድምነትና እኅትነት ለመመልከት የምንችለውም ያን ጊዜ ነው::

ስለዚህም ከዚህ ዓይነቱ የሐሳብ ምስቅልቅሎሽ ለመዳን ከፈቀድናቸው ሰዎች ጋር ሊኖረን የሚገባውን ግንኙነት፣ምን ማድረግ እንደሚጠበቅብን፣የመጠናናቱም ዋና ዓላማ ምን እንደሆነ እንደሚከተለው እንመለከታለን::

## 1/ ራስንም ሆነ ጓደኛን በደንብ ለማወቅ

ከመጠናናት ጥቅሞች አንዱ ለጓደኝነት የመረጡትን ሰው በደንብ ለማወቅ ማስቻሉ ነው:: «ለትዳር የመረጥኩትን ሰው ምን ያህል አውቀዋለሁ?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ያስችላል:: ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱ ወጣቶች ተጣድፈው ወደ ጋብቻ ከመግባት ይልቅ ጊዜ ሰጥተው የየራሣቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን እንዲመለከቱ፣ ስሕተታቸውን እንዲያርሙ ያደርጋቸዋል:: ለዚህም ነው አስቀድመን «የትምህርት ጊዜ ነው» ያልነው::

መጠናናት የሌላውን ደካማ ጎን ለመንቀስ መሞከር ብቻ አይደለም:: የራስንም መመልከት፣ነቅሦ ማውጣት፣እርምት መስጠትም እንጂ:: ለትዳር አጋርነት የመረጡት ሰው የሚወደውንና የሚጠላውን ማወቅም ነው:: ይህም በወደፊቱ የትዳር ሕይወት ላይ ትልቅ ሥፍራ ይኖረዋል:: የሚወደውን ለማድረግ፣ የሚጠላውን ለመተው ያስችላልና::

## 2/ ጥሩ ባል /ሚስት/ መሆን መቻል–አለመቻልን ለመመርመር

ወጣቶች ለትዳር፣ ለባልነትና ለሚስትነት፣ ለአባትነትና ለእናትነት የሚኖራቸው አመለካከት ያደጉበት ኅብረተሰብ፣ የኖሩበት ቤተሰብ፣ ነጸብራቅ ነው:: ባልተስተካከለ ትዳር፣ በማይስማሙ አባትና እናት፣በመጥፎ ጠባዮች የተያዙ ወላጆች /ለምሳሌ በሲጋራና በመጠጥ የተጠመዱ ፣ ለትዳር በማይታመኑ፣ገንዘብ በሚያባክኑ/ መካከል ያደጉ ወጣቶች ትዳርን ከዚህ አንፃር ብቻ ሊመለከቱት ይችላሉ::

በሌላም መልኩ ኑሯቸው ሁሉ አልጋ በአልጋ ከሆነ ቤተሰብ የበቀሉትም ትዳርን እንዲህ አድርገው ሊመለከቱት ይችላሉ:: ሁለቱም የየራሱ ድክመት አለው:: መስተካከል ያለበትና የሚችለውም በመጠናናት ወቅት ነው:: ጋብቻ እንደመጀመሪያው ዓይነት ሲኦል እንደሁለተኛውም ዓይነት የሞኞች ገነት አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል::

ከዚህም ባሻገር ጥሩ ባል ወይም ጥሩ ሚስት ለመሆን መዘጋጃ ጊዜም ነው:: የቤተሰብን ኃላፊነት ለመሸከም፣የትዳር ፍሬዎች የሆኑ ልጆችን ለመቀበል /በሥነ ልቡናም በገንዘብ ዐቅምም/ መዘጋጀት ይፈልጋል:: አስተምረው ለወግ ለማዕረግ ያደረሱ ወላጆች መረዳት አለባቸው:: ለዚህ ሁሉ ደግሞ ወደ ትዳር የሚገባው ሰው ራሱን ማዘጋጀት አለበት::

## 3. ዓላማን ለመፈተን

የተቃና ትዳር ለመመሥረት ማሟላት ይገባቸዋል ተብለው ከሚጠቀሱት ነገሮች አንዱ የሁለቱ «ተፈቃቃጆች» በዓላማ አንድ መሆን ነው:: በዓላማ አንድ ለመሆን ደግሞ መቀራረብ፣መተዋወቅ፣ጠባይ ለጠባይ መግባባት፣ሐሳብ ለሐሳብ መረዳዳት ያስፈልጋል:: የአንዱ «ሥራ» ሌላውን የሚያስደስት እንጂ የሚያበሳጭ መሆን የለበትም:: መጽሐፍ ማንበብ የምትወድ ሚስት ባሏ የወረቀት ዘር አያሳየኝ የሚል ቢሆን፣ጆሮው ከሬዲዮ–ዓይኑ ከቴሌቪዥን መስኮት መነቀል የማይሰ ማማው ደግሞ የነዚህ ጸር ከሆነች ሴት ጋር ቢገናኙ ይህንን መለያየት ሳይቀርፉ ወደ ጋብቻ ከመግባት ይልቅ /ችግሩን እንደቀላል በመቁጠር/ አስቀድሞ በመነጋገር፣ በመመካከር መፍትሔ መሻቱ ይበጃል:: ጥቃቅን መለያየት ሁሉ ለሰይጣን መግቢያ ሊሆን ይችላ ልና::

በአጠቃላይ ሁለቱም ጊዜያዊ ሆነ ዘላቂ ዓላማዎቻቸውን መረዳዳት አለባቸው:: ይህም መፈፀም ያለበት ከጋ ብቻ አስቀድሞ መሆን ይገባዋል እን ላለን::

## 4. ችግሮችን የመቅረፊያ መንገዶችን ለመመርመር

ሁሉም ሰው ችግር ሲገጥመው የሚፈታበት የየራሱ መንገድ አለው:: አንዳንዱ የችግሩ ሁሉ መውጫ ዕንባው ይሆንና መንታ መንታ እያወረደ ይገላገለዋል:: አንዳንዱ ደግሞ መለኪያ ሥር መደበቅን ይመርጣል:: ብዙ በመብላት /ሳይታወቃቸው/ ጭንቀታቸውን የሚገላገሉም አሉ:: እንቅልፍ አጥቶ መጨነቅ፣በአጠገቡ ያለውን ሁሉ ያባቱ ገዳይ ይመስል መቆጣት፣አንደበቱን ዘግቶ ከመናገር መከልከል፣ለተወሰኑ ቀናት ከሰው ተለይቶ ለብቻ መሆንን የሚመርጥ ወዘተ:: ብዙ ዓይነት ነው:: ለትዳር የመረጥነው ሰውስ? ሲናደድ፣ ሲከፋው ምን ያደርጋል? ይህንን ማወቁ የግድ ነው:: የራስን ጠባይ ከርሱ ጋር ለማስታረቅ፣መተው ያለበት ከሆነ መክሮ ዘክሮ ለማስተው የችግር መቅረፊያ መንገዱን ማወቅ ይገባል::

በትዳር ዓለም ውስጥ መጋጨት ሊኖር ይችላል:: ግጭቱ መፍትሔ የሚያገኘው አንዱ የሌላውን ጠባይልቅም አድርጎ ሲያውቅ ብቻ ነው:: ከትዳር ውጪም የሚያጋጥሙ የተለያዩ ችግሮች በትዳር ላይ ጫና የሚያሳድሩበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም:: በዚህ ጊዜ ችግር መፈጠሩን ተረድቶ የትዳር ጓደኛን ለማጽናናት «ሲናደድ ምን ያደርጋል?» የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል::

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ መቀራረቦችና መዋደዶች ለመፈቃቀድ በር ከፍተው፣መፈቃቀዶች አንዱ ሌላውን ለማጥናት አስችለው ለፍጻሜ የሚደርሰው ግንኙነት ብዙ ነገሮች እንዳሉት ለመመልከት ሞክረናል:: ለመሆኑ የተፈቃቀዱ ሰዎች አንድ ጊዜ ቃላቸውን ከተሰጣጡ በኋላ ሐሳባቸውን መቀየር አይችሉምን? ሐሳባቸውን የሚቀይሩትና ግንኙነታቸውን የሚያቋርጡት ምን ጊዜና ምን ሲፈጠር ነው? በመጠናናት ውስጥ ያሉ ወጣቶች ሊገጥሟቸው የሚችሉ ፈተናዎች ምን ምን ናቸው? ይህ ንንስ ፈተና ድል ለመንሣት ምን ማድረግ አለባቸው? በሚቀጥሉት ዝግጅቶቻችን እንመለስበታለን::

## ማሳሰቢያ

*ይህንን ርዕስ ጉዳይ በተመለከተ ያላችሁን አስተያየት ቀጣዩ ዕትም ከመውጣቱ በፊት ብታደርሱን ለትምህርቱ ጥንካሬ አጋዥ ነውና አስቡበት::*

# ሥራ ፈትነት

ፍጹም ግርማ

ሥራ ፈትታችሁ ቀኑን ሁሉ በዚህ ስለምን ትቆማላችሁ»

ማቴ.20÷6

ባለፈው እትም በዚህ ዓምድ «ለልመና መስፋፋት ተጠያቂው ማነው?» የሚለውን ጽሑፍ አንብቤዋለሁ:: ጸሐፊው በለማኙ መብዛትና አሁን አገራ ችን ባለችበት ሁኔታ አንጀቱ ያረረ ይመስላል:: ብቻዬን ሳብሰለስለው የነበረውን ስሜቴን በመጋራ ቱ ደስ ብሎኛል:: እርሱ ለልመናው መስፋፋት ብዙ ምክንያቶችን አስቀምጧል:: እኔ ደግሞ በአገራ ችን በሰፊው ተስፋፍቶ ስላለው ስንፍናና ሥራ ፈትነት የበኩሌን ለማለት እሞክራ ለሁ::

አስቀድሞ ልዑል እግዚአብሔር ሥራ ን ሠርቶ የሰው ልጅም መልካም እየሠራ በገነት እንዲኖር አዘዘው:: ዘፍ1÷18፣2÷2:: «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው::» ዘፍ.2÷15:: የሰው ልጅም የኑሮው መመሪያ የሆነውን አምላካዊ ትእዛዝ እየፈጸመ ሥራ ን እየሠራ ይኖር ነበር:: «ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራ ህን ትበላ ለህ» ተብሏልና ዘፍ.3÷19::

ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች ይህንን አምላካዊ ሕግ በመዘንጋት ሳይሠሩ ሊኖሩ ይወዳሉ:: በተለይም በአሁኑ ጊዜ በሀገራ ችን ያለውን ሁኔታ ስንመለከተው ስንፍና ከሚገባው በላይ በመንገሡ ሥራ ያለውን ከሌለው ለመለየት ያስቸግራ ል፡ ለዚህም ከገጠመኜ በመነሣት ወደ ዝርዝሩ ብገባ የተሻለ ይመስለኛል::

ከወር በፊት መሆኑ ነው:: ለግል ጉዳዬ ወደ አንድ በስሙ የተከበረ መሥሪያ ቤት ሄጄ ነበር:: በቅድሚያ በመሥሪያ ቤቱ ያሉትንና በትምህርት ቤት እያለን የማውቃቸውን ጓደኞቼን ማግኘት ፈልጌ ወደ አንደኛው ቢሮ አመራ ሁ:: እንደደረስኩ ለሻይ እንደወጣ ተነገረኝ:: ለተወሰኑ ደቂቃዎች ያህል ብጠብቀውም ባለመመለሱ ካገኘሁት በማለት ወደ መዝናኛ ክበባቸው አመ ራ ሁ:: በዚያም ስድስት ሆነው ከአንዱ ጥግ ክብ ሰርተው ሲሳሳቁ አገኘ ኋ ቸው:: ሰላምታ ከተለዋወጥንና ከዚህ በፊት ከማላውቃቸውም ጋር ከተዋወቅሁ በኋላ ወንበር ተስቦልኝ እኔም ተቀላቀልኩ:: የመጣሁበት ጉዳይ ቢያስ ቸኩለኝም የምፈልገውን ሰው በዚያ ሰዓት እንደማላገኘው ስለተነገረኝ ከአ ንድ ሰዓት በላይ ስንጫወት ቆየን:: ሥራ ያስፈታኟቸው መስሎኝ ጨንቀኝ:: ራ ሴን ከኃላፊነት ለማውጣት «ሥራ የለም እንዴ? እናንተ ወደ ቢሮ ሂዱ እኔ ልጠብቅ» አልኳቸው:: እነርሱም ምንም የሚሠራ እንደሌለና «እንዲያውም እኔን ማጫወት አንድ ትልቅ ሥራ እንደሆነ» እየቀለዱ መለሱልኝ:: ለጊዜው ፕሮጀክታቸው ስለተቋረጠ «የክበብ ወንበር አሟቂዎች» ከሆኑ መሰንበታቸውን ነገሩኝ:: ደሞዛቸው ግን አልተቋረጠም::

ሁኔታው አዲስ ባይሆንብኝም በአገራ ችን ከሚገባው በላይ ተንሠራ ፍቶ ያለውን ሥራ ፈትነትና የስንፍና ሁኔታ እንዳስበው አደረገኝ:: እንደዚህ በየመሥሪያ ቤቱ ወንበር አሙቀው የሚመለሱትን፣ በሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ መዝገብ ላይ ፊርማቸው በመስፈሩ ብቻ ደሞዝ የሚከፈላቸውን፣... ሠራ ተኞች ሁኔታ ሳስብ አዘንኩ:: ታዲያ እንዴት አገራ ችን ከችግር ትላቀቅ? ከድህነትስ እንዴት እንውጣ? ተስፋፍቷል የሚባለው የለማኙ ብዛትስ በምን ይቀነስ?

በአንድ ወቅት በዕድገታቸው ከእኛ በታች የነበሩት አገሮች ዛሬ ጥለውን ሄደዋል:: ከእኛ ርዳታ ሲያገኙ የነበሩት አሁን ግን የሚረዱን ሆነዋል:: ለዚህም ደቡብ ኮሪያንና ሲንጋፖርን ማንሣት ይቻላል:: ከዛሬ 35 ዓመት በፊት እኛ ከደቡብ ኮርያ በተሻለ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ነበርን:: ኢኮኖሚዋ በእርሻ ላይ ብቻ የተወሰነና ገና ከጦርነት ያላገገመች አገር ነበረች:: ዛሬ ግን ከበለጸጉት ውስጥ ተመድባ 11ኛ ደረጃን ይዛለች:: እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ የውጭ ንግድ ገቢያዋ 35 ሚሊዮን ዶላር ብቻ ነበር:: በ1997 ዓ.ም. ግን «ዘኢኮኖሚስት» በተባለ መጽሔት ዘገባ መሠረት ወደ 130 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል::

ከ3 ሚሊዮን የማይበልጥ ሕዝብ ያላት ሲንጋፖርም ከሠላሣ ዓመት በፊት ከድሃ አገሮች ተርታ የምትመደብ ነበረች:: ምንም የተለየ የተፈጥሮ ሃብት የለበትም:: ነገር ግን በፍጥነት አድጋ እ.አ.አ በ1995 ዓ.ም. የዕቃችና የአገልገሎት ምርቶችወደ 521 ቢሊዮን ብር ደርሷል:: በዚሁ ዓመት የነበረው የእያንዳንዱ ሰው ዓመታዊ አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢም ወደ 173,818 ብር /አንድ ዶላር 6.35 ብር በሚመነዘርበት ጊዜ ሆኗል::

ደቡብ ኮርያም ሆነች ሲንጋፖር እንደዚህ ያደጉት የተለየ የተፈጥሮ ሀብት ኖሯቸው አይደለም:: በነዳጅ ዘይትም ሆነ በሌሎች ማዕድኖች ተለይተው አይታወቁም:: የሁለቱም አገሮች ሀብታቸው ታታሪ ሠራ ተኛ ሕዝባቸው ብቻ ነው:: የሥራ ሁኔታ ተመቻቸላቸው:: አገሮቻቸውን በአንድ ብሔራ ዊ ስሜት ሊያሳድጉ ተነሡ እንደታየውም በጥቂት ዓመታት ውስጥ በዕድገታቸው መጠቁ!

በአንጻሩ የእኛን አገር ሁኔታ ስንመለከት ግን ከዚህ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን:: ምንም እንኳን የተሻለ የተፈጥሮ ሀብትና 60 ሚሊዮን ሕዝብ ቢኖረንም የሕዝባችን የሥራ ባህል ግን ወደ ዕድገት ለማምራ ት የሚያስችል አይመስልም:: ብዙዎችን የአገር ዕድገት አያሳስባቸውም:: የሚሠሩት የራ ሳቸው ፍላጐት በተወሰነ ደረጃ እስኪሟላ ብቻ ነው:: አንዳንዶቹም ወደ ሥራ የሚሄዱት ደሞዝ ስለሚከፈላቸውና የሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ ፊርማ ስላለ ወይም አለቃቸውን ስለሚፈሩ ብቻ ነው:: በተረፈ ሥራ ይሠራ ፣ አይሠራ ድርጅቱም ይክሰር አይክሰር ጉዳያቸው አይደለም::

እንደዚህ ያሉት በሌሎች አገሮች እንደሚደርገው በዜግነታቸው ብቻ የሚከፈላቸው ቢሆን ኖሮ ለመዝናናት ካልሆነ በቀር ከቤታቸው የሚወጡ አይመስለኝም:: እንዲያውም አንዳንዶቹ እንደ በሽተኛ በተኙበት መቀለብን ሳይፈልጉ አይቀሩም::

ሌሎቹ ደግሞ ከቢሮ ሥራ ውጭ ሌላው ሥራ ሥራ አይመስላቸውም:: በዚህ የተነሣ ሥራ ሲያማርጡ የሌሎች ተረጂዎች በመሆን ዕድሜአቸውን ይገፋሉ:: ካልሆነም ከአገር ይሰደዳሉ:: አለያም ወደ ልመናና የተለያዩ ወንጀሎችን ወደ መፈጸመ የሰማራ ሉ::

ለዚህም ዋንኛው ምክንያቱ የግል ጥረትና ሥራ ን የመፍጠር ባሕል አለመኖር ነው:: አንደኛው የራ ሱን ሥራ ፈጥሮ መሥራ ት ሲጀምር የሚያበረታታውና የሚያግዘው ሳይሆን የሚበዛው የሚያናንቅበትና ተስፋ የሚያስቆርጠው ነው:: የባሰባቸውም ሊያጠፉበት ይሯሯጣሉ:: ይህ ከክርስትና ትምህርት የመራ ቅና የመንፈሳዊነት ጉድለት ውጤት ነው :: እንዲህ ያሉትን ነው ነቢዩ «...ሰነፍ ግን ስንፍናን ይናገራ ል፣ልቡም ዝንጉነትን ይፈጽም ዘንድ በእግዚአብሔርም ላይ ስህተትን ይናገር ዘንድ፣ የተራበችውንም ሰውነት ባዶ ያደረግ ዘንድ ከተጠማም ሰው መጠጥን ይቆርጥ

ዘንድ በደልን ይሠራ ል» ያለው ኢሳ.32÷6::

«ጥሩ ሥራ አላቸው– ተምረዋል» ከሚባሉትም አለባበሳቸውን ብቻ አሳምረው ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጠው ወረቀት ላይ ሲፈርሙ ወይም ስልክ ሲቀጠቅጡ ከዋሉ የሠሩ የሚመስላቸው አሉ:: ራ ስ ወዳዶችና የወገን ፍቅር የሌላቸውም አገርና ወገ ንን በማ ገልገል ፈንታ በጉቦና በማጭ በርበር መኖርን ሙያቸው ያደር ጉታል:: «ሲሾም ያልበላ» በሚል አጉል ፈሊጥ የአገርን ሀብት የጠላታቸው ሀብት ይመስል መዝረፍ ዋንኛ ሥራ ቸው ነው::

አንዳንዶቹም የሰሙትን እንዳዩ ፣ባልነበሩበት እንደነበሩና ያልሠሩትን እንደሠሩ አድርገው ስለሚያወሩ ብቻ እንደሠራ ተኛ ተቆጥረው ይኖራ ሉ:: እንድያውም በደሞዝና በዕድገት ከሌላው የሚሻሉበት አጋጣሚም አይጠፋም:: ሌሎች የነዚሁ ቢጤዎች ደግሞ እንደተማሩ የሚያሳይ ወረቀት ካላቸው ወይም አንድ ጊዜ በሠሩት ሥራ ዝናውን ካገኙ ወረቀታቸውና ስማቸው ብቻ ይሠራ ላቸው ይመስል ወንበር እያሞቁ በሌሎች ሠራ ተኞች ትከሻ ይኖራ ሉ:: አንዳንዶቹ ለሚሠሩ እንቅፋት እስከመሆን ይደርሳሉ:: በባለሙያ ስም ተቀምጠው መሥራ ት እየቻሉ የውጭ ሀገር ዜጎች መጥተው እንዲሠሩላቸው የሚፈልጉም ጥቂቶች አይደሉም:: እነርሱ የተቀመጡት ለመፈረም ብቻ ነው:: በአንድ ፋብሪካ ያለ ማሽን አንዲት ብሎን ብትወልቅ «እስቲ እኛ እንሞክረው» ከማለት ይልቅ«የውጭ አገር ሰዎች መጥተው ይሥሩት» ማለት የተለመደ ሆኗል:: እንደዚህ ያሉት ሰዎች ጥናት ቢጠና፣ዲዛይን ቢሠራ ÷ ሕክምና ቢደረግ… በውጭ አገር ሰው ካልሆነ አይጥማቸውም::

ይህ የራ ስ የሆነውን ንቆ የውጭ የሆነው ነገር ላይ ብቻ መንጠልጠል ራ ሱን የቻለ ከፍተኛ ችግር ነው:: አንድ ሕግ ለማውጣት ባሕላዊው ሕግ ምን ይመስል ነበር ከማለት ወይም የሽማግሌዎችን ልምድ ከመጠየቅ ይልቅ ልምድ የሚቀስመው ከውጭ አገርና ከውጭ ሰዎች ብቻ ነው:: በአጠቃይ በሥራ ውም ይሁን በማንኛውም ዘርፍ የውጭዎች ላይ ጥገኛ መሆንና የራ ስ የሆነውን ሁሉ መናቅና ማጣጣል በጣም የተስፋፋ ስለሆነ ወደፊት በሰፊው እመለስበታለሁ::

አንዳንዶች ደግሞ ከየትኛው እንደሆኑ አይታወቁም:: «ሥራ » አላቸው፣ሲወጡና ሲገቡ ይታያሉ:: በፊታቸውም ሥራ ተከምሯል:: ደፋ ቀና ይላሉ:: ነገር ግን ምን እንደሚሠሩ አይታወቅም:: በጣም ሥራ እንደሚበዛባቸው እነርሱ ሲናገሩ ወዲያና ወዲህ ሲሯሯጡ እንጂ የሥራ ቸው ውጤት አይታይም::

በመሠረቱ አንድ ሰው ሥራ አለው የሚባለው የሥራ ፍሬው ጎልቶ በሰዎች ዘንድ ሲመሰክርለትና ሥራ ው ሲመሰክርለት እንጂ «ሥራ አለኝ» በማለት ስላወራ አይደለም:: እንዲያው ወጥቶ ስለገባ ወይም “ወንበር ሲያሞቅ” ስላዋለ ደሞዝ የሚከፈለው ከሆነ ይህ ሠራ ተኛ ሳይሆን ምጽዋተኛ ቢባል ይቀለዋል::

እዚህ ላይ የመመሪያና የአለቆች /የአሠሪዎችም/ ችግር ለሥራ ፈትነትና ለስንፍና ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው መዘንጋት የለበትም:: አንዳንድ አለቆች መልካም የሠራ ን ከማበረታታት ይልቅ፣ትንሽ ስህተት ሲፈጽም መጮህን ይወዳሉ:: ይህ ደግሞ ሠራ ተኛውን ሠርቶ ከሚሳሳት ይልቅ እጁና እግሩን አጣጥፎ እንዲቀመጥና በሥራ ውም ላይ የእኔነት ስሜት እንዳይኖረው ያደርገዋል:: ከዚህም ሌላ ዘወትር ከበታች ሠራ ተኞቻቸው ወሬ ሲለቅሙ የሚውሉ ካልተሞገሡ የተሠራ የማይመስላቸው፣ከመሥራ ት ይልቅ መመሪያ እያጠቀሱ ራ ሳቸውን ከኃላፊነት የሚያሸሹ አለቆች ቁጥር ቀላል አይደለም::

አንዳንድ «መንፈሳውያን» የሚባሉትና ዘወትር ቃለ እግዚአብሔርን የሚሰሙትም ይህንን ቃል አለማክበራ ቸው ሌላው አሳዛኝ ሁኔታ ነው:: የተገኘውን ሠርቶ ማደር÷በኑሮ ከሌላው ተሽሎ መገኘት ኃጢአት የሚመስላቸው ጥቂቶች አይደሉም:: እንደዚህ ያሉት ሌት ተቀን ተግቶ መሥራ ትን እንደስግብግብነት ይቆጥሩታል:: ይህንንም ስንፍናቸውን ከቅድስና ቆጥረው በባዶ «ያለኝ ይበቃኛል» እያሉ ስንፍናን የመንፈሳዊነታቸው መግለጫ ያደር ጉታል:: ለእነርሱ ትክክለኛው ነገር ዘወትር የተለያዩ ምክንያቶችን እየፈጠሩ ከሥራ መቅረት፣በበዓላት ሰበብ በየገዳማቱ መዞር ብቻ ነው::

አንዳንዶቹም እግዚአብሔር ሥራ እንዲሰጣቸው ዘወትር ይጸልዩና ሥራ ሲገኝ ለመሥራ ት የሚደረድሩት ምክንያት ከሥራ ፈትነት የሚያላቅቃቸው አይደለም:: ሁልጊዜ ለማስቀደስና ኪዳን ለማድረስ÷ በሠርክ ጉባኤ ለመሳተፍና በየገዳማቱ ለመዞር የማይመቻቸው ከሆነ «የኃጢአት ሥራ » ስለሚመስላቸው አይቀበሉትም::

የተቀሩትም «በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ በሁሉ ታዘዙ፣ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ÷ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉ÷ ከጌታ ርስትን ብድራ ትን እንደምትቀበሉ ታውቃችሁና» የሚለው ቃል አልገባቸውም:: ቆላ.3÷23:: የሚቆጣ አለቃ ካለና ቁጥጥር ካበዛ «…መንፈሳዊ» ስለሆኑ እዚያ መሥራ ት እንደሌለባቸው ያስባሉ:: የሚያሳዝነው ግን እንዲህ ዓይነት ሰዎች ስንፍናቸው ወደመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ስለሚዛመት በቤተክርስቲያን ጸንተው አለመቆየታቸው ነው:: ያን ሁሉ ሥራ ፈተው የነበረበትን ጊዜ ለማካካስ የተነሡ ይመስል የኃጢአቱን ኑሮ ንክር ብለው ይገቡበታል:: ለዚህም ሒብ አገር በመሄድ ጀምረው በሴተኛ አዳሪነት የሚጨርሱትን ለአብነት ማንሣቱ ይበቃል::

ይህም የሥራ ፈትነት የተዛባ አመለካከት ውጤትና ስንፍና እንጂ ምክንያቱ ሌላ ሊሆን አይችልም:: እንዲያውም ክርስቲያን በሥራ ው መልካም አርአያነትን ሊያሳይ ይገባዋል:: «በእናንተ ዘንድ አንድስንኳ እንዳንከብድበት÷ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራ ን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራ ን እንዲያው አልበላንም:: ይህም እኛን ልትመስሉ ራ ሳችንን እንደምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ ÷ ያለሥልጣን ስለሆንን አይደለም:: ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና:: ሥራ ከቶ ሣይሠሩ በሰው ነገር እየገቡ÷ያለሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለአንዳንዶች ሰምተናል:: እንደዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራ ቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን÷ እንመክራ ቸውማለን:: እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ÷ መልካም ሥራ ለመሥራ ት አትታክቱ::» 2ተሰሎ.3÷8–9::

እንኳን በዓለም ያለነው ዓለምን ንቀው በገዳም ያሉት አባቶቻችን ይህን መሠረት አድርገው በጸሎት ሰዓት ካልሆነ በቀር ከሥራ አይለዩም:: ምክንያቱም ሥራ መፍታት የኃጢአት በር ስለሚሆን ራ ሳቸውን በሥራ ያስጠምዳሉ:: በአገልግሎትም ይተጋሉ:: የቤተክርስቲያንም ትምህርቷ ይኸው ነው:: «…በውጭ ዘንድ በአግባብ እንዳትመላለሱ÷አንዳች እንዳያስፈልጋችሁ በእጃችሁ ልትሠሩ እንለምናችኋለን:: 1ተሰሎ.4÷10::

በዘመናችን ግን መሥራ ት ሳይሆን እያወሩ መኖር ባሕላችን ሆኗል ሥራ ባሕል ነው:: አንድ ሥራ መሥራ ትን የለመደ ሰው ሥራ ሲፈታ ይጨንቀዋል:: በአንጻሩ ደግሞ ሥራ ፈት ሆኖ ለረጅም ጊዜ የቆየ ሰው ተመልሶ በሥራ መጠመድ ያስቸግረዋል:: ቦዜኔ የመሆን ጠባይን ከማዳበሩ የተነሣ ከዚህ ለመላቀቅና የሥራ ዝንባሌን÷በሥራ የማመንና የመጣርን ችሎታ ማዳበር ያስቸግረዋል::

መለስ ብለን የአባቶቻችን ታሪክ ብንመለከት ግን እንደዚህ አልነበረም:: ዛሬ ዓለምን እያስደነቁ ያሉት አክሱም÷ቅዱስ ላሊበላ ፣አብያተ ክርስቲያናት÷የጐንደር የአፄ ፋሲል

ወደ ገጽ 21 ዞሯል

## ዘረኝነት አሸሸኝ

*ጥያቄ፡-* እኔ በምኖርበት ግዛት የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አለ:: በዚህ የሚኖሩ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች የሆኑ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ከተለያዩ የሀገራችን ብሔረሰቦች የመጡ ናቸው:: በአንዲት ቤተክርስቲያን ጥላ ሥር አስካሉ ድረስ በአንድ መንፈስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ሲገባቸው አመጣጣቸው ግን ዘረኝነታቸውን እንደያዙ ነው:: እንደ የብሔረሰቡም በተለያዩ ቀናት የተለያዩ ጉባኤያት ይካሄዳሉ:: ይህም ክፍፍል ጥላቻንና ዘረኝነትን ከማስፋፋት በቀር ምንም የጠቀመው ነገር የለም:: እኔም ከሀገሬ እንደወጣሁ ቤተክርስቲያን እዚህ በመኖሩ ብደሰትም የዘረኝነቱ ሁኔታ ግን ከቤተክርስቲያን እንድሸሽ አደረገኝ:: በዚህ የተነሣ በቤቴ ተወስኜ የግል ጸሎቴን ብቻ ለማድረግ ተገድጃለሁ:: አባካችሁ ምን እንደማደርግ ግራ ገብቶኛ ልና የሚበጀውን ምክራችሁን ለግሱኝ:: እንደዚህ እየተጠላላንና እርስ በርሳችን እየተለያየን የምንጸልየውን ጸሎት እግዚ አብሔር ይሰማናል?

*ሐና /ከሲያትል-አሜሪካ/*

<u>መልስ</u> ፡- ጥንትም ሆነ ዛሬ የሰውን ልጅ ሰላም እየነሱት ከኖሩት ታላላቅ በሽታዎች መካከል ዘረኝነት አንዱ ነው:: ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች ትኩረት ከሰጧቸው ወንጀሎች መካከል የዘር ማጥፋት ወንጀል አንዱ መሆኑ ይህንኑ ያመለክታል:: በዘርና በጐሳ ልዩነት ሰበብ ብቻ በሥላሴ አርአያ የተፈጠረው የሰው ልጅ እርስ በርሱ ይጨራረሳል:: ዘረኝነት ብዙዎችንም የፍርድ ያለህ እያሰኛቸው ነው:: ለብዙዎች ሰላም መናጋት፣ለንጹሐን ሰዎች ደም መፍሰስ፣ ለብዙዎች ከትዳር መራቅና ትዳር ለመሰረቱትም መናጋትና መፍረስ ዋነኛ ምክንያት ሆኗል:: ዘረኝነት ከፍተኛ የወቅቱ ችግር ስለሆነ በክርስትና እንዴት ይታያል? የሚለውን ጥያቄ በዝርዝር በመመልከት ወደ እኅታችን ጥያቄ እንመጣለን::

ማንኛውም ሰው ወደ ጥንተ ፍጥረቱ መለስ ብሎ ራሱን ሲመለከት … የሚያቆመው አዳም ላይ ነው:: …ዚአብሔር አንድ አዳምን እንጂ የተ… ዘርን አልፈጠረም:: ምንም እንኳ …ር በአስተሳሰብ ልዩነት የተነሣ …ኑ ሌላውን ባሪያ ወይም ዝቅ የማድ… ልማድ ቢፈጠርም የእግዚአብሔር …ት ዘንድ ግን እንዲህ ያለው ልማድ …ኝም::

በዘመነ ሕገ ልቡና /የተጻፈ … ባልነበረበት ዘመን/ ዘረኝነት ቦታ …ነበረውም:: ለዘህም አባባላችን በዘ… የነበሩትን የአብርሃምንና የዮሴፍን

የሚያምነውን ሎሌውን ሲልከው «እኔም አብሬ ከምኖራቸው ከከነዓን ሴቶች ልጆች ለልጄ ሚስት እንዳትወስድለት በሰማይና በምድር አምላክ በእግዚ አበሔር አምልሃለሁ፤ነገር ግን ወደ አገሬና ወደ ተወላጆቼ ትሄዳለህ ለልጄ ለይስሐቅም ሚስትን ትወስድለታለህ» ብሎታል:: ዘፍ 24÷3–4::

አብርሃም ይህን ያለው የከነዓናውያንን ዘር ስለጠላ አይደለም:: የከነዓን ሰዎች አምልኰተ እግዚአብሔር ስለሌላቸው እንዲያውም በሰዶምና በገሞራ የነበሩት ወገኖቻቸው እግዚአብሔርን በማሳዘናቸው በእሳት እስከመቃጠል በመድረሳቸው ነው:: ስለዚህ ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት የምትሆነው ሴት እግዚአብሔርን የምትፈራ መሆን ስላለባት አብርሃም ሎሌውን ወደ ወገኖቹ ልኰታል:: ባልና ሚስት አንድ የሚሆኑት በእግዚአብሔር ብቻ ነውና:: አብርሃም የፈለገውም በሃይማኖት የሚመስሉትን እንጂ ዘራቸውን ወይም ጎሳቸውን አልነበረም::

ዮሴፍ በእሥር ቤት ሳለ የግብጹን ንጉሥ ሕልም ከፈታለት በኋላ በንጉሡ ፈቃድ ግብጻዊቷን የጲጥፍራ ልጅ አስናትን አግብቷል:: ዘፍ 41÷45 ዮሴፍ ዘር መምረጥ አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ከዘሬ ውጪ አላገባም ማለት የሚከብደው ሰው አልነበረም:: አስናትን ያገባው ንጉሡን ፈርቶ ወይም ሌላ ሳግባ ቢል ስለማ ያገኝም አይደለም:: ምክንያቱም በሃይማኖት ጉዳይ ለመጣበት ለማንም እንደማይንበረከክ አሳይቷልና:: የገገርው የጲጥፋራ ሚስት ለዝሙት ስትጋብዘው እመቤቴ ናትና ትእዛዟን መፈጸም ይገባኛል አላለም:: አምላኩን ፈርቶ «በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአት እሠራለሁ?» በማለት ተቃውሟል:: የእግዚ አብሔር ሰዎች ሰውን ፈርተው ወይም ለሥጋ ፈቃዳቸው ሲሉ እግዚአብሔርን አያሳዝኑምና::እንደዚህ በመሆኑም እሥራኤላዊው ዮሴፍ ያገባው ግብጻዊቷን አስናትን ነው:: በሃይማኖት ሰዎች ዘንድ ዘረኝነት ቦታ ስለሌለው ዮሴፍ ከዘሩ ውጪ አግብቷል::

እንደ ዘመነ ሕገ ልቡና ሁሉ በሕገ ኦሪት የተጻፈ ሕግ ለሙሴ ከተሰጠ በኋላም ዘረኝነት ቦታ አልነበረውም:: ለአብነትም ዕብራዊውን ሙሴንና ኢትዮጵያዊቷን ማንሣት ይቻላል:: ሊቀ ነቢያት ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን አግብቷል:: ይህን በማድረጉም እኅቱ ማርያምና ወንድሙ አሮን ተቃውመውት ነበር:: እነዚህ ሰዎች የሙሴን ድርጊት በመቃወማቸው እግዚአብሔርን አስቆጡት:: «እግዚአብሔርም ተቆጥቶባቸው ሄደ÷ደመናውም ከድንኳኑ ተነሣ እነሆም ማርያም ለምጻም ሆነች» ተብሎ እንደተጻፈ:: ዘረኝነት በእግዚአብሔር ዘንድ

ማኅቶተ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስም ዘረኝነትን ደጋግሞ አውግዞ አስተምሯል:: «የምሕረቱ ዕቃዎች ከአይሁድ ብቻ አይደሉም ነገር ግን ከአሕዛብ ደግሞ የጠራን እኛ ነን» በማለት እግዚአብሔር ሕዝብና አሕዛብን ለአንድ አገልግሎት የጠራ መሆኑን ገልጿል:: ሮሜ 4÷24:: እንዲሁም «በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለም አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና» ሲል በሰው ዘር መካከል መብለጥ መበላለጥ እንደሌለ አስረድቷል:: ሮሜ 10÷12:: «ወይስ እግዚአብሔር የአይሁድ ብቻ አምላክ ነውን? የአሕዛብስ ደግሞ አምላክ አይደለምን?» በማለት የቀደመውን አሳብ አጠንክሯል:: ሮሜ 3÷30::

«አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን÷ባሪያዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና» 1ቆሮ 12÷13:: በጥምቀት ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማየ ዮርዳኖስ የተወለዱ ሁሉ ያለ ልዩነት አንድ ናቸው:: ስለዚህ የክርስትና ትምህርት መሠረቱ የሰዎች እኩልነትና አንድነት ነው:: በዘመናችን የሚታየው በዘር፣በቀለም፣በቋንቋ፣በጎሳ መከፋፈል ቦታ የለውም:: በመሆኑም በአንዲቷ ቤተክርስቲያን መለያየትንም ሆነ ልዩነትን መስበክ ከክርስትና ውጪ መሆን ነው:: መለያየት የሰይጣን ነውና! «ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና:: አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም÷ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም÷ወንድም ሴትም የለም፤ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» ገላ 3÷28::

ስለዘረኝነት ይህንን ያህል ካልን ወደ እኅታችን ጥያቄ እንመለሳለን:: ምንም እንኳን አንቺ ባለሽበት አካባቢ የዘረኝነት ችግር /በሽታ/ የተከሰተ ቢሆንም አንቺ ግን በምንም ዓይነት ሁኔታ ከእናት ቤተክርስቲያን መለየት ወይም መራቅ የለብሽም:: እንደገለጽሽልን በቤትሽ ሆነሽ መጸለይ ትችይ ይሆናል:: ነገር ግን እግር ከወጣ ልብም አብሮ መሸፈቱ አይቀርም:: እንዲሁም ከቃለ እግዚአብሔርና ከምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ትለያለሽ:: ከምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ተለይቶ ክርስቲያን ነኝ ማለት ደግሞ ከውኃ የወጣ ዓሣ እንደመሆን ነው::

ቤተክርስቲያን የእገሌ ወይም የእገሊት ናት አይባልም:: በቤተክርስቲያን የሚቀድሰው ካህን ወይም የሚያስተምረው ሰባኪ ከምናውቀው ዘር ወይም ጎሳ የመጣ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ቤተክርስቲያኒቱ የእርሱ ብቻ ናት ማለት አይደለም:: ከጀርባው ሥጋዊ

በተለያዩ ቋንቋዎች ማስተማር ይጠቅም እንደሆነ እንጂ ጉዳት የለውም::

እንዲሁም ማንም ይሁን ማን አንድ ሰው የአንድ ብሔረሰብ አባል የሚሆነው በእርሱ ምርጫ ሳይሆን ከዚያ ብሔረሰብ ስለተወለደ ብቻ ነው:: ፈልጎ ነጭ ወይም ጥቁር ሆኖ የተወለደ የለምና:: ስለዚህ ማንም ቢሆን በዘርና በቋንቋ ልዩነት ማድረግ የለበትም:: ክርስቲያን እንደክርስቲያንነቱ ሊናገር÷ሊያስተምር በተግባር ሊገልጸውም የሚገባው መለያየትን ሳይሆን ፍቅርና አንድነትን ነው:: «ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ:: ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም:: በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ:: ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና፤ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግፋል፤ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል:: በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው» 2ጴጥ 1÷22–25::

ስለዚህ እኅታችን ምንም እንኳን አንቺ ባለሽበት አካባቢ ከክርስትና ትምህርት ውጪ የሆነ መለያየት ጎልቶ ብትመለከችም ከቤተክርስቲያን ልትለይ ግን አይገባም:: ተለይተሽ ራስሽ ትጐጂ እንደሆን እንጂ የምታመጪው ለውጥ አይኖርምና:: ይልቁንም ቀርበሽ እንደ ዚህ ዓይነት መለያየትን የሚያመጡትን ሰዎች ልታስተምሪያቸውና ልትለውጪአቸው ይገባል:: ከቤተክርስቲያን መራቅሽ አንቺንም ከጽድቅ መንገድ ይለይሻል፤ለቤተክርስቲያንም ትሰጪ የነበረውን አገልግሎት ያስቀርብሻል:: የአንቺ ዓላማ እግዚአብሔርን ማገልገል እስከሆነ ድረስ በዚህኛው መርሐ ግብር ላይ ብገኝ የዚህኛው ወገን ናት እባላለሁ የሚል ሥጋትም አይደርብሽ:: በመጀመሪያ ግን አንቺም በስሜት ተገፋፍተሽ ራስሽም የአንድ ጎሳ ደጋፊ እንዳትሆኚ እግዚአብሔር እንዲረዳሽ ጸልይ:: ለጊዜው በምታይው ሥጋዊ ነገር ሳትበሳጪ እየታገስሽ ከውስጥ ሆነሽ ከቅዳሴው እየተካፈልሽ÷ ቃለ እግዚአብሔርን እየሰማሽና በአገልግሎት እየተሳተፍሽ ለውጥ ለማምጣት ሞክሪ:: እግዚአብሔር ይርዳሽ:: በተረፈ ይህ የዘረኝነትና የመለያየት ችግር ሁሉም ሰው ተግቶ ሊጸልይበት የሚገ ባው ጉዳይ ነው::

## ሞቴን ከመጠበቅ ሌላ...

*ጥያቄ* :– ከአገር ቤት ከወጣሁ ዓመት ከስድስት ወር ሆኖኛል:: በጆሃንስበርግ ከተማ በንግድ ሥራ ተሰማርቼ እየኖርኩ ነው:: ይሁን እንጂ በሰው አገር ተስፋ የሌለው የጨለማ ሕይወት ስመኖር ተገድጃለሁ:: ሕይወቴን ያጨለመብኝ የስደቱ ኑሮ አይደለም:: እንደዚህ ተስፋ የቆረጥኩት ዓለምን እንደሰደድ እሳት እያዳረሰ ያለው የዘመኑ ቀሳፊ በሽታ አለብህ ከተባልኩ ጊዜ ጀምሮ ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው ብዙ ፈተናና መከራ የደረሰበት ኢዮብ ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር በቸርነቱ ፈወሰው:: እኔም እንደኢዮብ መከራዬ የበዛ ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም:: ሆኖም መንፈሰ ጠንካራና መከራ ታጋሽ በመሆን እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጌ የምኖር ሰው ነበርኩ:: አሁን ግን ትዕግሥቴ ተሟጠጠ:: ተስፋዬም ጨለመ:: ከመቃብር አፋፍ ላይ ሆኜ የተስፋ ያለህ እላለሁ:: ስለዚህ አባካችሁ ንስሐ ገብቼ ሞቴን ከመጠበቅ ሌላ የማደርገው ነገር ካለ ጠቁሙኝ:: ለዚህም በሽታ መፍትሔ የሚሆን መድኃኒት ካለ እስያም አገር ቤት መጥቼ በጠበል መፈወስ የምችል ከሆነና ሌላም ተስፋ ካለ ንገሩኝ::

*ወንድማችሁ*

*/ከጆሃንስበርግ ደቡብ አፍሪካ/*

__መልስ__ :– በዓለም ላይ ማንኛውም ሰው በሕይወት ዘመኑ ችግር ሊገጥመው ይችላል:: ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ሰው ካለው የመንፈስ ጥንካሬና ብስለት አንጻር ከገጠመው ችግር የመውጣት ብቃቱ የተለያየ ነው:: አንዱ ተስፋ ሲቆርጥ የተቀረው ደግሞ ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር አሳልፎ በመስጠት ይታገሣል:: ለዚህም አንተው ወንድማችን ያነሣኸውን ኢዮብንና ሚስቱን በንጽጽር መመልከት ይቻላል:: ኢዮብ ንብረቱን ÷ልጆቹንና ጤናውን ቢያጣም ታገሠ:: ስለሁሉም ነገር እግዚአብሔርን አመሰገነ:: ሚስቱ ግን ተስፋ በመቁረጥ «እስከአሁን ፍጹምነትህን ይዘሃልን? እግዚአብሔርን ስደብና ሙት» እስከማለት ደረሰች:: ኢዮብ 2÷9::

እንግዲህ በእንደዚህ ዓይነት ችግር ለመፈተን አንተ የመጀመሪያው ሰው አይደለህም:: በመሆኑም እስከዚህ ተስፋ እስክትቆርጥና በጨለማ ውስጥ ነው ያለሁት እስክትል ድረስ ሊሰማህ አይገባም:: ይህ ያለማመን ምልክት ነውና አንተ ተስፋህ ምድራዊ ብቻ አይደለም:: ክርስቲያን እንደመሆንህ መጠን ዓላማህ ሰማያዊውን መንግሥት መውረስ ነው:: ስለዚህ ሥጋዊው ሞት ሊያስፈራህ አይገባም:: ይህማ እረፍት ነው:: እንዲያውም ቅዱሳን ሥጋዊውን ሞት ይናፍቁት ነበር:: «ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ:: ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና» ፊልጵ 1÷23:: ከዚህ ይልቅ ክርስቲያን ሊያስፈራው የሚገባው ሁለተኛ ሞት÷ከእግዚአብሔር ከአምላኩ መለየት ነው::

ምናልባትም እንደዚህ ዓይነቱ ስሜት ሊሰማህ የቻለው ስለንስሐ ያለህ አመለካከት የተሳሳተ በመሆኑ የጊዜውን ብቻ በማሰብህና ሰዎች በሽታውን መድኃኒት የለውም በማለታቸው ይሆናል:: ስለበሽታውም በቂ ግንዛቤ ያለህ አይመስለንም:: በኤድስ ቫይረስ መያዝ ማለት ወዲያው መሞት ማለት አይደለም:: እንዲያውም ኤድስ ቀን ይሰጣል:: በዓለማችን ላይ የአንዲት ቀን ዕድሜ እንኳን የማይሰጡ ሌሎች ብዙ በሽታዎች እንዳሉ ልታውቅ ያስፈልጋል:: ስለዚህ ኤድስን በበሽታነቱ ብቻ ልትቀበለው ይገባል:: አንዳንድ ሰዎች ይህንን ባለማወቅ ልክ በኤድስ ቫይረስ እንደተያዙ ሲነገራቸው ተስፋ ይቆርጣሉ:: ከሰዎች ይገለላሉ:: በጭንቀት ሞታቸውን የሚጠብቁ÷አልፎም የራሳቸውን ሕይወት የሚያጠፉ አሉ:: ይህ ሁሉ ግን በክርስትና ትምህርት ሲመዘን ትክክል አይደለም:: በመሆኑም ክርስቲያን በጊዜያዊ ችግር ተሸንፎ ተስፋ ሊቆርጥ አይገባውም:: «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ አይዟችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌአለሁ» ብሎ ተስፋ በሰጠው አምላክ ስለሚታመን በጽናት ፈተናውን ድል ያደርጋል:: ዮሐ 16÷3::

ስለዚህ አንተም አመለካከትህን አስተካክል:: ገና ለገና ሰዎች በሽታውን ገዳይ ነው ስላሉ እና በቫይረሱ ስለተያዝክ ብቻ ተስፋ ልትቆርጥ አይገባም:: በመሆኑም በጨለማ ውስጥ ነው ያለሁት÷ ሞቴን ከመጠበቅ በቀር ተስፋ የለኝም» የሚለውን አባባል ልታስወግድ ይገባል::

ከሁሉም በላይ አንተ እኮ ሁሉን ማድረግ በሚችል አምላክ የምትታመን ክርስቲያን ነህ! እግዚአብሔር ከፈቀደ እንኳን ከበሽታ ማዳን÷ከሞትም ያስነሣል:: «አልአዛርን ከመቃብር ያስነሣው አምላክ አንተን ከበሽታህ መፈወስ የሚያቅተው ይመስልሃል?» ዮሐ 12÷ :: ስለዚህ እግዚአብሔር የፈቃዱን እንዲያደርግልህ ንስሐ ግባ፤ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙንም ተቀበል:: ቅዱስ ቁርባን የነፍስና የሥጋ መድኃኒት ነውና:: በአካባቢህ ጠበል ካለም ጠጣ:: ምኅረቱ የበዛ አምላክ ሰዎችን የሚያድንበት ነገር አይታወቅምና በእርሱም ታምነህ እስከመጨረሻው ጽና::

ጠቢቡ ሰሎሞን «ለሁሉም ጊዜ አለው» እንዳለ እግዚአብሔር በወደደ ሰዓት ሊያድንህ ይችላልና ሳትጨነቅ በእርሱ ታምነህ ልትኖር ያስፈልጋል:: አንተው በትዕግሥተኛነቱ ያነሣኸው ኢዮብን ደጋግመህ አስብ:: እስከመጨረሻው ታገሰ:: እግዚአብሔርም በወደደው ሰዓት አዳነው:: ያጣውንም ከነበረው እጥፍ ሆኖ ተመለሰለት:: እንግዲህ አንተም ሳትጨነቅ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፡ ሕይወትህን በንስሐ አስተካክል:: ንስሐ አንተ እንዳልከው የሞት መጠበቂያ አይደለም:: ንስሐ በደልን ሁሉ እርግፍ አድርጎ በመናዘዝ ያለፈ የኃጢአትንና የጨለማን ሕይወት ሙሉ በሙሉ ፍቆ በመጣል አዲስ የጽድቅና የብርሃን ሕይወትን መጀመር ነው:: «እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ÷እኔም አሳርፋችኋለሁ» ያለ አምላክም

*ወደ ገጽ 32 ዞሯል*

# ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ

## ንዋያተ ቅድሳትና አያያዛቸው

ከሂሩት ገ/ኪዳን
/የመጨረሻው ክፍል/

ባለፉት አራት እትሞቻችን ስለንዋያተ ቅድሳት ዓይነቶች፣ ትርጉማቸው፣አገልግሎታቸው፣ ምሳሌነታቸውና ክብራቸውን አይተናል::በዚህ እትም ደግሞ እንዴት ልንጠብቃቸውና ልንንከባከባቸው እንደምንችል እናያለን::

አባቶቻችን ለንዋያተ ቅድሳት በእነርሱ በኩልም ለቤተክርስቲያናችን ክብር አንገታቸውን ለሰይፍ ደረታቸውን ለጦር ሰጥተው በሰማዕትነት አልፈዋል ታሪካዊት ቤተክርስቲያናችን ሰይጣን ባስነሣቸው ጠላቶቿ ጥቃት በተሰነዘረባት ቁጥር አባቶቻችን ከቤት ንብረታቸው ይልቅ ንዋያተ ቅድሳትን አስበልጠው ከጠላት ለመታደግ ራሳቸውን ከንዋያተ ቅድሳቱ ጋር በየዋሻው ቀብረው፣ ለንዋያተ ቅድሳቱ የተወረወረውን ድንጋይ በጀርባቸው እያስቀሩ፣በንዋያተ ቅድሳቱ ላይ የተለኮሰው እሳት እያቃጠላቸው በጽናት ጠብቀው ለእኛ አድርሰውልናል:: ዛሬ በየአድባራቱና ገዳማቱ የሚገኙት ንዋያተ ቅድሳት ለዚህ ዐበይት ማስረጃዎች ናቸው:: ጢስ አጥቁሯቸው፣አፈር አሻግቷቸው ይታያሉ:: በሽሽት ንዋያተ ቅድሳቱን በመያዝ ዋሻ ገብተው በዚያው በማረፋቸው አድራሻቸው እስከ አሁን ያልታወቀ በርካታ ንዋያተ ቅድሳት በየዋሻው እንደሚኖሩ ይገመታል:: ስላልተገኙት ማውራት የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ባለመሆኑ «ስለ አሉት ምን እንበል?» በሚለው ጥያቄ ወደ ርዕስ ነገራችን እንገባለን::

ለበርካታ ዘመናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሲጠበቁ የነበሩት በታሪክ ማስረጃነት ብቻም ሳይሆን በዓለም ቅርስነታቸው የሚታወቁት ንዋያተ ቅድሳት በአሁኑ ወቅት ለልዩ ልዩ ችግሮች ተጋልጠው ይገኛሉ:: ሊጠቀሱ ከሚችሉት በርካታ ችግሮች ውስጥ ዝርፊያ ቀዳሚ ተጠቃሽ ነው::

በአሁኑ ጊዜ በዜና ማሰራጫ አውታሮች እንዲሁም በልዩ ልዩ የኅትመት ውጤቶች ታቦታት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትና ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት ተዘረፉ ሲባል እንሰማለን፤ እናነባለን:: ሁላችንም በዛሬ ላይ ስለምንኖር የዛሬውን የንዋያተ ቅድሳት ሁኔታ አወራን እንጂ ይህ አሳዛኝ ድርጊት በቤተክርስቲያን ላይ ሲፈጸም የኖረ ጥንታዊ ነው:: ይህንን ሁናቴ በ4ኛ ዓመት ቁጥር 1 እና 2 እትሞቻችን በስፋት የዳሰስነው በመሆኑ አንመለስበትም:: የሆነው ሆኖ በዚህ ቦታ አንድ ሁሉም የተረዳውና ያልተረዳውም ሊረዳው የሚገባ እውነታ ልንጠቅስ እንወዳለን:: የንዋያተ ቅድሳት ዝርፊያ የትናንት ወንጀል ቢሆንም ይህ ወንጀል እያደር እየተባባሰ ነው::

ለመሆኑ ለንዋያተ ቅድሳት ዝርፊያ መባባስ ምክንያቶቹ ምን ምን ናቸው? በመልስነት በርካታ ነጥቦች ሊነሡ ቢችሉም ዋና ዋና የምንላቸውን ቀጥለን እንመለከታለን::

1. የትምህርት ማነስ

በአባቶቻችን ዘመን ቤተክርስቲያን ቃለ ወንጌልን ለልጆቿ በማስተማር፣ ምእመናንም መብትና ግዴታቸውን ለይተው በማወቃቸው በገንዘባቸው፣ በዕውቀታቸውና በጉልበታቸው ለማገልገል ይቅርና አንገታቸውን ለሰይፍ፣ አጥንታቸውን ለመንኮራኩር ለመስጠት ወደኋላ አይሉም ነበር:: ነገር ግን የሚያስተምሯቸውና የሚመክሯቸው ሲያጡ ከመንፈሳዊነት ጉዳና ወደዓለማዊነት በመሄድ ለቤተክርስቲያናቸው በተለይም ንዋያተ ቅድሳትን ለመጠበቅ ላይበቁ ይችላሉ:: የትምህርት ማነስ ምእመናን ስለ ንወያተ ቅድሳት ክብርና ጥቅም እንዳያውቁ እንዲሁም የእኔነት ስሜት እንዳይሰማቸው አደረጋቸው::

2. የአያያዝ ችግር

ንዋያተ ቅድሳት እንዲጠበቁ የተጠናከረ አያያዝ አለመኖሩ ሌላው ትልቅ ጉድለት ነው:: እጅግ ውድ የሆኑ ቅርሶች ያሉባቸው ብዙ ገዳማትና አድባራት የሚደረግላቸው ጥበቃ በጣም አናሳ ነው::

ምናልባት ዕድል ገጥሟቸው በተወሰኑ ቦታዎች በተሠሩላቸው ሙዝየሞችና ቤቶች በክብር ተቀምጠው የሚጎበኙና የሚያገለግሉ ንዋያተ ቅድሳት ቢኖሩም፤ በበርካታው የአገራችን ክፍል የሚገኙ ንዋያተ ቅድሳት፤ ለእነሱ በማይገባ ቦታ እንደአልባሌ ዕቃ ተቀምጠው በእጅ እየተዳሰሱ ተገላብጠው እየታዩ «የሚጐበኙ» ንዋያተ ቅድሳት ይገኛሉ:: ቀድሞ በጉልምስናቸው ዘመን ባገኙት የቤተክርስቲያንና በእሷም በኩል በንዋያተ ቅድሳቷ ፍቅር ታስረው እዚያው ከንዋያተ ቅድሳቱ ጋር እየተኙ ካሉ አዕሩግ መነኮሳት በስተቀር ከዘራፊ ለመጠበቅ «በሰው ሰው ኛው» ጉልበት ያለው ጠባቂ የለም:: ከዚህም በተጨማሪ ከዚሁ ከአያያዝ ጉድለት የተነሣ በያሉበት በብልና በዝገት እየጠፉ ይገኛል::

3. የዕምነት መጉደል /የፈሪሃ እግዚአብሔር መጥፋት/

ዛሬ ከንዋያተ ቅድሳት ዝርፊያ በተጨማሪ የሰው ልጅ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረውን ወንድሙን በአሠቃቂ ሁኔታ የሚገድለው፣ በወንድሙ ርሃብና ስቃይ ተረማምዶ እሱ የሚጠግብ ከዕምነት መጉደል፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ከማጣት የተነሣ ነው:: ራሳቸውን ለሠይጣን ያስገዙት ይቅሩና በመንፈሳዊነት ጐራ የሌሉ፣ ለሥጋዊ ጥቅማቸው ብቻ ቤተክርስቲያንን የተጠጉ አንዳንድ ሰዎች፤ አባቶቻችን መከራውን ሁሉ ታግሰው ያቆዩትን ንብረት ከሌቦች ጋር በመተባበር ያስዘርፋሉ:: የዚህም ምክንያቱ የመንፈሳዊነት መጉደል ነው::

4. የክርስቲያኖች መፈናቀል

የክርስቲያኖች ክብርና ሞገስ በአካባቢያቸው የሚኖሩ አድባራትና ገዳማት እንደሆኑ ሁሉ ለአድባራቱና ገዳማቱ ከነክብራቸው ተጠብቆ መኖር ምዕመናን ወሳኞች ናቸው:: ነገር ግን ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ በሆኑ ምክንያቶች ሕዝቦች ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ይዘዋወራሉ:: ሰዎች በጦርነት፣ በርሃብና በበሽታ የትውልድ ቀዬአቸውን ለቀው በሚሄዱበት ጊዜ ስመ ክርስትና ጸጋ መንፈስ ቅዱስ የተቀበሉበትን አድባር ትተው ነው:: በዚያን ጊዜ ከላይ በገለጽናቸው ዕምነት የጐደላቸው ሰዎች በውስጣቸው ያሉ ንዋያተ ቅድሳት ይዘረፋሉ::

እንግዲህ ሌሎችም በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ብለን እናምናለን::

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስለችግር ማውራት በራሱ መፍትሄ አይሆንምና ወደ መፍትሄዎቹ እንገባለን::

ንዋያተ ቅድሳት ሀብቶች ናቸው:: ሀብትነታቸውም ለቤተክርስቲያን ነው:: በመሆኑም እንደባለሀብትነቷ ንዋያተ ቅድሳትን በመጠበቁ በኩል ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ኃላፊነት አለባት:: እንዲጠበቁ ከምታደርግባቸው መንገዶች አንዱ ምእመናን ንዋያተ ቅድሳት የአምልኮት መፈጸሚያ፣ የክብራቸው መገለጫ፣ ሀብታቸው መሆናቸውን እንዲያውቁ ማድረግ ነው:: ምንምእንኳ በወንጀሉ በቀጥታ ባይሳተፉም /የሚሳተፉ ግን ንዋያተ ቅድሳት ሲዘረፉ እያዩ በ«እኔምን አገባኝ» ስሜት የሚቀ መጡ ምእመናን

እንዳሉ ዘራፊዎቹ በፖሊስ ተይዘው ከሚ ሰጡት የእምነት ክህደት ቃል መገንዘብ ይቻላል:: ስለዚህ ቤተክርስቲያን በተቻለ መጠን ምዕመናን በአጥቢያቸውና በአካ ባቢያቸው የሚገኙት ንዋያተ ቅድሳት የእ ነሱ እንጂ የማንም እንዳልሆኑ ተረድተው ለክብራቸው ዘብ በመቆም የአባቶቻቸውን አኩሪ ተግባር እንዲደግሙ ማስተማር ይኖርባታል::

ምንም እንኳን ሁሉም ባይሆን አሁን አሁን ከንዋያተ ቅድሳት ዝርፊያ ጋር በተያያዘ ሁኔታ አባቶች ካህናት እን ደተባባሪና እልፍ ሲልም እንደዘራፊ ሲፈ ርጁ ይታያል:: በመሠረቱ ከእነሱ ሀብ ትና ንብረት የንዋያተ ቅድሳቱን ደኅን ነት አስበልጠው ከንዋያተ ቅድሳቱ ጋር እያደሩና እየዋሉ ሕይወታቸውን እስከ ማጣት የደረሱ ሰዎች የመኖራቸውን ያህል፤ ሥጋዊ ጥቅምን በማስቀደም እም ነት ከሌላቸው ጋር በመተባበር ንዋያተ ቅድሳትን የሚዘርፉና የሚያዘርፉ «ካህ ናት» ይኖራሉ:: ታዲያ ቤተክርስ ቲያን እነዚህ ሰዎች በስሟ የተቀመ ጠውን ወንበር ይዘው ነውና ይህንን ኢ- ክርስ ቲያናዊ ድርጊት የሚፈጽሙ ትን ተከታ ትሎ እርምጃ መውሰድ ይኖ ርባታል::

እንዲሁም እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት አንድ ዐቢይ ጉዳይ አለ:: ካህ ናት ሥጋ ለባሽ በመሆናቸው አንዳንድ ጊዜ ከማያዩት ጸጋ መንፈስ ቅዱስ የሚያ ዩት ገንዘብ ሊበል ጥባቸው ይችላል:: እግ ዚአብሔር የተሰወረውን ገልጦት በዝር ፊያው የተባበሩትን ካህናት ፖሊስ በቁጥ ጥር ስር ሲያደርጋቸው /ለመስረቃቸው/ ከሚሰጡት ምክንያቶች አንዱ «የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ በማጣታችን ነው» የሚል ነው:: ዕለታዊውን ነገር ለማግኘት ዘላለማዊውን ማጣት ከአባቶቻችን የተማ ርነው ባይሆንም ላይ በላይ ስናየው ምክ ንያታቸው እውነታ ያለው ይመስላል:: ንብረትነታቸው በገንዘብ ከሚተመን በላይ የሆኑ በርካታ ታሪካዊና ሃይማ ኖታዊ ቅርሶችን በጠባቂነት የተቀመጡ አባላት እንኳንስ ቤተሰባቸውን ጨምሮ ራሳቸውን እንኳ በሚገባ የማይጠውር ደመወዝ ሲያገኙ ሰይጣን የበለጠ እንዲ ነሣባቸው ያደርጋል:: ስለዚህ ቤተክርስ ቲያን የጠባ ቂዎችን ማንነት ማለትም መንፈሳዊ ብስለት ከማወቁም በተጨማሪ ሊኖርባ ቸው የሚችለውን ችግር ልት ገነዘብ ይገባል::

ከዚሁ ጋር ቤተክርስቲያን በቅ ርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅት እንዲ ሁም በክልል የባሕልና ማስታወቂያ ቢሮዎች በኩል ለሚካሄዱ የታሪካዊና ባሕላዊ ቅርሶች ምዝገባና ቁጥጥር ግን ባር ቀደም ሆና የማስተ ባበር ኃላፊነት አለባት::

ከላይ እንደተገለጸው ለንዋ ያተ ቅድሳት መዘረፍ አንዱ ምክንያት የንዋ ያተ ቅድሳቱ ለሌባ በተጋለጠ ሁኔታ መቀመጣቸው ነው:: ቤተክርስቲያንን የሚጠብቅ አምላክ እየጠበቃቸው እንጂ በብዙዎቹ የገጠር አድባራትና ገዳማት ንዋያተ ቅድሳት በገመድ ከመጠገን ባላለፈ ቤት ውስጥ ይቀመጣሉ:: በዚያም ቢሆን ከላይ ከሚ ወርድባቸው ፍሳሽ በተጨማሪ ከታች ከሚፈላባቸው ምስጥና ብል እንዲያ መልጡ ሆነው አይ ቀመጡም:: በመሆኑም ባሉ በት በብልና በም ስጥ ይጠፋሉ:: ከባሰም

ይህንን ችግር ከስሩም ባይ ሆን ከጉኑ ቆርጦ ለመጣል ንዋያተ ቅድ ሳቱ በተሻለ ሁኔታ ሊቀመጡባ ቸው የሚችሉ ቤቶችን በመሥራት ማስቀ መጥ ይገባል:: ምናልባት ሰዎች ሙዝየም የሚለውን ስም የተለየ ትርጉም ሰጥተው እኛ እዚያ አንደርስምና እንዳለን ያለንን ይዘን እንቀመጥ ካሉ በስተቀር በመስታ ወት አሽብርቆ የሚሠራው የቅርሳ ቅርስ ማስቀመጫ «ቤት» ና በጥሩ ሁኔታ በእንጨት የተሠራው ማስቀመጫ «ቤት» በመሠረታዊ አገልግሎታቸው ልዩነት የላቸውም:: ሁለ ቱም ንዋያተ ቅድሳት ተከብርው ይቀመጡባቸውና አገልግሎ ትም ይሰጡ ዘንድ የተሠሩ ናቸው:: ስለዚህ አድባራቱና ገዳማቱ በሚገኙ በት ቦታ አቅም እንደፈቀደ «ሙዝየም» ሠርቶ ንዋያተ ቅድሳቱን ከዝርፊያና ከብልሽት ማዳን ይጠበቅብናል:: ለዚህ ሥራ ተግባራዊነት ምእመናን በተለይ ወጣት የሰን በት ትምህርት ቤት አባላት ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው::

የንዋያተ ቅድሳትን በአጠቃላ ይም የታሪካዊና ባሕላዊ ቅር ሶችን ስር ቆትና ዝርፊያ ለመከላከል ሊጠቀሱ ከሚ ችሉ ሌሎች መፍትሔዎች ውስጥ ምዝገባ አንዱ ነው:: ቅርሶችን ቆጥሮ በመመዝገብ ባሉበት እንዲጠበቁ ማድረግ የቅርስ ጥና ትና ጥበቃ ድርጅት ኃላፊነት ነው ቢባ ልም፤በተለይ ንዋያተ ቅድሳትን በሚ መለ ከት ቤተክርስቲያን በግሏም ሆነ ከድር ጅቱ ጋር በመተባ በር ግንባር ቀደም ኃላፊ ናት:: ንዋያተ ቅድሳት ከብዛታቸው የተነሣ የተቀመጡበት ተዘበራርቆ ካልተ ገኘ በስተቀር የተሰረቀው የማይ ታወ ቅበት አጋጣሚ ይበዛል:: ይህም የሆነው ንዋያተ ቅድሳት በተቀመጡበት በስነ ሥርዓት ተመዝግበው ባለመያዛቸውና ዕለት ዕለት ባሉበት መኖራቸው ባለመ ታየቱ ነው:: ስለ ዚህ ንዋያተ ቅድሳት በጥሩ ቦታ መቀመጣቸው ብቻ ሳይሆን መመ ዝገብም አለባቸው:: ይህም ሲደረግ ነገ ሮችን መዝግቦ በመያዝ ዕለት ዕለት መቆጣጠር ራሱን የቻለ ዕውቀት በመ ሆኑ ያንን የሚያከናውኑ ሰዎችን ማሠ ልጠን ይገባል:: ስለዚህ በሙያው ጥልቅ ዕውቀት ባላቸው ሰዎች አማካኝነት ሥል ጠና በመስጠት የንዋያተ ቅድሳትን ዝር ፊያና ብልሽት መታደግ ያስፈልጋል:: በዚህ ነገር ሰንበት ት/ቤቶች ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው ልንገልጽ እንወዳለን::

እንግዲህ ከላይ ለንዋያተ ቅድ ሳት ዝርፊያ እያደር መባባስ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው ያልናቸውን ነጥቦች በመጠኑ ተመልክተን ይህንን ለመግታት እንድንችል ምን እናድርግ? ለሚለው በመጠኑም ቢሆን መፍትሄዎችን ለማ የት ሞክረናል:: ነገር ግን ለአንድ ችግር መፈታት ወሳኙ ተቸጋሪው ነውና የዛሬው የንዋያተ ቅድሳት ችግር የሁሉም ኦርቶ ዶክሳውያን ብሎም የኢትዮጵያውያን በሙሉ ነው እንላለን:: አምላከ ቅዱሳን እግዚአብሔር በንዋያተ ቅድሳቱ የምንጠ ቀም እንጂ የምን ወቀስ አያድርገን አሜን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

✠ ✠ ✠

## ሞቴን ከመጠበቅ ሌላ

ከገጽ 30 የዞረ

ጭንቀትህን ያቀልልሃልና ንስሐ ከመግ ባት አታመንታ:: ማቴ 11÷28::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎ ስም «እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገሩ ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናው ቃለን» እንዳለው ክርስቲያን ኀዘን ይሁን ደስታ የሚደርስበት ነገር የበለጠ ወደ እግዚአብሔር የሚያ ቀርበው እንጂ ከእግዚአብሔር የሚለየው ሊሆን አይገባም:: ሮሜ 8÷28:: ስለዚህ በበሽታው በመያዝ መዓት እንደወረደብህ ተመልክተህ ተስፋ አትቁረጥ:: ለበጎ ሊሆን እንደሚችል ተቀብለህ ሕይወ ትህን ልታስተካክል ያስፈልጋል:: ማን ያውቃል እግዚአብሔር ከፈ ቀደ ለሰዎች ይከብዳቸው ይሆናል እንጂ እርሱ ምንም የሚሳነው ነገር ስለሌለ በቀላሉ ትድን ይሆናል:: ደግሞም በእምነት ከተ ጓዝክ ትድናለህ:: እግዚአብሔር የሚያድንህ ሰዎች እንደሚያድኑህ አይደለም:: ነፍስህንም ሥጋህንም ያድንሃል:: ማር. 2÷1-12:: በሥጋ ባትድንም እንኳን ሰማያዊ ተስፋ ስላለህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ሊያስጨንቅህ አይገባም::

ይልቁንም እንደ ክርስቲያ ንነትህ ካለፈው ተምረህ በቀረው የሕይወት ዘመንህ ለሌሎች ሊተ ርፍ የሚችል መልካም ሥራን ሥራ:: ምናልባትም እስከዛሬ ከኖርክበት ረጅም ጊዜ ይልቅ በቀ ረው ጊዜህ የበለጠና የተቀደሰ ሥራ ትሠራ ይሆናል:: በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ደግሞ ትልቁ ደስታም ይኸው ነው:: ረጅም ዕድሜ ኖረቸው ምንም ቁምነገር ሳይሠሩበት ከሚያል ፉት ይልቅ በአጭር የዕድሜ ዘመናቸው ብዙ ሥራዎችን ሠር ተው የሠሩት የበለጠ ክብርና ዋጋን ያገኛሉ::

በመሆኑም በቀሪው ዕድሜህ /ረጅም ይሁን አጭር አንተ የምታቀው ነገር የለምና/ በማኅበራ ዊም ሆነ በመንፈ ሳዊ ሕይወትህ መልካም ሥራን የምትሠራበት ሊሆን ይገባል:: በአካባቢህ ያሉትን ሰዎች በማስተማር፣ በበሽታው የተ ያዙት ወገኖችን በማጽናናት፣ ለሌሎች ጥንቃቄ በማድረግ ወዘተ... አሳልፍ:: ያንጊዜ ጨልሞ የነበረው ሕይወትህ ይበራል:: አንተም በኑሮህ ደስተኛ ትሆናለህ:: ሰማያዊውንም ዋጋ ታገኛለህ:: ስለሁሉም እግዚአብ ሔር ይርዳህ::ድንግልም አትለይህ::

## ከመጻሕፍቶቻችን

### *አባ ጎርጎርዮስ ፣*
### <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣</u>
### *ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፣*
### *አ/አ ፣ 1986*

አባ ጎርጎርዮስ ከአባታቸው ከአቶ ገበየሁ እሰዬ ከእናታቸው ከወ/ሮ አሰለፈች ካሤ በ1932 ዓ.ም. በደሴ ከተማ ተወለዱ። በሕፃን ልባቸው የመስቀሉ ፍቀር የተለኮሰው አባ ጎርጎርዮስ፣ ያገራችንን መንፈሳዊ ዕውቀት በስፋትና በጥልቀት ገብይተዋል። ዝናቸው ከታወቀው የተለያዩ የኢትዮጵያ ገዳማትና ብቃታቸው ከተመሰከረላቸው ሊቃውንት ዘንድ ዜማ፣ትርጓሜ መጻሕፍት፣ አዕማደ ምሥጢር፣ ባሕረ ሃሳብ፣ ቅኔ ት/ተ ሃይማኖት አጠናቀው ተምረዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ከነበሩት ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት በ1971 ዓ.ም. ጳጳስ ሆነው የተሾሙት አባ ጎርጎርዮስ ሐምሌ 22 ቀን 1982 በመኪና አደጋ እስከአለፉበት ዘመን ድረስ ስምንት መጻሕፍት ደርሰዋል፡ ከእነዚም ውስጥ ለኅትመት የበቁት <u>መሠረተ እምነት</u>፣ <u>የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረ ክና</u> ይኸው <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ</u> ናቸው። ለኅትመት ባይበቁም ሌሎች አምስት ያህል ሥራዎች እንዳሏቸው ደቀመዛሙርቶቻቸው ይናገራሉ። አባ ጐርጐርዮስ ልዩ በሆነና ፍቅርን በተመላ መንፈሳዊ ስሜት ዘወትር እንዲታሰቡ የሚያደርጓቸው አያሌ ቁም ነገሮች አሉ። ዋና ዋናዎቹ መንፈሳዊ አገልግሎታቸው፣ትምህርታቸው፣ ሰብአዊ ባሕርያቸው የምርምር፣ የሥነ ጽሑፍና የማስ ተማር ተሰጥዎአቸው ናቸው። አባ ጐርጐርዮስ ዘመናዊ ውንም ትምህርት ከዩኒቨርስቲ በቲኦሎጂ /ነገረ መለኮት/ በማስትሬት ዲግሪ ተመርቀዋል፣ ፈረንሳይኛና አረብኛ ቋንቋም አጥንተዋል።

20 ሴ.ሜ በ 14 ሴ.ሜ የሆነው ይህ መጽሐፍ 11 ምዕራፋት ያሉት ሲሆን አገራችን ኢትዮጵያ በዘመነ ኦሪት፡ በኋላም የክርስትናን እምነት ከተቀበለችበት ወቅት አንሥቶ እስከ አሁን የተጓዘችባቸውን ወጣ ገብ የታሪክ ሂደቶች ወለል አድርጐ የሚያሳይ፣ በሥዕላዊ ቃላት የተኳሉ ጥልቅ ሃሳቦችን ፍንትው አድርጐ የሚገልጽ ድንቅ መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ የቤተክርስቲያ ናችንን መሠረተ እምነት /ዶግማ/፣ የታቦት፣ የሥዕልና የመስቀልን ክብር፣ የአማላጅነት ምሥጢር፣የቤተክርስቲያን ትውፊትና ሥሪት ግልጽ በሆነ ሁኔታ አብራርቶ ያስረዳል። ኤኩሜኒዝም ወይም ዓለም አቀፍ የክርስቲያኖች ንቅናቄ ምንነት በውል የተነተነና ይልቁንም በንቅናቄው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ድርሻና ተሳትፎ በግልጽ የሚያቀርብ ነው። በ193 ገጾች ብቻ ታሪክን ከምሥጢራት፣ መሠረተ እምነትን /ዶግማ/ የያዘው ይህ መጽሐፍ በ1986 ዓ.ም. ለሁለተኛ ጊዜ ታትሟል። በሁለተኛ እትም መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ገጾች «ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሕያው መንፈሳዊ አባት» በሚል ርዕስ የደራሲው የሕይወት ታሪክ በስፋት ቀርቧል።

## ዜና አድባራትና ገዳማት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በልማት ክፍሉ ሥር ያዋቀረው የገዳማትና አድባራት ማቋቋሚያና መርጃ ንዑስ ክፍል ምእመናንን በማስተባበር ለተቸ ገሩት ገዳማትና አድባራት ርዳታ መስጠቱን ቀጥሏል። ርዳታቸው የዋለበትን ማወቅ እንደሚገባቸው ባለን ጽኑ እምነት መሠረት ከዚህ በፊት የተሰጠውን ባለፉት እትሞቻችን ማውጣችን የሚታወስ ሲሆን ከዚያ ወዲህ የተከናወኑትን ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበናል።

1. በምዕራብ ጐጃም ሀገረ ስብከት ለናዳ ማርያም ገዳም የአብነት ተማሪዎች የመማሪያ ደብተር /ለእነርሱ በሚሆን መልኩ የተዘጋጀ እና ስክሪብቶ/
2. በሰሜን ሸዋ ሀ/ስብከት አቡነ ዜና ማርቆስ ገዳም 5 ጣቃ ልብስ
3. በሰ/ወሎ ሀ/ስብከት ለጭራ መድኃኔዓለም ገዳም 4 ጣቃ ልብስ
4. ምስካየ ስዑዳን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ካኩማ /ኬንያ የስደተኞች ቤተክርስቲያን/ የጸሎት መጻሕፍት፣ጀንጥላ፣ዕጣን ዘቢብና ጧፍ
5. አጄ.ሬ ተ/ሃይማኖት ቤተክርስቲያን /ወላይታ/ ዕጣንና ጧፍ
6. ለበቅሎ አዛኝ ቅድስት ማርያም /ሰ/ሸዋ/ ዕጣንና ጧፍ

ከዚህ በተጨማሪ ለገዳማትና አድባራት ዘላቂ ፕሮጀክቶችን ነድፎ ለበጐ አድራጊዎች ለማቅረብና በተናጠል ከሚደረግ ርዳታ ይልቅ የበታውን ችግር ለዘለቄታው በሚፈታ መንገድ ለማስተባበር ጥናቱ ተጠናቅቋል። በዚህም መሠረት፡

♠ ለአንድ ገዳም የመስኖ ፕሮጀክት ተሠርቶ ያለቀ ሲሆን ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም የበጐ አድራጊዎችን ርዳታ በማሰባሰብ ላይ እንገኛለን።

♠ ለአንድ የአብነት ት/ቤት የጉባኤ ቤት ሥራ በመከናወን ላይ ነው።

የሁለቱን ጠቅላላ ሪፖርት ሥራ ዎቹ ሲጠናቀቁ በፎቶ ግራፍ አስደግፈን እንገልጣለን።

በተናጠል የምናደርገውን ሥራ ብናቀናጀው ችግሮችን ለዘለቄታው ለመፍታት እንችላለን። አብረውን ሊሠሩ ከፈለጉ

የባንክ ቁጥራችን
ወ/ት ቅድስት ዓለሙ እና/ወይም
አቶ ዮሐንስ አፈወርቅ
4 ኪሎ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
ቅርንጫፍ
የባንክ ሂሳብ ቁጥር 89269
አዲስ አበባ

*በአካል መምጣት ከፈለጉ*

ከቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተክ ርስቲያን አጠገብ ከብሔራዊ ሙዚየም ጀርባ በሚገኘው ጽ/ቤታችን ያገኙናል።

ስልክ 11 48 70
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ

ለጽ/ቤታችን ከቀረቡት የርዳታ ጥያቄዎች

- ❖የጸሎትና የቅዳሴ መጻሕፍት
- ❖ምንጣፍ
- ❖መጋረጃ
- ❖የቅዳሴ ንዋያተ ቅድሳት

አቡጀዲ ስለሆኑ እነዚህን በዓይነት ብትለግሱን ከደረሱን በኋላ ከተቀበለው አካል ማስረጃዎችን ለመስጠት ዝግጁ ነን።

በማኅበረ ቅዱሳን ልማት ክፍል የገዳማትና አድባራት ማቋቋሚያና መርጃ ንዑስ ክፍል


## በሐመር መጽሔትና በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያችን

- ❖ የትምህርተ ሃይማኖትና የጸሎት መጻሕፍት
- ❖ የተለያዩ የመዝሙርና የስብከት ካሴቶች
- ❖ ንዋያተ ቅድሳት
- ❖ የስጦታ ዕቃዎች ...አሉን

በተጨማሪም የፎቶ ኮፒ እና የካሴት ማባዛት አገልግሎት ጀምረናል። ብቅ ብለው ይጎብኙን።

<u>አድራሻ</u> ፣ ከቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያንፊት ለፊት ከሸዋ ዳቦ ቤት ጐን ከሚገኘው ማከፋፈያችን

ስልክ 11 48 70
ፖስታ 80078

እነዚህን ሁሉ በሚከተሉት ቅርንጫፎቻችን ያገኛሉ

❖ ጅማ፣ባሕር ዳር፣አዋሳ፣አርባ ምንጭ ፣ጎንደር፣ጋምቤላ









# ስምዐ ጽድቅ

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ













ዋጋ 3 ብር

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡